# ሽመልና አንጥረኝነት በጃናሞራ ወረዳ

በ
መሰረት ብርሃኔ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር
በሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር
ክፍል ትምህርት የማስተርስ ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ

ሰኔ 2003
አዲስ አበባ

# ሽመናና አንጥረኝነት በጃናሞራ ወረዳ

በ
መሰረት ብርሃኔ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር
በሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ በኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር
ክፍለ ትምህርት የማስተርስ ዲግሪ ለማሟላት
የቀረበ

ሰኔ 2003
አዲስ አበባ

# ሽመናና እንጥረኛነት በጃናሞራ ወረዳ

በ
መሰረት ብርሃኔ

አማካሪ
ዘሪሁን አስፋው

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር
በሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ በኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር
ክፍለ ትምህርት የማስተርስ ዲግሪ ለማሟላት
የቀረበ

ሰኔ 2003
አዲስ አበባ

# የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ADDIS ABABA UNIVERSITY
I L S
LIBRARY

ፈታኝ

ፊርማ

## ማውጫ


ምስጋና ........ I
አጠቃሎ ........ II
1. መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2
1.3 የጥናቱ አላማ ........ 2
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 3
1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 4
1.6 የጥናቱ ዘዴ ........ 4
1.6.1 ቃለ መጠይቅ ........ 5
1.6.2 ምልከታ ........ 7
1.6.3 የተተኳረ ቡድን ውይይት ........ 7
1.7 የጥናቱ አደረጃጀት ........ 10
1.8 የመስክ ተሞክሮ ........ 10
1.9 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎቻቸው ........ 12
2. ክለሳ ድርሳን ........ 15
2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 15
2.2 የንድፈ ሃሳቦች ቅኝት ........ 17
2.2.1 የቁሳዊ ባህል ምንነት ........ 17
2.2.2 የቁሳዊ ባህል ጥናት አስፈላጊነት ........ 20
2.2.3 የቁሳዊ ባህል አተናተን ሂደቶች ........ 22
2.2.3.1 የቁሳዊ ባህል አተናተን ከPrown ቲዎሪ አንጻር ........ 23
2.2.3.1.1 ገለጻ ........ 23
2.2.3.1.2 ትርጓሜ ........ 24
2.2.3.1.3 ማመላከት ........ 24
2.2.3.2 የቁሳዊ ባህል አጠናንና አተናተን ከFleming ቲዎሪ አንጻር ........ 25
2.2.3.2.1 መለየት ........ 25
2.2.3.2.2 ግምገማ ........ 26
2.2.3.2.3 ባህላዊ ትንታኔ ........ 26

2.2.3.2.4 ትርጓሜ ........ 27
3. የጃናሞራ አካባቢያዊና ማህበረ ባህላዊ ዳራ ........ 28
3.1 የተጠኚ አካባቢ መግለጫ ........ 28
3.2 የህብረተሰብ መግለጫ ........ 28
4. የሽመናና የአንጥረኝነት ቁሳዊ ባህል ........ 32
4.1 የሽመና መስሪያ ቁሶች ስምና አገልግሎት ........ 32
4.2 በሽማኔዎች የሚሰሩ ቁሶች አሰራርና ተግባር ........ 41
4.3 የሽመና ሙያተኞች ሕይወት ........ 49
4.4 የአንጥረኞች መስሪያ ቁሶች ስምና አገልግሎት ........ 58
4.5 በአንጥረኞች የሚሰሩ ቁሶች አሰራርና ተግባር ........ 61
4.6 የአንጥረኝነት ሙያተኞች ሕይወት ........ 71
4.7 የትዕምርታዊ ቁሶች ትንተና ........ 76
5. ማጠቃለያና ይሁንታ ........ 81
የተጠቀሱ ምንጮች ........ 85
አባሪ 1 ሽማኔዎች ለስራቸው የሚገለገሉባቸው ቁሶች ........ 1
አባሪ 2 አንጥረኞች ለስራቸው የሚገለገሉባቸው ቁሶች ........ 3
አባሪ 3 በሽመና የሚገኙ ቁሶች ........ 4
አባሪ 4 በአንጥረኝነት የሚገኙ ቁሶች ........ 5
አባሪ 5 የአውራ መረጃ አቀባይ ፕሮፋይል ........ 6
አባሪ 6 የአጋዥ መረጃ አቀባይ ፕሮፋይል ........ 9
አባሪ 7 ሽማኔዎችንና አንጥረኞችን በጋራ ለማወያየት የቀረበ መጠይቅ ........ 10
አባሪ 8 ሽማኔዎችንና አንጥረኞችን በግል ለማወያየት የቀረበ መጠይቅ ........ 11
አባሪ 9 የፖሊስ ንባብ ........ 23



Amhara Region/Ethiopia
Therapeutic Feeding Programmes
Suported by UNICEF as of July 2005
Weredas where Integrated Therapeutic Feeding Units to be Established
Weredas where Functional Therapeutic Feeding Centers and Therapeutic Feeding Units Exist.
Wereda label indicates name of the wereda, Partner and Max Capacity
Wereda Boundary
Zone Boundary
Dabark (Gov ; 20)
Dabat (Gov ; 20)
W. Hamra
Sekota (Gov ; 30)
N. Gondar
Gondar (Gov ; 30)
Gondar (Gov ; 20)
Belessa (Gov ; 20)
Kamaham (Gov ; 30)
Kamaham (Gov ; 20)
Ebinat (Gov ; 20)
Bugna (Gov ; 30)
N. Wello
Debre Tabor (Gov ; 30)
Meket (Gov ; 20)
Woldiya (Gov ; 30)
Habru (Gov ; 30)
S. Gondar
Lay Gayint (Gov ; 20)
Bahir Dar (Gov ; 30)
Bahir Dar
Estie (Gov ; 20)
W. Gojam
Simada (Gov ; 20)
Tenta (Gov ; 20)
Dessie (Gov ; 20)
Bati (Gov ; 20)
Sayint (Gov ; 20)
Dessie (Gov ; 30)
Dessie (Concern ; 300)
Kombolcha (Gov ; 20)
Kalu (Concern ; 300)
Agew-Awi
S. Wello
Dewa Cheffa (Gov ; 20)
E. Gojam
Kelela (Gov ; 20)
Oromiya
Gera Keya (Gov ; 30)
Efratana Gidim (Gov ; 20)
Debra Markos (Gov ; 30)
Dejene (Gov ; 20)
Merha Bete (Gov ; 30)
Kewet (Gov ; 20)
N. Shewa (R3)
Debre Berhan (Gov ; 30)
Boundaries are approximate and unofficial
Graphic by ENCU/EWD, DPPC Ethiopia July 2005



የጃናሞራ ወረዳና ቀበሌዎች
ጠቋሚ ካርታ
አዲ አርቃይ ወረዳ
በየዳ

# ምስጋና

በተደጋጋሚ ጊዜ ያለመሰልቸት ወረቀቴን በማረም አስተያየትና ምክር ለለገሱኝ ካደረጉልኝ ርዳታ አንጻር የጥቂት ቃላት ምስጋና የሚያንሳቸው ቢሆንም መጀመሪያ መምህሬንና አማካሪየን ዘሪሁን አስፋውን አመሰግናቸዋለሁ።

በመቀጠል የድህረ ምረቃ ትምህርት እንድማር ያደረገኝን የመደወላቡ ዩኒቨስቲን አመሰግናለሁ። ለጥናቴ ጥቂት የገንዘብ ርዳታ ስላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን አመስግነዋለሁ። መስክ ከመሄዱ በፊትና በኋላ በስልክና በአካል መረጃ ለለገሳችሁኝ መረጃ አቀባዮች በሙሉ ስለድጋፋችሁ አመሰግናችኋለሁ። እንዲሁም የጃናሞራ ወረዳ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ካሜራ ቀራጺ መላሽ መኳንንትና የፕሬስ ጉዳይ ሰራተኛዋ ወሰን አያሌው የመደበኛ ስራችሁን ጊዜ በመተላለፍ ጭምር ስለረዳችሁኝ ምስጋናየ ይድረሳችሁ።

ሳለዲን ሃሰን ለጥናቴ ኮምፒውተር እንደሚያስፈልገኝ ባወጋን ጊዜ መግዛት ብትፈልግም ያለአቅድህ ገዝተህ እንድጠቀምብት ስለፈቀድክ አመሰግንሃለሁ። በመጨረሻም አብዲ ተማም ለጥናቴ የሚያግዙ ሃሳቦችንና የአርትኦት ስራ ስለረዳኸኝ አመሰግንሃለሁ።

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት "የሽመናና የእንጥረኝነት ሙያ በጃናሞራ ወረዳ" በሚል ርዕስ ሳዘጋጅ ዋና ዓላማ አድርጌ የተነሳሁት የቁሶቹን ስያሜ፣ አገልግሎት፣ የአሰራር ሂደት እንዲሁም የሙያተኞቹን ሕይወት ማሳየት ነው። እንዲሁም በሙያተኞቹ ላይ የተነገሩ ቃል ግጥሞችን መሰብሰብና መተንተን ነው። እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የቃለ መጠይቅ፣ የምልከታና የተተኳሪ ቡድን ውይይትን መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ አድርጌ ተገልግያለሁ። በእነዚህ ዘዴዎች የተገኙት መረጃዎችም በምዕራፍ ሁለት በቀረቡት የFleming፣ Prown እና Schlereth ቲዎሪዎች ተቃኝተው በገለጻ ስልት ትንተና ተደረገባቸዋል። ትንታኔውም የሚከተሉትን ግኝቶች አምጥቷል።

ሙያተኞቹ ለመስሪያ ቁስነት 38 ያህል ቁሶችን ሲጠቀሙ፣ የስራ ውጤቶቻቸው ደግሞ 29 ያህል ቁሶች ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ 13 ያህሉ በሽመና፣ 16 ያህሉ ደግሞ በእንጥረኝነት ሙያ የሚገኙ ናቸው። አብዛኛዎቹ ሙያተኞች ሙያውን የለመዱት በዘር ከትውልድ ወደ ትውልድ በልምድ እየለመዱ ያወቁት ሲሆን፣ የተወሰኑት ደግሞ አጭር ሥልጠና ወስደው የለመዱ መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል። ጠቁሟል። ሙያተኞቹ ቁሶችን የሚሰሩበት ብዙም የተለየ ቀንና ቦታ የለም። ቢሆንም ወርቅ ለመስራት ግን ሊነጋ ወገግ ሲል ከሙያተኞች ውጭ ሰው በማይኖርበትና በማይገባበት ወቅት እንደሚሰራ ጥናቱ

በጥናቱ የተተነተኑት ቁሶች በህብረተሰቡ ዘንድ አገልግሎት ላይ በሚውሉበት ጊዜ ከተቀድሞ ሚናቸው ባሻገር ትዕምርት/ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሚና/ እንዳላቸው ታይቷል። እንዲሁም አሁንም ድረስ ሙያተኞቹ በተለይ እንጥረኞቹ ኑሯቸውን በተጽዕኖ እንደሚገፉም ጭምር ጠቁመዋል። ገቢያውን በሚመለከት በሁለቱም ሙያዎች ጥሩ የሚባል ገቢ ያገኛሉ።

ከላይ የተገለጹትን ግኝቶች መነሻ በማድረግ ቢደረግ ይበጃል ያልኩትን የሚከተለውን የይሁንታ ሃሳብ አስቀምጫለሁ። የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ የወረዳው ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤትና የወረዳው የጥቃቅን ንግድ ኢንዱስትሪ ጽ/ቤቶች በአካባቢው የሚገኙ ቁሶችን በመለየትና በመቅረስ፣ ሙያተኞቹን በመደገፍና ገበያ በማፈላለግ ስራ ቢሰሩ። እንዲሁም የቁሳዊ ባህል ጉዳይ የሚመለከታቸው ተቋማት በጉዳዩ ላይ በትኩረት የሚንቀሳቀሱበትና የሚሰሩበትን ሁኔታ መፍጠር ቢችሉ የሚል ሃሳብ አለኝ።

## 1.መግቢያ

ይህ ክፍል በተለያዩ ንዑሳን ርዕስ ጉዳዮች የተከፋፈለ ሲሆን፣ የሚከተሉትን ጉዳዮች በዋናነት አንስቷል፡፡ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ ዓላማዎች፣ ጠቀሜታዎች፣ ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው፣ የመስክ ቆይታ፣ የጥናቱ ወሰንና የጥናቱ ዘዴ እንዲሁም የጥናቱ አደረጃጀት ናቸው፡፡

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ይህ ጥናት በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር ዞን በጃናሞራ ወረዳ ስር ባሉ ሁለት ቀበሌዎች(ደረስጌ እና መካነብርሃን) የሚገኙ አንጥረኞችና ሸማኔዎችን ሕይወት የሚያጠና ነው፡፡ ሽመናና አንጥረኝነት ደግሞ በቁሳዊ ባህል ስር የሚካተት/የሚጠና የሃገረሰባዊ እጅስራ ዘርፍ ነው፡፡

ቁሳዊ ባህል (material culture) ፤ አንዳንድ ምሁራን artifact በሚል ሲጠቀሙበት ተስተውሏል፤ ከፎክሎር ዘርፎች መካከል አንዱ መሆኑን ምሁራን ገልጸውታል፡፡ ከእነዚህ መካከል ፈቃደ (1991፡15) ፤ Dorson (1972:2) እና Wilson (1986፡229)[1] ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ቁሳዊ ባህል የተለያዩ ሰፋፊ ክፍሎች ያሉትና በሰፊው የሚጠና ነው፡ ፤ የዚህ ጥናት ትኩረት ከነዚህ የፎክሎር ዘርፎች ከሆኑት አንዱ ሃገረሰባዊ እጅ ሥራ (Folk craft) የሚባለው ሲሆን ከዚህ ውስጥ አንጥረኝነትንና ሽመናን ተመልክቻለሁ፡፡

"ቁሳዊ ባህል በቁስ የሚገነባ ሲሆን ሲነሳ መሰረት የሚያደርገው ቁሱን ቢሆንም በቁሱ ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡ ቁሳዊ ባህል ቁሱ በሰው አመለካከት ላይ የሚያሳድረውን ሁኔታ (ተጽዕኖ) እና ቁሱ ለሰው ያለውን ትዕምርትና ተግባር የሚያሳይ ነው፡፡" Glassie(1999: 41) ጥቅሱ እንደሚያሳየው ቁሣዊ ባህል ሲባል ቁሱ ብቻ ሳይሆን በቁሱ አሰራር፣ ትዕምርት፣ ዋጋ ወይም ሌላ ምክንያት ሰበብ በማድረግ በቁሱ አማካኝነት ያለን

---

[1] የገበት ስሁተትን ለማስወገድ ሲባል በእንግሊዝኛ የተጻፉ ስሞች በእንግሊዝኛ፣ የህትመት ዘመናቸው ደግሞ በሙገኛ ቋንቋቸው እ.ኤ.አ ነው፡፡ በአማርኛ የተጻፉ ስሞችና የህትመት ዘመናት የቀረቡት በሙገኛ ቋንቋቸውና በግሙተ ምህረት የቀረቡ ሲሆን፣ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የየትኛውም አገር ጹሑፍያን ስራዎች በአንድ ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ በተከታታይነት ሲመጡም በዘመን ቅደም ተከተላቸው ከተደምት ወደ አዲስ በሚል ቀርበዋል፡፡

የሰው አመለካከት እና ሙያ እንዲሁም ሰው ለቁስ፣ ሰው ለቁሱ ተጠቃሚ እና ሰው ለቁሱ ስራ የሚሰጠውን ዕምነት፣ ትዕምርትና ተግባር የሚያጠቃልል ነው።

Woodward (2007) BMW መኪና እና የግል ጀት (Jet) አውሮፕላን ቁሳዊ ባህል እንደሆኑ ጠቁመዋል። በምክንያትነት ያስቀመጡትም ህብረተሰቡ ለባለቤቶቹ(ገዝተው ለሚጠቀሙት) የሚሰጠው ቦታ ቁሶቹ ከቁስ የዘለለ ሚና እንዲኖራቸው አድርጓል። ቁሱ የባለቤቱን ቱጃር እና ባለጸጋ መሆንን ያመለክታሉና። ምክንያቱም ሰዉ ለቁሱ ሰጠው እሴት፣ አመለካከት ስላለ ነው።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በቁሱና በማህበረሰቡ /በህብረተሰቡ/ መካከል ያለውን ግንኙነት እና የሙያተኞቹን ህይወትና ሙያ ለማሳየት የሚለው የጥናቱ አንዱ አነሳሽ ምክንያት ነው። ጥናቱ በሚደረግበት አካባቢ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች በሽመናም(ከአልባሳቱ) ሆነ በአንጥረኞች በሚሰሩት ቁሶች የመጠቀማቸው ነገር እየቀነሰ በመሄዱ ባህሉ ሳይቀየጥ ወይም ሳይጠፋ ቁሱን፣ የቁሱን ቅርጽና አገልግሎት ለማሳየት የሚለው ሌላው ምክንያት ነው። እንዲሁም በጥቂቱም ቢሆን የሚፈልግን አካል ይረዳ ዘንድ ቀርሶ ለማኖር፣ ቁሳዊ ባህሉቹ እንዲጠበቁና ቀጣይነት እንዲኖራቸው የሚያግዙ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለመሰንዘር ስል ይህን ጥናት ለማድረግ ችያለሁ።

የወረዳው ቁሳዊ ባህል ትኩረት ተሰጥቶት መጠናት ሲገባው ትኩረት መነፈጉ፣ ምክንያቱም ከሌሎች በበለጠ ለለውጥ የተጋለጠ ስለሆነ ነው። በተለይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በወረዳው ቁሳዊ ባህልም ሆነ በሌሎች የፎክሎር ዘርፎች ምንም አይነት ጥናት ባለመኖሩ በተመረጠው አካባቢ በሚገኙ ቀበሌዎች ላይ ጥናት ለማድረግ በመወሰን ጥናት አካሂጃለሁ።

## 1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በተመረጠው አካባቢ የሚገኙ አንጥረኞችና ሸማኔዎችን ሙያና ሕይወት በመመርመር የቁሱን ምንነት፣ አሰራር፣ አገልግሎት እና የሙያተኞቹን

ሕይወት የሚያሳይ ነው። እንዲሁም ሙያተኞቹን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞችን መሰብሰብና መተንተን ነው። የሚከተሉት የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች ናቸው።

- የቁሶቹን ምንነት፣ ተግባር፣ ባለቤትና አሰራርን ማቅረብ፣ በአሰራራቸው ላይ ለውጥ ተካሂዶ ከሆነ የለውጡን ሁኔታ ከህብረተሰቡ አስተያየት ጋር አናብቦ ማቅረብ፣
- ሙያተኞች(አንጥረኞች) ከሌላው አንጥረኛ ካልሆነው የህብረተሰብ ክፍል ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማሳየት፣
- ሙያተኞቹ (ሸማኔዎች) ከሌላው ሸማኔ ካልሆነው የህብረተሰብ ክፍል ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማሳየት፣

ይህ ጥናት ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች መሰረት አድርጎ ግቡን ለመምታት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል።

- ሙያተኞቹ ምን ምን ዕቃዎችን ይሰራሉ? መቼ ይሰራሉ? ለማን ይሰራሉ? ወዘተ. ቁሶቹ በምን መልክና መቼ ይበጃሉ? መቼ አገልግሎት ይሰጣሉ? የሚሰሩበት የተለየ ቀንና ሁኔታ አለምይ? ካለ ምክንያቱ ምንድን ነው?
- ሙያተኞች ለህብረተሰቡ ያላቸው አመለካከት ምንድን ነው? ህብረተሰቡስ ለሙያተኞች ያለው አመለካከት ምንድን ነው? ቁሱን በማምረት ወይም በመስራትና ባለመስራት የተነሳ የሚፈጠረውን ገጽታ ነው።
- ሙያውን ከማን ተማሩት? ቅብብሎሹስ ምን ይመስላል?
- የገበያው ሁኔታስ ምን ይመስላል?
- ሙያተኞችን ጨምሮ የሕብረተሰቡ ዕምነት፣ ትዕምርት፣ ሃሳብና አመለካከት ከማንጸባረቅ አንፃር በቁሱና በሰዎቹ መካከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል።

- በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ወደ ፊት ሰፊ ጥናት ይካሄድ ዘንድ አዎንታዊ ግፊት ይፈጥራል።
- ጥናቱ በሚካሄድበት አካባቢ ወደ ፊት ጥናት ለሚያካሂዱ አጥኚዎች መነሻ መረጃ በመስጠት ያገለግላል።

አጥኙ ከቤተመጻሕፍት፣ ከጴስክና ከአርካይብ መረጃዎች ከዳሰሰ በኋላ ወደ መስክ በመውጣት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ ከዘዴዎቹ ውስጥ ምልከታ/Observation/፣ ቃለ መጠይቅ /interview/፣ መጠይቅ /questionnaire/ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት/ Focusing group discussion/ ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ከመጠይቅ በቀር ሌሎቹ ጥቅም ላይ ውለዋል:: ለምን? መጠይቅ አልተካተተም ቢባል ሌሎቹን ዘዴዎች በመጠቀም ከመጠይቅ የሚገኘውን መረጃ ማግኘት ስለሚቻል ነው፡፡ ቀጥሎ ዘዴዎቹ አንድ በአንድ ይቀርባሉ፡፡

## 1.6.1 ቃለ መጠይቅ

በዚህ ክፍል የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም መረጃ አቀባይ በመምረጥ በቃለ መጠይቅ በተለይ በዕድሜ፣ ሙያውን በማወቅ፣ ሃሳብን በተብራራ ሁኔታ መግለጽ መቻልና ፈቃደኝነትን መሰረት በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ቃለ መጠይቁ በተዋቀረ እና ባልተዋቀረ መንገድ በመከተል የሚፈለገው መረጃ ተሰብስቦበታል፡፡ እነዚህን መንገድ መጠቀም ለፎክሎር ጥናት በጣም አስፈላጊ እንደሚሆን Kenneth (1964፡109 -110) ፥ Mac Donald (1972:420) ፥ List (1972:447) ይመክራሉ፡፡ "ቃለ መጠይቅ መረጃ ከመረጃ አቀባይ ማግኘትን የሚመለከት ሲሆን የመረጃ አቀባይን ዕውቀት፣ ዕምነት፣ ስሜት፣ ግምት/ መላምት፣ ፍላጎት፣ ስራ ወይም ተግባር ወይም ስለ ቀደመ ነገር በማስረጃ የሚቀርብ ማብራሪያን ነው" Kenneth (1964:104)፡፡

ይህ ጥናት የተዋቀረ ዘዴ መጠቀሙ ለጥናቱ አስፈላጊ ያልኳቸውን መሰረታዊ ጥያቄዎች ቀድሜ አዘጋጅቼ ያቀረብኳቸው ስለሆነ ጥያቄዎቹ ቀርበው ሳይረሱ መልስ እንዲያገኙ ረድቶኛል፡፡ በዚህ ዘዴ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ከላይ እንደተገለጸው ቀድመው መዘጋጀት አለባቸው፡፡ ምክንያቱም ከዓላማው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች ሳይዘነጉ መልስ እንዲያገኙ ስለሚያግዝ ነው፡፡ ዘዴው ይህን ጥቅም ስላስገኘልኝ ተገልግየበታለሁ፡፡

ያልተዋቀረ ቃለ መጠይቅ በመጠቀም እንድም የጠያቂና የተጠያቂ ስሜት ሳይኖር ነጻ በሆነ መልኩ መረጃ ለመሰብሰብ ስለሚያግዝ፣ በወቅቱ የሚሰጠውን መልስ መሰረት አድርጌ ከአእምሮ የሚፈልቁ አዳዲስ ጥያቄዎችን ለመጠየቅና ለጥያቄውም መልስ

ለማግኘት ዘዴው አገልግሎት ላይ ውሏል። እንዲሁም መረጃ አቀባዩ መልስ በሚሰጥበት ጊዜ የሚፈጠሩ ድንገተኛ ጥያቄዎችና የሚሰጡ ምላሶች ለጥናቱ ሙሉ መሆን ስለሚያግዙ ይህን መንገድ መጠቀሙ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ስላለው ዘዴውን ተጠቅሜበታለሁ። ይህን ዘዴ በመጠቀም የተጣረሱ መረጃዎችን ለማጥራት፣ መረጃ አቀባዮች በድንገት የተናገሩትን አስተያየትና ሃሳብ መሰረት በማድረግ ጥያቄ በመጠየቅ፤ እንዲሁም ዘዴው ለመረጃ አቀባዮች ነጻነት ስለሚሰጥ መረጃ አቀባዮች በነጻነት ሰፊ መረጃ እንዲሰጡኝ ተገልግየበታለሁ።

አጥኚ በቃለ መጠይቅ ከመስክ የሰበሰበውን መረጃ ማመሳከር አለበት። ይህንን ሃሳብ በማስመልከት Kenneth የሚከተለውን ሃሳብ ሰንዘረዋል። መረጃ አቀባዩ አጥኚውን ለማስደሰት ብሎ አስደሳች ጉዳይን ብቻ ነቅሶ በማውጣት የተዛባ መረጃ እንዳይሰበስብ አጥኚው ጥንቃቄ ማድረግ ይገባዋል። የመረጃውን ገቢር/fact/ መሆን ለማረጋገጥ በሶስት ዘዴዎች ማረጋገጥ ይቻላል። አንደኛው ዘዴ በቃለ መጠይቅ የተገኘን መረጃ በተደጋጋሚ ምልከታ ማረጋገጥ ይቻላል። ሁለተኛው የማረጋገጫ ዘዴ ተመሳሳይ ጥያቄን ለተለያዩ መረጃ አቀባዮች መጠየቅ። መረጃ አቀባዮች አንዱ ከአንዱ የተሻለ መረጃና ተጨማሪ መረጃ ሊሰጡት ይችላሉ። ሶስተኛው ዘዴ የተለያዩ ቃለ መጠይቆችን አዘጋጅቶ ተመሳሳይ ጥያቄ ለተመሳሳይ ሰው መጠየቅ። ይህ ዘዴ መረጃ አቀባዩ እና አጥኚው በተደጋጋሚ ሲገናኙ ወዳጅነታቸው ከፍ ብሎ ለአጥኚ ብዙ መረጃ ሊሰጡት ይችላሉ፤ (Kenneth፡113 - 114)።

ከላይ እንደተገለጸው የተጠቀሱትን መረጃ መሰብሰቢያ ሆነ የመረጃን ትክክለኛነት ማረጋገጫ ዘዴዎች በጥናቱ ለመተግበር ጥረት አድርጌያለሁ፤ በጎ ምላሽም አግኝቼበታለሁ። አንድ በሽመና ሙያ የሚተዳደሩ ሰው የመስሪያ ቁሶችንና አገልግሎታቸው ምን እንደሆነ እንዲነግሩኝ ጠይቂያቸው የሰጡኝ ምላሽ ከሌላው መረጃ አቀባይ የተለየ ነበር። እንዲህ ሲሆን ሌላ ሰው ቃለ መጠይቅ አድርጌ፤ እንዲሁም በተተኳሪ የቡድን ውይይት ጊዜ ትክክለኛውን ምላሽ ለማግኘት ችያለሁ።

### 1.6.2 ምልከታ

ምልከታ ሌላው መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ "The term "observation", as used in this context, is not limited only to visual aspects of the situation, but also involves full range of sensual experience including hearing, feeling, smiling and testing, when ever these may be appropriate." Kenneth (1964:77)

በምልከታው ወቅት ተሳታፊ በመሆን እና ታዛቢ መስየ መረጃ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ዝሃ ሲያዘጉ ዝሃ በኮሻይሌ ይገፎ የመዘርጋት ስራ ከሙያተኞቹ ጋር ሰርቻለሁ፡፡ የተመለከትኩትን መረጃ በተሻለ መጠን ምልከታውን በከወንኩ በአጭር ጊዜያት ውስጥ በወረቀት ላይ አስፍሬያለሁ፡፡ በነገሩ ላይ ቁዘማ በማድረግ ስለጉዳዩ በቂና የተሟላ መረጃ ለመሰብሰብ ሞክሬያለሁ፡፡ ይህንን ማድረግ ጠቃሚ እንደሆነ ፈቃደ (1991፣ 91-96) ይመክራሉ፡፡ የመረጃውን ሙሉነት ከፍ ለማድረግም ተከታታይ ምልከታ ተደርጓል፡፡ በምልከታው በተሻለ መጠን ተፈጥሯዊ መቼትን ተጠቅሜያለሁ፡፡ ቢሆንም የጠፉ ቁሶች ምንነት፣ አሰራራቸውን እና አገልግሎታቸውን ቀርሶ ለማስቀመጥ ይረዳ ዘንድ ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼትን ተገልግያለሁ፡፡

### 1.6.3 ተተኳሪ የቡድን ውይይት

በቃለ መጠይቅና በምልከታ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ተደጋጋሚ ቃለ መጠይቅና ምልከታ ከማድረግ በተጨማሪ ተተኳሪ የቡድን ውይይት መጠቀም ጥሩ አማራጭ በመሆኑ ይህን ዘዴ ለመተግበር የተቻለኝን ሁሉ አከናውኛለሁ፡ ፤ በተለይ ሸማኔዎችና እንጥረኞች ልክ እንደ ማንኛውም ሰው/ግለሰብ/ በእነሱ ላይ የሚነገሩ አሉታዊ ገጽታ ያላቸውን ጉዳዮች ለመናገር ፈቃደኛ ያለመሆን ችግር ተስተውሏል፡፡ ፈቃደኛ ቢሆኑ እንኳ ሙሉ በሙሉ መረጃውን ያለመናገር ችግር ገጥሟል፡፡ ዘዴው ይህን ችግር ፈትቷል፡፡ እንዴት? መረጃ አቀባዮቹን ከተለያዩ ሙያዎች፣ ማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ ተቋማት አምጥቶ አብረው እንዲወያዩ በማድረግ አንዱ ሌላው ያልገለጸውን መረጃ እያወጡ ስለተናገሩ ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ተችሏል፡፡ በተለይ አሉታዊ ገጽታ ያላቸውን ጉዳዮች ያለመናገር ችግር ተፈጥሮ የነበረ ሲሆን ይህ ዘዴ መረጃ አቀባዮችን ፊት ለፊት ያፋጠጠ ስለሆነ "ውሸታም ላለመባል

ይመስላል" በፊት የደበቁትን ሃሳብ ለመናገር ችለዋል። በተለይ አሉታዊ ገጽታ ያላቸው ስንቃሎችንና ሕይወታቸውን የሚመለከቱ መረጃ ለማግኘት ዘዴው እጅጉን ጠቅሟል።

በዚህ ዘዴ ሸማኔዎች ለብቻ፣ እንጥረኞችም ለብቻ፣ ከሁለቱ ሙያ ውጭ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ለብቻ በተለያየ ቡድንና ቀን እንዲሁም የመወያያ ርዕስ ውይይት አድርገዋል፤ የተስማሙበትን ሃሳብ ሰንዝረዋል። ከተጠኚዎቹ ውጭ የጽሕፈት ቤት ሰራተኞችን፣ የእድሜ ባለጸጎችን በሌላ ወገን አድርጎ በማወያየት መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል። በዚህ ዘዴ የመረጃውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የተጠቀምኩበት ሲሆን፤ ከዚህ ዘዴ በተጨማሪ ተደጋጋሚ ምልከታና ቃለ መጠይቅ በመጠቀም የመረጃውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ችያለሁ ብየ አምናለሁ።

በዚህ ዘዴ መረጃ አቀባዮችን የመረጥኩት ፈቃደኝነታቸውን ከገለጹልኝ በኋላ በዕድሜ ገፋ ያሉትን መርጫለሁ ምክንያቱም አንደኛ በልምድ ብዙ ያውቃሉ፤ ሁለተኛ የድሮና የዛሬውን በማነጻጸር ይነግሩኛል ብየ በማሰብ ነው። በመቀጠል ዛሬ ላይ ወጣቶችና አዛውንቱ ስለሙያው ያላቸውን አመለካከት ለመረዳት ወጣት ሙያተኞችንም መርጫለሁ። ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የጽ/ቤት ሰራተኞች በመምረጥ ውይይት አካሂደዋል።

ውይይት የተካሄደባቸው ስፍራዎች መካነ ብርሃንና ደረስጌ የተባሉ ቀበሌዎች ሲሆኑ በደረስጌ እንጥረኞችን፣ መካነ ብርሃን የሸማ ሙያተኞችንና ሙያተኛ ያልሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን አወያይቻለሁ። ጥር 27፣ 2003 በቁጥር ዘጠኝ የሚሆኑ ሸማኔዎችን ለሶስት ሰዓት ያህል ያወያየሁ ሲሆን የመወያያ ነጥቦቹ የሸማቃ የመስሪያ ዕቃ ምንነትና የሚሰሩት ቁሶች ስም፣ አሰራርና የሙያተኞቹን ሕይወት በሚመለከት ነበር። የተነሱት ጥያቄዎች በቃለ መጠይቅ ወቅት የማይስማሙ መረጃዎች የተገኙበት ነጥቦች ላይ እንጂ የቁስ ምንነትና አሰራሩን ሙሉ በሙሉ በተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃውን ሰብስቢያለሁ ማለቴ እንዳልሆነ ልብ ይሏል። ሙያተኞቹ ከተወያዩ በኋላ የተስማሙበትን ሃሳብ ገልጸዋል። በምዕራፍ አራት የቀረበው የቁስ ስያሜ፣ አሰራርና የሙያተኞች ሕይወት ውስጥ ከፊሉ በዚህ ዘዴ የተገኘ መረጃ ነው።

የካቲት 6፣ 2003 ደግሞ በቁጥር አምስት የሆኑ አንጥረኞች ለሶስት ሰዓት ያህል ደረስጌ ቀበሌ ስለ ሕይወታቸው፣ ስለ ቁስ አሰራራቸው ለማወያየት ጥረት ተደርጓል። ስለ ቁስ አሰራራቸው (ወርቅና ብር) አንዱ ለሌላው ለመንገር ፈቃደኛ ሳይሆኑ ስለቀረ በዚህ ጉዳይ የተደረገው ውይይት ፍሬያማ አልሆነም። ምክንያቱም አንዱ የአንዱን አሰራር ቀስሞ ተጠቃሚ እንዳይሆን ስለፈለጉ ነው። ቢሆንም ሙያተኞቹ ስለ ሕይወታቸው ተናግረዋል በተለይ "ቡዳ" ሆኑም አልሆኑም "ቡዳ" እንደሚባሉ ተስማምተዋል። ትንታኔው በምዕራፍ አራትና አምስት ቀርቧል።

የካቲት 11፣ 2003 ደግሞ አራት የአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ለሁለት ሰዓት ያህል ስለአንጥረኞችና ስለ ሸማኔዎች ሕይወት፣ ስለሚነገሩ ቃል ግጥሞች ይዘት እንዲወያዩ አድርጌያለሁ። ማጠቃለያቸውም ሙያተኞቹ የህብረተሰቡ ቀኝ እጅ (ልብስ፣ ጌጥና እንጀራ) እንደሆኑና የሚመለስላቸው ምላሽ ግን በጎ ገጽታ እንደሌለው ገልጸዋል።

ጥር 8፣ 2003 ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው አራት የጽ/ቤት ሰራተኞች ጋር ለአንድ ሰዓት ውይይት ተደርጓል። ባለሙያዎቹ የተመረጡት ከጥናቱ ግራ የሚያገናኛቸው ጉዳይ ስላለ ነው። መረጃ አቀባዮችን መምረጥ፣ ቢሮዎቻቸው ለሙያተኞቹ እያደረገ ያለውን ርዳታ በሚመለከት አወያይቻለሁ። ውጤቱም የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ መረጃ አቀባዮችን ጠቁመውኛል። እንዲሁም ጥቃቅን ንግድ ኢንዱስትሪ በብድርም ቢሆን ለሙያተኞቹ የሸማ እቃ አቅርበውላቸው፣ አክሽን ኤይድ ድርጅት የገንዘብ ርዳታ አድርጓል። የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ደግሞ የሙያተኞቹን ስራ በቪዲዮ በመቅረጽ ስፊ ፕሮግራም በመስራት ስራቸውን ለህብረተሰቡ የማስተዋወቅ ስራ ሰርቷል።

በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት የሚሰበሰበው መረጃ እንደ አስፈላጊነቱ ታይቶ በቴፕ ሪከርደር (በካሴት)፣ በፎቶ ካሜራ እና በቪዲዮ ካሜራ ተቀርጿል። አስራ ሰባት ካሴት፣ 205 ፎቶ ግራፍ እና ቪዲዮ። እንዲህ የተሰበሰበው መረጃ በተግባራዊ/Functionional (የFleming እና Schlereth በምዕራፍ 2 የቀረበውን)፣ ትእምርታዊ/Symbolic እና ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ተተንትኗል።

## 1.7 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት አምስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ ቀርቧል። ምዕራፍ አንድ በመግቢያ አቢይ ርዕስ ስር የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ አላማዎች፣ ጠቀሜታዎች፣ የጥናቱ ዘዴ፣ ወሰን፣ የመስክ ተሞክሮ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው እና የጥናቱ አደረጃጀት የሚሉት ቀርበዋል። ምዕራፍ ሁለት ከጥናቱ አካባቢና ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጥናቶች እንዲሁም የንድፈ ሃሳብ ቅኝት ተደርጓል። ምዕራፍ ሶስት የጥናቱን አካባቢ/መልክዓ ምድራዊ/፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራን የሚመለከት መረጃ የሚቀርብበት ነው። በምዕራፍ አራት የእንጥረኝነት ሙያ፣ የአሰራር ሂደት፣ የጥበብ ውጤቶቻቸው እና የገበያ ሁኔታ እንዲሁም ስለሙያተኞችና ስራዎቻቸው ሕይወት ተዳስሰውበታል። በመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦች የቀረቡበት ሲሆን ዋቢ መጻሕፍትና አባሪዎችም ከዋናው ጽሑፍ ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

## 1.8 የመስክ ቆይታ

ርዕስ ከጸደቀበት ቀን ጀምሬ ወደ መስክ ከመሄዴ በፊት ስለአካባቢው መረጃ ለማግኘት ይረዳኝ ዘንድ ቀድሜ በስልክ ሙከራ አድርጌያለሁ። መረጃ አቀባይ አገኝ ዘንድ በአቶ ካሳ ልጆመልካም አማካኝነት የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ የሆኑት አቶ የኑስ ሁሴንን በስልክ አግኝቼ ማን ስለ ሽመና፣ ማን ስለእንጥረኝነት፣ ማን ስለ ወረዳው ባህልና ታሪክ ያውቃል በሚሉት ነጥቦች ላይ ተወያይተናል። ለጥናት የመረጥኩት አካባቢ ቀደም ብየ አውቀው ስለነበር መረጃ አቀባዮችን ለመምረጥና ለማግኘት ብዙም አልተቸገርኩም፣ መረጃ የማግኘቱ ነገር ግን ፈታኝ ነበር። በመስክ ከጥር 6 እስከ የካቲት 28፣ 2003 ቆይቻለሁ።

ጥናት በማደርግበት አካባቢ ከደረስኩ በኋላ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ያጻፍኩትን የትብብር ደብዳቤ በማሳየት መረጃ አቀባይ የሚሆኑኝን ሰዎች ስም ዝርዝር አግኝቻለሁ። ስራ የጀመርኩት ዝርዝሩን ይዤ ስለአካባቢው ባህልና ታሪክ ከሚያውቁ ሰዎች ጋር በአጠቃላይ ወግ ነው። ምክንያት አንደኛ ስለ ወረዳው የአየር ጠባይ፣ መልክዓምድራዊ፣ ሃይማኖታዊ ሁኔታና የህዝብ ብዛትና መተዳደሪያ የሚሉት ይዘቶች የጥናቱ አንድ ምዕራፍ በመሆን ነው። ሁለተኛው ባህልና ታሪክ አዋቂዎች በዕድሜ ገፋ ያሉ ስለሆኑና

አካባቢውን በደንብ ስለሚያውቁት በምን ጉዳይ ማንን ማነጋገር እንዳለብኝ እንዲጠቁሙኝ በማሰብ ነው።

በሌላ መንገድ ደግሞ እኔ በግሌ ከማውቃቸው ሴቶች፣ የመንግስት ሰራተኞችና ሌሎችን ማን በምን ዙሪያ ያውቃል በማለት የመረጃ አቀባይ የስም ዝርዝር ሰጥተውኛል። በመቀጠል ከሶስቱም የተሰጡኝን ስም ማን ሶስት ጊዜ፣ ማን ሁለት ጊዜ፣ ማን አንድ ጊዜ ተጠቆመ እያልኩ ተመለከትኩ። የተጠቆሙትም በብዛት ተመሳሳይ ሰዎች ሆነው አገኘሁ። ቀጥየ እኔ ባወጣሁት መስፈርት መለኪያ ማለትም መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆንን፣ ስለ ጉዳዩ ሃሳብን የመግለጽ አቅምና የመናገር ችሎታንና በጥቂቱ በሙያው የቆዩበትን ዘመን አካትቻለሁ። ምክንያቱም በሙያው ለረጅም ጊዜያት የቆዩት የልምድ፣ የዕውቀትና የጥበብ ባለቤት ስለሆኑ በደንብ ይረዱኛል ብየ ስላመንኩኝ ነው።

ቀጥየ የጥናት አካባቢ መረጣ አደረግሁ። የመረጣው ዋና መለኪያ ብዙ ሙያተኞች የሚገኙበትን ቦታ ነው። ከላይ ከተገለጹት ሶስት አካላት ጋር በተደረገ ውይይት ብዛት ያላቸው የእንጥረኝነት ሙያተኞች ደረስጌ ቀበሌ ድልድሊትና ደረስጌ አካባቢ እንደሚገኙ፣ የሸማ ሙያተኞች ደግሞ መካነ ብርሃን ቀበሌ እንደሚገኙ ስለታወቀ የጥናቱን ትኩረት በነዚህ ሁለት ቀበሌዎች ላይ አደረግሁ። በሁለት ቀበሌ እየተዘዋወርኩ ለጥናቱ ይበጃሉ ያልኳቸውን መረጃዎች በካሴት፣ በፎቶና በማስታወሻ በመመዝገብ በትጋትና ጊዜ ተገልግየበታለሁ።

መረጃ የሰበሰብኩት ሙሉ በሙሉ መረጃ አቀባዮች በሚኖሩበትና በሚሰሩበት አካባቢ ሲሆን ቁሱ እየተሰራ መጠየቅና መቅረስ ያለብኝን መረጃ ቁሱ እየተሰራ በተደረገ ቃለ መጠይቅ በፎቶና ቪዲዮ መረጃ ሰብስቤያለሁ። አውድ የግድ የማይፈልጉ መረጃዎች የተሰበሰቡት ሙያተኞቹ ስራ በማይሰሩበት ቀን ነው። ይህኛው አማራጭ ሙያተኛው በነጻነት ሃሳቡን እንዲገልጽ ስለሚረዳው ሰፊና ብዙ መረጃ ለማግኘት አስችሏል። በተለይ የሙያተኞቹን ሕይወት የሚመለከት ጉዳይን ለመዳሰስ ቀን በካሴት የተቀረጹ ቃለ መጠይቆችን ቶሎ ቶሎ ወደ ጽሑፍ ቀይሬ አሻሚ ነጥቦችን እንደገና በማስታዎሻ ይገኘ በመጠየቅ መረጃውን ሙሉ ለማድረግ የተቻለኝን ሁሉ አድርጌያለሁ።

እስከ የካቲት 28፤ 2003 ድረስ መረጃዎችን ከሰበሰብኩ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ፎቶ ግራፎችንና ቪዲዮውን ወደ ሲዲ አስገልብጫለሁ፡፡ የመጀመሪያ ረቂቅ ከጨረስኩና ለአማካሪየ ከሰጠሁ በኋላ አልተሟሉም ያልኳቸውን መረጃዎች(በተለይ የቁሶችን ትዕምርታዊነት) ለማሟላት ከሚያዝያ አስራ አምስት እስከ ግንቦት አራት ቀን 2003 ድረስ ለሁለተኛ ጊዜ መስክ በመውጣት ቀሪ መረጃዎችን አሟልቼ ተመልሻለሁ፡፡

## 1.9 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

ከመረጃ ቋት/ኢንተርኔት የሚገኙ መረጃዎች "በኮኔክሽን" ችግር ምክንያት እየተቋረጠ መረጃዎች ሳይሰበሰቡ ጊዜ የመፍጀት ችግር፤ ከቤተ መጻሕፍት በካታሎግ ቁጥራቸው አለመገኘትና ቁጥራቸው የተገኙትም በቦታቸው ያለመገኘት ችግር ተስተውሏል፡፡ እንዲያውም አመት ሙሉ ሳይመለሱ የሚቆዩበት አጋጣሚ አለ፤ ለአብነት ያህል የEdith Mayo ቴክስት American Material Cultute የጠሚለው፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት ኮኔክሽን ሲኖር ከኢንተርኔት በሚገኝ መረጃ ችግሩ ተፈትቷል፡፡ ከቤተ መጻሕፍት የሚገኙ መጻሕፍትን ለመተካት ከኢተርኔት( ሙሉ በሙሉ hjstor) መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በተጨማሪም በመስክ ቆይታየ ለገጠሙኝ የተለያዩ ችግሮች የተቻለኝን ሁሉ ጥረት በማድረግ ለመፍታት ችያለሁ፡፡ ከገጠሙኝ ችግሮች መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹና ሊጠቀሱ የሚገባቸው ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡

ከችግሮቹ ውስጥ አንዱ መረጃ አቀባዮች ቀጠሮ ይዘው በመስጋታቸው በቀጠሮ ሰዓት ያለመገኘት ችግር ነበር፡፡ በተደጋጋሚ ጊዜ በመመላለስ አላማየን በማስረዳት መረጃ ሰብስቢያለሁ፡፡ የጥናቱን ዓላማ በመጠራጠርና አሉታዊ ገጽታ በመስጠት በቀጠሮ ጊዜ ያልተገኙትን የሚያውቋቸውንና የሚያከብሯቸውን ሰዎች ሽምግልና በመላክ ዓላማየ እነሱ ባሰቡት ገጽታ እንዳልሆነ አስረድቻው፤ የማን ልጅ እንደሆንኩም ነግረው ሙያተኞቹ ፈቃደኛ እንዲሆኑ በማድረግ መረጃ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜም በቀጠሮው ሰዓት ይጠብቁኝና ሰዓቱ ስደርስ ጥሪ አለኝ ብለው ወደ ጥሪው ስፍራ ወስደው (በወቅቱ ባለገዘኩና የአዲስ መላኩ የጥር ማርያም ያስተርዮ ዝክር ነበር) ትንሽ መጠጥ ከቀማመሱ በኋላ አሁን መጀመር እንችላለን ሲሉኝ ያለመቅረጸ ድምጽ ሁለት ጥያቄ ብቻ ጠይቄ አቋርጫለሁ፡፡ ምክንያቱም አንደኛ እየው እኔን የሚያጠና ሰው ከአዲስ አበባ ድረስ መጣ ብለው ራሳቸውን ከፍክፍ ስላደረጉ፤ ሁለተኛ መጠጥ እየጠጡ ያውም ዝክር

ቦታ የሚሰጡኝ መረጃ ምን ያህል ታማኝነት ሊኖረው ይችላል ብየ ከራሴ ጋር መክሬ ቃለ መጠይቁን አቋርጫለሁ። በሌላ ጊዜ በስከነ መንፈስ ተደርጓል።

ሴፍቲኔት ርዳታ ከሌለው በሚል መረጃ ለመስጠት ያላቸው ተነሳሽነት መቀነስ ሌላው የገጠመኝ ችግር ነው። ጥናቱ ያለውን ጥቅም በማስረዳት አብዛኛዎቹ መረጃ እንዲሰጡኝ አድርጊያለሁ። ርዳታ ከሌለው ብለው አሻፈረኝ ያሉትን በሌላ መረጃ አቀባይ ተክቻለሁ፡ እኔ መስክ በሄድኩበት ጊዜ ለአስር ተከታታይ ቀናት በወረዳው የነዋሪዎች "ኮንፈረንስ" ስለነበር ስብሰባ በመሄዳቸው ሄደው ያለመገኘት ችግር አንዱ ነበር። ይህ ሁኔታ በተፈጠረበት ጊዜ እንደ መፍትሄ የወሰድኩት አማራጭ 1ኛ አውድ በማይፈልጉ ነጥቦች ዙሪያ ከስብሰባ በኋላ ጥቂት ጥቂት መረጃ እየሰበሰብኩ መቆየትና ስብሰባው ሲያልቅ ከነአውዱ መሰብሰብ ነበር። ሌላው መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆኑ በኋላ በቃለ መጠይቁ ወቅት ግን መረጃ የመቆጠብ ችግር ተመልክቻለሁ። ምክንያቱም አንደኛ መተዳደሪያቸው ስለሆነ ለሌላ ሰው ሰጥቶ ሙያችን ቢሰጥብንስ፤ ሁለተኛ ስለ ማህበራዊ ሕይወታችን(በተለይ አንጥረኞች) ይጠይቁናል በሚል ምላሻቸውን ይቆጥቡት ነበር። ርምጃ የማግባባት ስራ በመስራት(ዓላማየን ማስረዳት) የተወሰኑት ሙያተኞች ፈቃደኛ ሆነው መረጃ እንዲሰጡኝ አድርጊያለሁ። አንዳንዶች ግን በፍጹም ፈቃደኛ ሳይሆን ስለቀሩ መረጃ ማግኘት አልቻልኩም። በተለይ ከአቶ አለሙ ቸኮልና ቤተሰቡ መረጃ ለማግኘት የተደረገው ጥረት አልተሳካም።

አንዳንድ መረጃ አቀባዮች ፈቃደኛ እንዲሆኑ በአማላጅ ተጠይቀው ፈቃደኛ ከሆኑ በኋላ መረጃ ይቆጥቡ ነበር። በዚህ ጊዜ ሁለት የመፍትሄ ሃሳቦችን አቅርቤያለሁ። አንደኛ ተነሳሽነታቸው እንዲጨምር የሌላ መረጃ አቀባይ ስም በመጥራት ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ እንዲህ አሉኝ በማለት ስነግራቸው ከእሱማ እኔ እበልጣለሁ ወይም አላንስም በሚል የማውጣጣት ስራ በመስራት መረጃ አግኝቻለሁ። የማውጣጣቱ ስራ ለፎክሎር ጥናት አጋዥ እንደሆነ MacDonald ይመክራሉ። ሁለተኛኛ በተደጋጋሚ ከመረጃ አቀባዮች ጋር ስገናኝ የመቀራረቡ አጋጣሚ ስለሚፈጠር በዚህም ተጠቃሚ ሆኛለሁ። እንዲሁም በተለይ ከሙያተኞች ሕይወት ጋር በተያያዘ  አሉታዊ ስለሆነው የሕይወት ገጽታ በተተኳሪ ቡድን ውይይት ጊዜ መረጃውን ለማግኘት ችያለሁ። ከዚህ በተጨማሪ የገጠመኝ ችግር  ነቀፌታ ያዘሉ ቃል ግጥሞችን ለመናገር አለመፍቀድ ሲሆን ችግሩን

ለመፍታት እንጥረኞችን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች ለመሰብሰብ እንጥረኞች ያልሆኑት እንዲነግሩኝ ከነዚህ ውስጥ ባህልና ታሪክ አዋቂዎችና የአካባቢው ቃል ገጣሚዎች ዋናዎቹ ናቸው። ስለ ሽመና ከሙያው ውጭ ያሉ ሰዎች በመጠየቅ ቃል ግጥም ሰብስቤያለሁ።

# 2. ክለሳ ድርሳናት

ይህ ምዕራፍ ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የታተሙና ያልታተሙ ጽሑፎችና የንድፈ ሃሳብ መነሻዎች የሚቃኙበት ነው።

## 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የታተሙና ያልታተሙ ጥናቶች ተደርገዋል። በዚህ ክፍል ጥናቶቹ በምን በምን ጉዳዮች ላይ ተሰሩ፣ ምን ምን ሃሳቦችን አነሱና መቼ ተሰሩ የሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ አግኝተዋል። በመቼት ተመሳሳይነት ያለው ጥናት ግን አልተገኘም። ጃናሞራ ወረዳ ላይ የተደረጉ በተለይ□ባህልና ስነጽሑፍ ላይ የሚያተኩሩ ጥናቶች ለማግኘት አልቻልኩም። በአካባቢው በሽመናና በእንጥረኝነት ሙያ ላይ የተደረገ ጥናትም አልተገኘም። በርዕስ ተቀራራቢነት ከታተሙት ውስጥ የDexter Burely(1978), Sophie Desta(1963), Michael Gerver(1988) እና Richard Pankhurst(1992) ሥራዎች ተጠቃሽ ናቸው። Pankhurst ሽመናና እንጥረኝነትን የተመለከቱ ሲሆን ሌሎቹ ሽመና ላይ ያተኩሩ ናቸው። ካልታተሙት ውስጥ የዋልተንጉስ መኮንን እና የሄለን አላምረው የሁለተኛ ዲግሪ ጥናቶች በዋናነት ተጠቃሽ[2] ናቸው።

D. Burley (1978) "The Despised Weavers of Addis Ababa" በሚል ባቀረቡት ጥናት ደገኛ የጋሞ ህብረተሰብን መሰረት በማድረግ ሽሮ ሜዳ መቼ እንደ ተቆረቆረች? ጋሞዎቹ ወደ ሽሮ ሜዳ መቼና እንዴት እንደመጡ? ወደ ሽመና ሙያ እንዴት እንደገቡ? ሙያውን ከማን ተማሩት? ሽሮ ሜዳ ለምን የሸማኔ መንደር ተባለ? ለሚሉት ጥያቄዎች ጥናታቸው መልስ ሰጥቷል። የጥያቄዎቹ መልስ በአብዛኛው ከፖለቲካ፣ ከማህበራዊ ደረጃና ተጽእና፣ ከኢኮኖሚ እና ከባህል ጋር የተያያዙ ናቸው። ይህ ጥናት ሽመናን በዋናነት ማንሳቱ ስለሸማኔዎች ማህበራዊ ሕይወት መዳሰሱ ከእኔ ጥናት ጋር

[1] ያሬድ ተፈራ(2002)፣ የኔአለም አረዶ(2000) እና ሰዒድ ይማም(2002) አለባሳትና ጌጣጌጥ ላይ፤ መኮንን ባይህ(2002) ማቅ ላይ፤ አቢዩ አስማማው(2000) የቤት ውስጥ መገልገያና ማጌጫ ላይ ጥናት ማድረጋቸውን አውቃለሁ። ቢሆንም ከእኔ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ዝምድና ስሌላቸው በጥናቱ በዝርዝር አላነሳኋቸውም።

ይዛመዳል፡፡ ጥናቶቹ በመቼት እና በአላማ የተለያዩ ናቸው፡፡ የእኔ ጥናት በቁሱና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲሁም የቁሱን አሰራር ሂደቶች የሚመለከት ሲሆን ይህ ጉዳይ የBurley የትኩረት አቅጣጫ አይደለም፡፡

Sophie Desta (1963) "Cottage Crafts" በሚል በጻፉት ጽሑፍ ጥጥ በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ እንደሚገኝ፣ የተለያዩ የጥጥ ዝርያዎች በሀገሪቱ እንደሚገኙ ይገልፃሉ፡፡ ቀሚስ፣ ኩታ፣ ነጠላ፣ ድርብ እና ጃኖ ከጥጥ እንደሚሰሩ ጠቁመው ኩታና ነጠላ በመስራት ኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም እንደምትለይ ጠቁመዋል፡፡ ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያዛምደው የሽመና ውጤቶችን በመዘርዘሩ ብቻ ነው፡፡ ጥናቶቹ በመቼት፣ በዓላማና በአጠናን ዘዴ ይለያያሉ፡፡

የMichael Gevers (1988) "Cotton and Cotton Weaving in Medieval Ethiopia" በሚል ባሳተሙት ጽሑፍ የጥጥ መገኛ አቢሲንያ ወይስ ኑቢያ የሚል የክርክር ሃሳብ ያነሳሉ፡፡ የሽማ አይነቶች የተለያዩ እንደሆኑ ጠቁመው፣ የአሰራር ሂደታቸውን ገልጸዋል፡ ፡ ሸማ፣ ኩታ፣ ቀሚስ እና መቀነት በሌላ ቋንቋም አቻ ትርጉም እንዳላቸው አክለው ጠቁመዋል፡፡ ከሽማ ስራ የሚገኙ ቁሶችን በመግለጻቸው ከእኔ ጥናት ጋር የሚገናኙ ቢሆንም ጥናቶቹ በአላማና በአጠናን ዘዴ የተለያዩ ናቸው፡፡

"History of Ethiopian Hand Crafts and Hand Craft Workers" በሚል Pankhurst(1992) ጥናት አድርገዋል፡፡ የጥናታቸው ዓላማ በኢትዮጵያ በተለይ በሰሜኑ ክፍል የሚገኙ የእደጥበብ ሙያተኞች ጥንተ አመጣጥ፣ ሙያና የሙያተኞቹን ማህበራዊ ሕይወት ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ ከአክሱም ዘመን ጀምሮ እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ያሉትን ጊዜያት አካትቷል፡፡ ሙያተኞቹም ከተራ ሰራተኝነት እስከ ቤተመንግስት ሙያተኝነት ደረጃ እንደሰሩ ገልጸዋል፡፡ ማህበራዊ ሕይወታቸውን በተጽዕኖ ይገፉ እንደነበር አውስተዋል፡፡ በተለይ "ቡዳ" እየተባሉ ጥሩ ያልሆነ ስም ሲሰጣቸው እንደነበር ጠቁመዋል፡፡ Pankhurst ሲያጠኑ መሰረት ያደረጉት ካልዓይ መረጃን ሲሆን የእኔ ጥናት መሰረት ያደረገው ቀዳማይ መረጃን ነው፡፡ እሳቸው ትኩረት ያደረጉት የሙያተኞቹን ክዋኔ መጤነት እና ማህበራዊ ሕይወት ሲሆን የእኔ ደግሞ ከPankhurst

ነጥቦች በተጨማሪ የቁሶቹን ምንነት፣ አሰራርና አገልግሎት እንዲሁም ሙያና ሙያተኞች ጭምር ነው።

ሌላው ካልታተሙ ጥናቶች ውስጥ "የሽመናና የጥልፍ ትውፊት በአክሱም" ዋልተንጉስ መኮንን (2000) የ2ኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ሲሆን በምዕራፍ አራት ስለሽመና ጥሬ ዕቃ አዘገጃጀት፣ የመስሪያ ዕቃዎችና ውጤቶችን ማቅረቡ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። በዓላማ የተለያየን ነን የዋልተንጉስ ጥናት ዓላማ የሽመናና የጥልፍ ትውፊት እና ገጽታዎችን ማሳየት ሲሆን የእኔ ጥናት አላማ ደግሞ አሁን ያለውን የሙያተኞችን ሙያና ሕይወት ማሳየትና መቅረስ ነው። ዋልተንጉስ የመስሪያ ቁሶችን ምንነት፣ አሰራርና ተግባር በሰፊው አብራርቷል። ከምርቶቹ ውስጥ ኩታ፣ ነጠላ፣ ቀሚስ እና ሌሎች ቁሶች አሰራርና አገልግሎቱን ገልጿል።

"ባህላዊ ሽመናና የቆዳ ሥራ በደንበጫና አካባቢዋ" በሚል ሔለን አሳምረው (1999) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርጋለች። ከእኔ ጥናት ጋር በብዙው ይዛመዳል። የሔለን ጥናት አላማ በደንበጫና አካባቢዋ የሚገኙ የሽመናና ቆዳ ሥራ ባለሙያዎች በስራቸው የሚጠቀሙባቸውን የአሰራር ሂደቶች ላይ ነው። እንዲሁም የባለሙያዎቹን ማህበራዊ ሕይወትና ስለ እነሱ የሚነገሩ ስነቃሎችን ይዘት ማመልከት ደግሞ ሌላው የጥናቷ አላማ እንደሆነ ገልጻለች። ሔለን ስለ መስሪያ ቁስ ስያሜ ፣ ቁስ አሰራርና አገልግሎት ሰፊ ትንታኔ አቅርባለች። እንዲሁም በሙያተኞቹ ሕይወት ዙሪያ የተነገሩ ስነቃሎችን ሰብስባ ተንትናለች።

## 2.2 የንድፈ ሃሳብ ቅኝት

ይህ ክፍል ስለቁሳዊ ባህል ምንነት በስሩ ስለሚጠኑ ዘርፎች፣ ስለመጠናታቸው አስፈላጊነትና ስለአጠናን ዘዴያቸው የተጻፉ ጽንሰ ሃሳቦች በማቅረብ ከጽንሰ ሃሳቦቹ ትይዩ ይህ ጥናት በሚመለከታቸው ጉዳዮች ዙሪያ የተቃኘ ነው።

### 2.2.1 የቁሳዊ ባህል ምንነት

ቁሳዊ ባህል በፎክሎር ስር እንደሚካተት የተለያዩ የመስኩ ምሁራን ገልጸዋል። ከነዚህ መሃከል ፈቃደ (1991፡ 15) ፣ Dorson (1972፡ 2) ፣ Wilson (1986፡ 229) እና Martha (2005፡ 12) ይጠቀሳሉ።

የቁሳዊ ባህልን ምንነት በተመለከተ የመስኩ ምሁራን የተለያዩ ክርክር የሚያስነሱ ሃሳቦችን ሰንዝረዋል፡፡ የተወሰኑት ቁሳዊ ባህል (material culture) ማለት ተጨባጭ ነገሮችን እጅ ስራን፣ ቅርጻ ቅርጹን፣ ምግብ፣ ልብስ፣ ወንበር፣ ወዘተ. የሚመለከት ሲሆን በደምሳሳው የቁስ ስብስብ እንደሆነ የሚገልጹ ናቸው፡፡

ሌሎቹ ደግሞ ቁሳዊ ባህል ከቁሱ ስብስብ የሰፋ ሰፊ ዘርፍ አለው ባይ ናቸው፡፡ ይህም በቁሱ ላይ ያለን የህብረተሰብ አመለካከት፣ እምነትና እሴት የያዘ ነው ይላሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ Glassie (1966:41 - 66)፣ Schlereth (1983: 334) ፣ prown (ውስተ ኢንተርኔት:1) እና Michael O. Jones (1972:47- 48) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከምሁራኑ ውስጥ ለማሳያነት ያህል የPrownን ሃሳብ ላቅርብ "Material culture is the study through artifacts of the beliefs, values, ideas, attitudes and assumptions of a particular community or society at a given time." Prown (1982:1) እኔ ከሁለቱ ወገኖች ሁለተኛውን እከተላለሁ፡፡ ምክንያቱም እንደኛ ቁሳዊ ባህል ሲባል ስሙ እንደሚናገረው ቁስ እና ባህልን በአንድ አስተሳስሮ የሚይዝ እንጂ የቁስ ስብስብ ብቻ አይደለም፡፡ ምክንያቱም "Culture is pattern in mind, in word, in visible, and shifting." ነውና Glassie(1999: 41)፡፡

እዚህ ላይ ቁስ ተጨምሮ ሲዋሃድ ነው ቁሳዊ ባህል የሚሆነው፤ አለበለዚያ ስያሜው ቁሳዊ ባህል ሳይሆን ቁሱ ብቻ መባል ነበረበት ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚያስኬድ አይመስለኝም፤ ምክንያቱም ቁሱን ነጥለን እናጥና ብንል የቁስ ዝርዝር ብቻ ይሆናል፡፡ ምሳሌ ማረሻን ማረሻ ብሎ መግለጽ ማለት ነው፡፡ አሰራሩንና ተግባሩን እንመርምር ከተባለ ግን የግድ በቁሱና በሰሪው መካከል ያለን ግንኙነት ይመለከታል፡፡ ማረሻ ለገበሬውና ለሰሪው ህይወት ሲሆን ለሌላው ደግሞ ቁስ ነው፡፡ ምክንያቱም ባህል ሲሆን የህብረተሰቡን እምነት፣ አመለካከትና ትዕምርት መጨመር አለበት፡፡ ቁሶቹ በምን፣ እንዴትና በማንና ለማን እንደሚሰሩ፤ መቼ፣ ለምንና እንዴት አገልግሎት ላይ እንደሚውሉ ጥናት ሲደረግ ከቁሱ ሰፋ ባለ መልኩ የሰሪውና የህብረተሰቡ አመለካከት በቁሱ ላይ ያሳደረውን ገጽታ መመልከት ይቻላል፡፡ ሁለተኛው አንድን ቁስ በሰራ ህብረተሰብ ውስጥ የግድ የሰሪው አሻራ (የህብረተሰቡ አመለካከት፣ ዕምነት፣ ፍላጎት)

ያርፍበታል። ስለዚህ የግድ በቁሱና በሰሪው(በሰዉ) መካከል ግንኙነት አለ ማለት ነው። ይህ ደግሞ ቁሳዊ ባህል የቁስ ስብስብ ብቻ አለመሆኑን ያረጋግጣል።

Glassie ቁሳዊ ባህል ሶስት የተለያዩ ክፍሎች እንዳሉት፤ እነርሱም ፈጠራ፣ ግንኙነትና ፍጆታ እንደሆኑ ጠቁመዋል። ፈጠራ ሲባል ዲዛይን፣ የቁሱ አሰራር፣ የቁሱ አመጣጠን እና ቀለም ምርጫውን ይመለከታል። ለመዳውም እውድን የግድ የሚል ሲሆን ሲሰራ መመልከት፣ ቀጥሎ የተመለከቱትን ከሚሰጣቸው መመሪያ ጋር በማጣመር ሙያውን ይለምዳሉ። መመሪያው በጽሑፍ ወይም በቃል የአሰራሩን ቅደም ተከተል በማጥናት እንደሚለምዱ ገልጸዋል። በዚህ ጥናት ሁለቱንም ለመታዘብ ችያለሁ። ግንኙነት ሰሪና ተጠቃሚውን የሚያገናኝ ነው። ፍጆታ የተጠቃሚው ግንኙነት ከሰሪው ፍላጎት ጋር የሚስማማበት ነው። ስለዚህ የፈጠራ እውድ ስለሰሪዎች፣ የፍጆታ እውድ ስለተጠቃሚዎች ያስተምራል፤ የግንኙነት እውድ ሁለቱን ያጣምራል። ቁሳዊ ባህል ከቁስ የሰፋ ጉዳዮችን እንደሚዳስስ ልብ ይሏል።

በቁሳዊ ባህል ስር ይካተታሉ ከተባሉት ውስጥ ሀገረሰባዊ እጅስራ/folk crafts/፣ ሃገረሰባዊ ልብስ/folk costume/፣ ሃገረሰባዊ ምህንድስና/folk architecture/፣ ሃገረሰባዊ የምግብ አሰራር/ folk Cookery/ እና ሃገረሰባዊ ስዕል/folk art/ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ ፈቃደ (1991፡15)፤ Dorson (1964:10) ገልጸዋል። Leymans (2002) ደግሞ artifact፣ craft and trade፣ folk craft እና cultural land scape ብለው ከፍለውታል።

እኔ የመጀመሪያዎቹን እደግፋለሁ፤ እከተላለሁ። ምክንያቱም የእነሱ አከፋፈል ሰፋፊና ራሳቸውን የሚችሉ ዘርፎችን ስለለዩ፤ Layman's ግን ሰፋፊና ጠባቡን ስለቀላቀሉት ለምደባ አሻሚ ነው። ለምሳሌ artifact የቁሳዊ ባህል እቻ እንጂ በቁሳዊ ባህል ስር ከሚጠኑት ንኡስ ክፍል መመደብ የሚገባው አይመስለኝም። ሌላው Folk arts እና craft and trade በተለያየ ምድብ መሆን የሌለባቸውን Layman's በአንድ ላይ አድርገዋቸዋል። Folk arts ሲባል ምንነቱ፣ አሰራሩ፣ ተግባሩ፣ የገበያው ሁኔታ አብሮ መጠናቱ አይቀርም ብዩ አምናለሁ።

ቁሳዊ ባህል ሲጠና ቁሱ፣ በቁሱ ማህበረሰቡ፣ የባለቁሱ ታሪክ ሊጠና እንደሚችል የመስኩ ምሁራን ይመክራሉ። ". . . material culture is overview the . . . biograghy of an oriental rug crafts man, the biography of several potters, . . ." በቁሳዊ ባህል ስር መጠናት እንደሚገባቸው Glassie ይናገራሉ። Glassie (ውስተ ኢንተርኔት፡84)።

ሃገረሰባዊ ዕጅ ስራን በተመለከተ Roberts (1972: 233 - 252) የሚከተለውን ሃሳብ ሰንዝረዋል። የቁሱ አሰራርና ጌጥ የሚተላለፈው ከአንድ ቤተሰብ ወደ ሌላው ቤተሰብ ለረጅም ጊዜ በተስተላልፎ አባት ልጁን በማስተማር ሙያተኛ እንዲሆን ይረዳዋል። ትልልቆቹ ለትንሾቹ ክህሎትና ዕውቀታቸውን በልማድ፣ በስልጠና፣ በታተሙ መመሪያዎችና መጻሕፍት አማካኝነት ይሰጣሉ። ባህል ብዙ ጊዜ መልክዓ ምድራዊና ታሪካዊ ስርጭት አለው። የፎክሎር ዘርፎችም በተለያየ ቦታ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው ወይም ከአንድ የአለም ጫፍ ወደ ሌላው ይተላለፋሉ። አሰሪዎች የመስሪያ ቁሱን ያቀርባሉ። ምክንያቱም ጥሬ ዕቃውን በአብዛኛው በአካባቢያቸው ስለሚያገኙት፤ እንዲሁም መግዣ ዋጋው ርካሽ በመሆኑ እንደሆነ Robert's ገልጸዋል።

## 2.2.2 የቁሳዊ ባህል ጥናት አስፈላጊነት

የቁሳዊ ባህል ጥናት አስፈላጊነትን በሚመለከት አንድና ሁለት የለውም። አስፈላጊነቱ ጥያቄ የሚያስነሳ ስላልሆነ መጠናት ይገባዋል። ምክንያቱም ዞሮ ዞሮ ጉዳዮችን ሰው ስለሆነ በቁሱ አማካኝነት የሰዎችን አመለካከትና እምነት ለመረዳት ያግዛል። በዚህ ርዕስ ስር የቁሳዊ ባህል መጠናት አስፈላጊነትን ከዚህ ጥናት መደረግ አስፈላጊነት ጋር በማዛመድ ንድፈ ሃሳባዊ (theories) ቅኝቶች የሚቀርቡበት ይሆናል። እንዲሁም የቁሳዊ ባህል ጥናት አተናተን ዘዴ የሚዳሰስበት ነው።

የሰው ልጅ በምድር መኖር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ቁስን በመስራት ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቱን ለመሙላት ራሱን ከጊዜው ጋር እያስማማ ኖሯል፤ እየኖረም ነው። ኡደቱም ይቀጥላል። ይህንን ሃሳብ Schlereth ሲገልጹ "material culture is not only the most ancient of time shapes, it is also a tangible form of a past time persisting in present time." በማለት ነው Schlereth (24)።

"ቁሳዊ ባህል ሲጠና እቃውን ራሱን ማጥናት አንድ ዋና ተግባር ሲሆን አሰራሩን ማጥናት ደግሞ ሌላው ነው።" ፈቃደ (1991፡15) ለምን? ሙያውን ለማሳየት በሙያው ሙያተኞቹ ይጠናሉ። እንዲሁም በዕቃው ላይ ያሉ ጌጦችን ትዕምርት ለመተንተን። ቁሳዊ ባህልን ማጥናት ማለት ሰውን ማጥናት እንደሆነ የተለያዩ የመስኩ ምሁራን ገልጸዋል። ከነዚህ ውስጥ Glassie (1991፡41-66) ፣ Roberts (1972፡ 233 - 252) ፣ Schlereth ውስተ ኢንተርኔት (110) ፣ Fleming (1972፡156 – 161) ቁሳዊ ባህል በፊትም ዛሬም ያለ ቢሆንም ትኩረት ሲገባው ትኩረት ተነፍጎት እንደቆየና ትኩረት እንደሚሻ የተለያዩ የመስኩ ምሁራን ይገልፃሉ። ከነዚህ መሃከል Roberts ተጠቃሽ ናቸው።

> the importance of field work and recording in the area of traditional material culture can not be too highly stressed, several generations of folklorist have warned that folkloristic item are disappearing with out leaving a true behind. This warning is more applicable today than ever before, especially in connection with material culture. More and more traditional artifact and techniques are out moded by accelerating technical change. Roberts (1972:431)

ከጥቅሱ ቁሳዊ ባህል ትኩረት ተሰጥቶት መጠናት እንደሚገባው አለበለዚያ ባህሉ የመጥፋት ወይም የመበረዝ አደጋ ሊገጥመው እንደሚችል እገነዘባለሁ። ይህ ጥናትም በሽመናና በእንጥረኛነት ላይ የማተኩሩ ምክንያት አንደኛው ሙያውን ለማሳየትና ቀርሶ ለማስቀመጥ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የመፍትሄ ሃሳብ ለመስጠት ነው።

Schlereth ውስተ ኢንተርኔት (7 - 8) ቁሳዊ ባህል ሲጠና የቁሳዊ ባህል ባለሙያ /አጥኚ/ በስራው ሊያጤነው የሚገባ ዘጠኝ ነጥቦችን አንስተዋል። እነርሱም፡- ጥበብ አመልካችነት፣ ተምሳሌታዊነት፣ ባህላዊነት፣ አካባቢያዊነት፣ አገልግሎታዊነት፣ መዋቅራዊነት፣ ባሕርይ አመልካችነት፣ ማህበረሰባዊነት እና ማህበረሰብ ታሪካዊነት

ናቸው። Schlereth እክለውም በቁሳዊ ባህል ጥናት ጊዜ የአስተሳሰብ መንገድ ብልጫውን ይወስዳል በማለት ገልጸውታል። ይህ ጥናት ከሞላ ጎደል እነዚህን ዘጠኝ ነጥቦች መሰረት በማድረግ ስለ ርዕሰ ጉዳዩ መረጃ ለመሰብሰብና ለመተንተን ጥረት አድርጓል።

Leone ደግሞ ቁሳዊ ባህል የቁሶችን ማህበራዊ አውድን ትርጉም የሚገልጹ ሲሆን በዚህ ስራ የእጅ ባለሙያዎችን የሕይወት ታሪክ፣ የሸማኔዎችን የሕይወት ታሪክ፣ ዘመናዊ ቤቶችን እና ቤቶቹን የሚያንጹትንና ነዋሪዎችን ጭምር ያጠቃልላል ይላሉ። Leone (ውስተ ኢንተርኔት ፡ 84) ይህ ጥናት ከ Leone የሙያተኞቹን የሕይወት ታሪክ የሚለውን ቢመለከትም ሙሉ በሙሉ የሕይወት ታሪካቸውን ሳይሆን ከተጠኚዎቹ ሙያ እና ሙያተኝነት ጋር በቀጥታ እሚገናኙት ላይ ብቻ ያተኩራል።

በአጠቃላይ የቁሳዊ ባህል ጥናት ለሁሉም ህብረተሰብ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ቁሳዊ ባህሉ ከማህበረሰቡ ህልውና ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነው። ቁሱን ከማህበረሰቡ፣ ማህበረሰቡን ከቁሱ ነጥሎ ማጥናት ስለማይቻል። ይህን በተመለከተ Fleming እንዲህ ይላል "every culture, however, primitive or advanced, is absolutely depend on its artifacts for its survival and self-realization "(Fleming፡ 153)

የእኔ ጥናት በቁሳዊ ባህል( ሽመናና እንጥረኝነት) የማድረጉ አስፈላጊነት የሙያተኞቹ የመስሪያ ቁስ፣ የሚያበጁት ቁስ ስለራሳቸው የሚጠቁመውን አትጣጫ ለማሳየት፤ የሚሰሩት/የሚበጁት ቁሶች ራሳቸው ስለህብረተሰቡ የሚናገሩትን ለመለየት ማለትም የሚወጡትን ትዕምርታዊነት ለማብራራት ነው። እንዲሁም በህብረተሰቡና በሙያተኞቹ መካከል ያሉ ክፍተቶች ጠበብ ይሉ ዘንድ የመፍትሄ ሃሳብ ለመሰንዘር ነው።

### 2.2.3 የቁሳዊ ባህል አተናተን ሂደቶች

ቁሳዊ ባህል በተለያየ መንገድ ሊተነተን ይችላል። በዚህ ክፍል ቁሳዊ ባህል የሚተነተኑባቸውን የተለያዩ የመተንተኛ ዘዴዎችና ሂደቶች ከመስኩ ምሁራን ምደባ ጋር በማዋሃድ ይቀርባል። በዋናነት Prown (1982) እና Fleming (1972) የቁሳዊ

ባህል መተንተኛ ያሉት ዘዴ ይቀርባል። በቅድሚያ ግን የቁሳዊ ባህል መመደቢያ መስፈርቶችን እጠቅሳለሁ።

በቁሳዊ ባህል ጥናት ስር ሊጠኑ የሚችሉ ቁሶችን በምድብ በምድብ ማስቀመጡ በቀላሉ ሊወጡት የሚቻል ተግባር አይደለም። እንዲያውም ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚሻ አስቸጋሪ ስራ ጭምር ነው። ይህ አስቸጋሪነቱን Prown (1982 ፡ 2) ከሁለት ምክንያቶች አኳያ እንደሆነ ይናገራሉ። አንደኛው ምክንያት የቁሶቹ ዓይነትና ቁጥር ብዙ ሆኖ መገኘት ሲሆን፣ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የሚያስማማ አንድ ወጥ መስፈርት አለመገኘት ነው። በመስኩ ምሁራን የተለያዩ መስፈርቶች የተገለጹ ሲሆን በአብዛኛው ያስማሙት መስፈርቶች ቅርጽ፣ አገልግሎት፣ መስሪያ ንጥረ ነገር፣ ዘመንና ስልት ናቸው። ይህ ጥናት እነዚህን መስፈርቶች ይቀበላል። ምክንያቱም ሌሎች ያልተጠቀሱ መስፈርቶች ብዙም የማያስኬዱና አሻሚ ስለሆኑ ነው።

### 2.2.3.1 የቁሳዊ ባህል አተናተን ከ Prown ጽንሰሃሳቦች አንጻር

በዚህ ስር Prown (1982) ቁሳዊ ባህልን ለመተንተን ይበጃሉ ብለው የጠቆሟቸው ቲዎሪ ቀርቧል። Prown ቁሳዊ ባህልን ለመተንተን ሶስት ደረጃዎች እንዳሉ ይገልጻሉ። እነርሱም ገለፃ/description/፣ ትርጓሜ/deduction እና ማመላከት/speculation ናቸው። ቀጥለን ሶስቱን የመተንተኛ ደረጃዎች እንመለከታለን።

#### 2.2.3.1.1 ገለፃ /description

ቁሱን ራሱን በመመዝገብ ዋና መረጃ ማድረግ ነው። ይህ ዘዴ በሚታየው ቁስ ምልከታ ላይ ትኩረት ያደርጋል። ቁሱ በአብዛኛው አንድ አይሆንምና ብዙ ምልከታ ይፈልጋል። ቁሱ የተመረተበት ጊዜ፣ ቁሱ የሚገኝበት የአየር ጠባይ እና የቁሱን አገልግሎት መመልከት ይቻላል። ገለፃ ሶስት ንኡስ ይዘቶች አሉት።

የመጀመሪያው substantial analysis የሚባለው ሲሆን የቁሱ ዝርዝር የሚገለጽበት ነው። የቁሱ ወርድና ስፋት፣ የቁሱ ቁጥር የሚነገርበት ነው። ከቁሱ ገለፃ ቀጥሎ የሚመጣው ምንድን ነው፣ አገልግሎት እንዴት ይሰጣል፣ የቁሱ ክፍፍልስ እንዴት ይዳረሳል የሚለውን ይመለከታል። ሁለተኛው ዘዴ አውድ/context/ የሚባለው ነው።

በዚህ ጊዜ የአጥኚው ትኩረት ርዕሰ ጉዳይ/subject matter/ ላይ ይሆናል። ይህ ብዙ ጊዜ የሚከሰተው በጥበብ ወይም በሌሎች ጌጥ በሚፈልጉ ስራዎች ላይ ነው። አውድ የተቀረጹ ጽሑፎችን/inscription/፣ የብረት ጌጥን/embossed on metal/፣ የእንጨት ወይም የድንጋይ ስዕልን፣ የጨርቅ ሽመናን /weaver in textile /፣ የማስጌጫ ዲዛይኖችን ወይም ማባያወችን /motifs/ እና ወ.ዘ.ተ ይመለከታል። ሶስተኛ formal analysis ሲሆን የቁሶቹን ቅርፅ የሚተነትን ነው። ይህ ዘዴ በሶስት መልኩ ቁሱን ይተነትናል።

## 2.2.3.1.2 ትርጓሜ/Deduction

የዚህ ዘዴ መገለጫ በቁሱና በተቀባዩ (በሰዉ) መካከል ያለውን ግንኙነት ትርጓሜ ማውጣት ነው። አጥኚው ከቁሱ ከራሱ መረጃ ከማግኘት በተጨማሪ ራሱን ወደ ምርመራ የሚያስገባበት ነው። ይህ ዘዴ የቁሱን ውስብስብነትና የአጥኚውን የበፊት ወይም የቀደመ እውቀትና ልምድ መሰረት የሚያደርግ ነው።

## 2.2.3.1.3 ማመሳከት/Speculation

በበፊቶቹ ሁለት ደረጃዎች በገለፃ ቁሱ ራሱን ከማየት፣ በትርጓሜ ደግሞ በቁሱና በተቀባዩ/ በሰዉ መሃከል ያለን ግንኙነት ወደ ማየት የተሸጋገረ ሲሆን በማመሳከት ደረጃ የሚታየው ደግሞ ወደ ተቀባዩ አእምሮ /the mind of the perceiver/ የሚሸጋገረውን ነው። የተንታኙን የተፈጥሮ እውቀት /common sense/ እና ውሳኔ /Judgment/ ያካትታል። በዚህ ሂደት ከገለፃ እና ትርጓሜ የሚገኙ መረጃዎችን ጨምሮ በመቃኘት አሳድጎ መላምት የሚሰራበት ነው። እንዲሁም ከመላምት በተጨማሪ ተመራማሪዎች ቁሱን ለመመርመር የሚያነሱትን ጥያቄና የሚያነሱትን "ፕሮግራም" የሚመለከት ነው። ይህ ለውጥ ደግሞ ትንተናው ከራስ/ ከውስጣዊ ወደ ውጫዊ መረጃ ተሸጋገረ ማለት ነው። ከራስ ያለን መረጃ መሰረት በማድረግ ወደ ውጭ ተመልከቶ የራስ/የግል ምርመራ የሚደረግበት ነው። ምርመራው ቁስ ራሱ፣ በቁስና በተቀባዩ መካከል ያለን ግንኙነት የሚያካትት ነው። እንዲሁም የተንታኙን የግል የመመርመር ችሎታና ውሳኔን ጭምር የሚያጠቃልል ነው።

### 2.2.3.2 የቁሳዊ ባህል አጠናንና አተናተን ከ Fleming ቲዎሪ አንጻር

በዚህ ንዑስ ርዕስ Fleming ቁሳዊ ባህል ሲጠና የትኩረት አቅጣጫዎቹ ምን ምን እንደሚሆኑ እና ቁሳዊ ባህል ሲተነተን መተንተኛ ዘዴዎቹ ምን ምን እንደሆኑ የቀረበበት ነው። Fleming ቁሳዊ ባህል በ5 መልኩ ሲጠና እንደሚችል ይገልጻሉ። ይህም የቁሱ ታሪክ /history/፣ ቁሱ ራሱ /material/፣ የአሰራር ሂደት /construction/፣ ጉጉ/design/ እና አገልግሎት/function/ ናቸው። Schlereth ቁጥሩን ዘጠኝ እንዳደረሱት ልብ ይሏል። Fleming እነዚህን አምስት ነገሮች በአራት ዘዴዎች ሲተነትኑ እንደሚችሉ ጠቁመዋል። እነርሱም መለየት/identification፣ ግምገማ/evaluation፣ ባህላዊ ትንታኔ/cultural analysis እና ትርጓሜ /interpretation ናቸው።

#### 2.2.3.2.1 መለየት /identification

በዚህ ስር ገለፃ /description፣ ምደባ /classification እና ትክክለኛነት (authentication) በንኡስነት የሚካተቱ ናቸው።

ምደባ /classification/ የመጀመሪያው የመለየት ደረጃ ነው። ብዙ የአሁን የምደባ ስልት ስርዓታዊ አይደለም። ብዙው ምደባ መሰረት የሚያደርገው በቁሱ አገልግሎት፣ አንዳንዶቹ በቁሱ ላይ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በአሰራር ሂደቱ ነው። ሁለተኛው የመለየት ደረጃ ትክክለኛነት /authentication/ ነው። ይህ ሂደት የቁሱን ትክክለኛ መሆን ይመለከታል። ይህም አጠቃላይ ትርጉሙ ምንድን ነው የሚለውን በቀን፣ የመገኛ ቦታውን፣ የመጻሕፍት መገኛውን /authorship/ ፣ የቁሱን የአሰራር ሂደት ይመለከታል፡ ፡

ሶስተኛው የመለየት ደረጃ ገለፃ ሲሆን ብዙ ጊዜ የሚጀምረው የቁሶቹን ወርድና ስፋት እንዲሁም ክብደት በመለየት ነው። ገለፃ በPrown በንኡስ ክፍልነት ሳይሆን በዋና መተንተኛ ዘዴ እንደቀረበ ልብ ይሏል።

አራተኛው የመለየት ደረጃ extended identification ሲሆን ትኩረቱ ስለ ሙያተኞች /makers/፣ ስለእቃ ገዥዎች /purchaser/፣ ስለየቁሱ ባለቤት የሕይወት ታሪክ በስፋት ፈልጎ ማግኘት ነው። ይህ ሲባል የመጡበት አካባቢ ባህላዊ መልክዓምድር ጥንተ

አመጣጥ፣ የቁሶቹ ባህርያትና ምንጭ፣ የሰሪዎችን የአሰራር ሂደት/ግንባታ/ እና የጌጦቹን መስሪያ ቴክኒክ ምንጭ እና ጥንተ አመጣጥ፣ የአገልግሎቱን ታሪክ ቅርጽ /the history of functional form/፣ ወይም the meaning of the iconography ላይ ነው። የመለየት ዋና ዓላማ ስለ እምስቱ የቁሳዊ ባህል ባህርያት ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ነው። እነሱም፡- ቁሱ፣ የቁሱ ታሪክ፣ የአሰራር ሂደት፣ አገልግሎት እና ጌጥ ናቸው።

## 2.2.3.2.2 ግምገማ /Evaluation

ግምገማ በሁለት መልኩ የሚታይ ሲሆን የመጀመሪያው ግምገማ ኪነ-ውበታዊ ጉዳያቸው ላቅ ያሉትንና በስራው ላይ የሚያተኩር ነው። ይህም በቁሱ አስፈላጊነት፣ የሙያተኛው ሙከራ ክህሎት፣ በሁሉም ጌጥ ስኬታማነት ማለትም የቅርጽ /form/፣ የስልት እና የጌጥ ገላጭነትን ወይም ገላጭ መሆንን ይመለከታል።

ሁለተኛው የግምገማ ዓይነት ደግሞ ተመሳሳይ ቁሶችን ማነጻጸርን (በቅርፅ፣ በዋጋ፣ በአዲስነት) ይመለከታል። የግምገማው ንጽጽር በአንድ ሙያተኛ የተሰሩ ቁሶችን አንዱን ከሌላው መለየት፣ በአንድ ባህል ውስጥ ያለና በተለያዩ ሙያተኞች የተሰሩ ተመሳሳይ ቁሶችን መገምገምን ይመለከታል። እንዲሁም በተለያየ ቦታ የሚገኙ ተመሳሳይ ቁሶችን መገምገም ይቻላል።

## 2.2.3.2.3 ባህላዊ ትንታኔ /Cultural Analysis

ባህላዊ ትንታኔ ሁለት ቅርጾች አሉት። አንደኛው የቁሱ ተግባራዊነት በራሱ ባህል መሆኑን የሚያሳይ ነው። ተግባራዊነት በቁሱ ምንነት፣ አሰራር /ግንባታ፣ ጌጥ፣ አገልግሎትና ትዕምርት እማኝነት የቁሱን ተግባር እንደ መገናኛ ድልድይ በመቁጠር ህብረተሰቡን ከሃሳቡ፣ ከእሴቱ፣ ከስሜቱ፣ ከምንነቱ እና ከአካባቢው ጋር ያገናኛል።

ሁለተኛው የባህላዊ ትንታኔ ቅርጽ የግንባታ ቴክኒኮችን እና የጌጦቹን ባህርያት በቅደም ተከተል ይመለከታል። ቅደም ተከተሉ የጌጦቹን ባህርያት ትኩረት በማድረግ በአንድ አካባቢ የተገኙ ጌጦችን ቀጥሎ ያን ጌጥ በሌላ ቦታ መፈለግ ነው።

በቁሳዊ ባህል ጥናት ባህላዊ ትንታኔ ከገለፃ ባሻገር በሰው እና በሰሩት ቁስ ላይ ግንኙነት መኖሩን ማብራርያ ይሰጣል፡፡ Cultural Analysis is concerned with the relation of the artifact to its culture በማለት (Fleming፣161) ይገልጻሉ፡፡

### 2.2.3.2.4 ትርጓሜ/ Interpretation

"Interpretation is concerned with relation of the artifact to our culture" Fleming (ውስተ ኢንተርኔት፡ 162) ብለው ገልጸውታል፡፡ ትርጓሜ ትኩረት የሚያደርገው ስለ ቁሱ ያወቅነውን ሃቅ እና በባህል ባለቤቶቹ ባለው ቁልፍ ሚናና እሴት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡ ትርጓሜ እንደ ግለሰቡ፣ እንደ ርዕዮተዓለም፣ እንደ መደቡ፣ እንደ ታዳሚው አተያይ አንዱ ከሌላው የሚለያይበት አንጻር የተለያየ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የትርጓሜ ጥናት ጠቃሚና ጥሩ ሆኖ ቢሰራ እንኳ ምልዑ አይደለም፡፡

# 3. የጃናሞራ አካባቢያዊና ማህበረ ባህላዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ የተጠኚው አካባቢ ዳራዊ መግለጫና የነዋሪው ህብረተሰብ የኢኮኖሚ መሰረት ይቀርባሉ።

## 3.1 የተጠኚ አካባቢ

የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው አካባቢ በአማራ ክልል ስር ከሚገኙት ዞኖች መካከል የሰሜን ጎንደር ዞን አንዱ ነው። ዞኑ በሃያ ሶስት ወረዳዎች የተዋቀረ ሲሆን ከእነዚህ ወረዳዎች ውስጥ ጃናሞራ ወረዳ አንዱ ነው። የዚህ ጥናት ትኩረትም በዚህ ወረዳ ላይ ሲሆን ወረዳው በሰሜን ከአዲአርቃይ ወረዳ፣ በደቡብ ከበለሳ፣ በምስራቅ ከበየዳ፣ በምዕራብ ከወገራ ወረዳ ይዋሰናል። የቆዳ ስፋቱ 1949.5 ካሬ ኪሎ ሜትር ሲሆን የህዝቡ ብዛት 197,751 ይሆናል። የህብረተሰቡ ኑሮ በእርሻና በንግድ ላይ የተመሰረተ ነው። የአየር ንብረቱ 26.47 በመቶ ደጋ፣ 41.17 በመቶ ወይና ደጋ እና 32.35 በመቶ ቆላማ ነው። ወረዳው በሰላሳ ሶስት ቀበሌዎች የተከፋፈለ ሲሆን የወረዳው ከተማ መጠረያ መካነ ብርሃን ይባላል። (የወረዳው ኮሙኒኬሽን ጉዳይ ጽ/ቤት፣ 2003)

ጃናሞራ ወረዳ በ1888 የተመሰረተች ሲሆን የወረዳው ከተማ ደረስጌ ነበር። መካነ ብርሃን አሁን የወረዳዋ ከተማ ስትሆን የተመሰረተችው በ1945 ሲሆን የመሰረቷትም ደጃች አድማሱ ብሩ እና ፊታውራሪ ላቀው ደስታ ናቸው። ወረዳዋን ሲመሰርቱ በሰሜን ሉሪ ወንዝ፣ በደቡብ በኩል ደግሞ እስከ መና ወንዝ፣ በምስራቅ በኩል መሸሃ ወንዝና በምዕራብ በኩል ደግሞ እስከ በለገዝ ወንዝ ድረስ በማለት እንደከለሏት የአካባቢው ነዋሪዎች ይገልጻሉ። (የወረዳው ኮሙኒኬሽን ጉዳይ ጽ/ቤት፣ 2003)

## 3.2 የወረዳው ህብረተሰብ ዳራዊ መግለጫ

በዚህ ክፍል የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውን የጃናሞራ ወረዳን ህብረተሰብ ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶች ይዳሰሳሉ።

### 3.2.1 ባህላዊ የሰርግ ስርዓት

በወረዳው የሰርግ ስነስርዓት የሚፈፀመው በተፋቃሪዎቹ ፍላጎት ሳይሆን በወንድየውና በሴቷ ቤተሰቦች ፍላጎት ነው፡፡ ይህም የእንደኛው ቤተሰብ ከሌሎች ዝምድና እንዲኖራቸው ሲፈልጉ ልጁ/ልጇ ገና ህፃን እያለ ልጅህን ለልጄ ተባብለው ይስማማሉ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በተለይ የወንዱ ቤተሰቦች የልጃቸውን ለአቅመ አዳም መድረስ አይተው ከእነሱ ዘርና ደረጃ ጋር የሚስማማ ቤተሰብ ፈልገው ለልጃቸው ያሳጫሉ፡፡ ሙያተኞቹም በዚህ መንገድ ጋብቻ ይፈጽማሉ፡፡ የሽማ ሙያተኞች ከሙያው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሰዎችን ልጅ ወይም ሌላ ዘመድ ለጋብቻ በመጠየቅ ለድግስ ወጭ ሳያበዙ እንደ አቅማቸው ይሰርጋሉ፡፡

የመጀመሪያውን የጋብቻ ሥርአት ዓይነት ስንመለከት የወንዱ ቤተሰብ ወደ ሴቷ ወላጆች/ቤተሰቦች/ አማጭ ይልካሉ፡፡ አማጮቹም በጠዋት ወደ ልጅቱ ወላጆች በመሄድ "ልጃችሁን ለልጃችን" ብለው ይጠይቃሉ፡፡ በዚህ ጊዜ እሽታውን ሳያገኙ አማጮቹ ተቀመጡ ቢባሉ እንኳ እሽ አይሉም፡፡ የልጅቱ ቤተሰቦችም እሺ ግን ከቤተዘመዱ ጋር እንምከር ተመልሳችሁ ኑ ብለው መልስ ይሰጧቸዋል፡፡ አማጮቹም ወደ ወንዱ ቤተሰቦች በመሄድ የልጅቱን ቤተሰቦች አሳምነው እሺ እንዳስባሉ ለልጁ ወላጆች የደስታ ቃል ያበስራሉ፡፡ ከዚህ በኋላም በልጅቱ ክርስትና ቀን የልጁ ወላጆች በመገኘት በአገር ሽማግሌዎች አማካኝነት ቃል ይጋባሉ፤ ዝምድና ተፈጠረ ማለት ነው፡፡ሙያተኞቹ በዚህ ብዙ ተጠቃሚ አልሆኑም ሽማግሌ ሲልኩ እንኳ በሙያም በደረጃም ከሚቀራረቡት ውስጥ ስለሆነ የተለየ ድግስ፣ የተለየ መልስም አይጠብቁም፡፡

ሌላው የህብረተሰብ ክፍል ግን በየዓመቱ ከፍተኛ ወጭ በማውጣትና ድግስ በመደገስ የልጅቱ እድሜ ሰባት እስከ አስራ ሶስት ዓመት፣ የልጁ እድሜ ከአስራ ሁለት እስከ አስራ አምስት ዓመት እስከሚሞላቸው ድረስ እየተጠራሩ ይገባበዛሉ፡፡ የልጅቱ እድሜ አስር ዓመት፣ የልጁ እድሜ ደግሞ ከአስራ ሁለት እስከ አስራ አምስት ዓመት ሲሆን በአዲስ መልክ በደንብ ይደገስና ወዳጅ ዘመድ ተሰብስቦ፣ የአካባቢው ህዝብ ተጠርቶ የሙሽሪትና የሙሽራው ወላጆች በደማቅ ሁኔታ ይሰርጋሉ፡፡

በመጨረሻም የተጋቢዎቹ ቤተሰብ ለተጋቢዎቹ ማጫ ይጥሉና የሙሽራው ሚዜ ሙሽራዋን ይዘው ሲወጡ የሙሽራዋ ወገን እንዲህ እያሉ ሲያዜሙ "ውሰዳት እመቤትህ ናት" የወንድየው ወገን ደግሞ "እንዲያው ወሰድናት አላየናት" እያሉ መልስ ይሰጣሉ:: ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ለሙያተኞች የታጨች ልጅ እስከታድግ ድረስ ከወንድየው ቤተሰቦች ጋር ሁና ስራ በማገዝ ቤተሰቦቹና የምትረዳበት አጋጣሚ አለ:: አሁን ግን የወንዱም ሆነ የሴቷ ዕድሜ 18 ሳይሞላ ህጉ ስለሚከለክል እንደ በፊቱ ዓይነት ጋብቻ እየቀነሰ የመጣ ሲሆን አልፎ አልፎ ግን አንድም በቤተሰብ ተጽእኖ፤ አንድም ምታገባውን ላለማጣት አስራ ስምንት ዓመት ሳይሞላት ሞልቶኛል በማለት የሚጋቡ አሉ:: በመስክ ቆይታ ወቅት በወረዳው ፍትህ ጽ/ቤትና ጤና ጣቢያ የዕድሜ ምርመራ ለማድረግ የመጡ ተጋቢዎችን ለመመመልከት ችያለሁ::

ሃይማኖት

በወረዳው ከሚገኘው ህዝብ ውስጥ ዘጠና ስምንት በመቶው የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ ሲሆን ቀሪው ሁለት በመቶ ደግሞ የእስልምና እምነት ተከታይ ነው:: ክርስቲያኖቹ የሚተዳደሩት በግብርና ሲሆን ሙስሊሞቹ ደግሞ በንግድ ሥራ ይተዳደራሉ:: አሁን አሁን በተለይ ከ1983 ወዲህ ሙስሊሞች መሬት ስላገኙ ማረስ ጀምረዋል፤ ክርስቲያኑም መነገድና መሸመን ጀምሯል::

በወረዳው የሚገኙ ሙስሊሞች ሀገር አቀፍ ከሆነው የሙስሊም በዓላት ሌላ የሼህ አብደላ አባት ሼህ ሁሴን የሞቱበትን ቀን ለማስታዋስ መውሊድ በዓልን ያከብራሉ:: የኦርቶዶክስ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ደግሞ አገራዊ ከሆኑት የእምነትና የድል በዓላት ውጭ ሶስት በዓላትን በደመቀ ሁኔታ ያከብራሉ:: ታህሳስ ሃያ ዘጠኝ ቅድመ ላሊበላ ሰረባር ባለእግዚአብሔር ሰረባር ቀበሌ ላይ፤ ጥር ሃያ አንድ አስተርዮ ማርያም ደረስጌ ላይ እና የአባሆን ፃድቃን ገብርኤል ታህሳስ አስራ ዘጠኝ አባሃን ላይ ያከብራሉ::

አስተርዮ ማርያም ጥር ሃያ አንድ ቀን ሲከበር የሚከበርበት ቦታ ደረስጌ ማርያም ሲሆን ቤተክርስቲያኗ በ1682 ዓ.ም በአጼ አድያም ሰገድ እያሱ እንደተመሰረተች ይነገራል:: የቤተክርስቲያኗ ታሪካዊ መናገሻ ግን በ1818ዓ.ም ደጃች ውቤ ሀይሉ እንዳሰሩት ይነገራል:: በ1847 ዓ.ም አጼ ቴዎድሮስ ደጃች ውቤን ድል በማድረግ ደረስጌ ላይ

ንግስናውን እንደተቀበሉ ታሪክ ያስረዳል። በቤተክርስቲያኗ ከሌሎች ቀናት በተለየ መልኩ ጥር ሃያ አንድ ቀን በደመቀና ባማረ መልኩ አስተርዮ ይከበራል። ተወላጁ ብቻ ሳይሆን ሌላው ምእመን ከጎንደርና ከባህርዳር ተነስቶ ለበዓሉ ደረስጌ መጥቶ ያከብራል። ከበራው ከዋዜማው ጀምሮ የሃይማኖት አባቶች በዝማሬ፣ በቅዳሴና በቅኔ ፀሎት ያደርጋሉ፤ ምስጋና ያቀርባሉ።

የዕለቱ ለት ከፀሎት ሥርአቱ በተጨማሪ የጉብኝት ፕሮግራም አለ። ሁሉም በትኩረት ለማየት ከሚጓጉባቸው ቁሶች ውስጥ የወርቅ ከበሮ፣ የወርቅ መስቀል፣ የደጃች ውቤ አፅም፣ የብር ከበሮና መስቀል፣ የወርቅ የዘውድ ቆቦች፣ የወርቅ ካባዎች እና ከጎሽ ቀንድ የተሰሩ በጣም ትልልቅ ዋንጫዎች ይገኙበታል። በዋንጫዎቹም ይጠጣል። ምእመኑ በዚህ እለት ቤተክርስቲኗ ሀብታም እንደሆነች በማዕረግም በስምም ከአክሱም እኩል እንደሆነች ይናገራሉ። በእርግጥ አሁን የቤተክርስቲያኗ ጉልላትና ማጫዎቻዎች የወርቅ ናቸው። እነዚህ ቁሶች ሲበላሹ የሚሰሩት በአካባቢው አንጥረኞች እንደሆነ ልብ ይሏል።

## 4. የሽመና ቁሳዊ ባህል

በዚህ ምዕራፍ ሸማኔዎችና አንጥረኞች አንድን ቁስ ለመስራት የሚገለገሉበት ቁስ፣ ስለሚሰሩት ቁስ ምንነት፣ አገልግሎትና ዋጋ፣ በሙያተኞቹ ሕይወት ውስጥ የሚታዩ የመገለል ሁኔታ፣ ሃይማኖት በሙያው ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ፣ ሙያውን የሚለምዱበት ሂደትና በሕይወታቸውና በሙያው ውስጥ የተከሰቱ አሉታዊና አዎንታዊ ለውጦች ምን ምን ናቸው የሚሉትን አቢይ ጉዳዮች የሚብራሩበት ነው፡፡ ከላይ የተነሱትን ነጥቦች ስፈትሽ በምዕራፍ ሁለት የተነሱትን የFleming፣ Prown እና የSchlerethን ቲወሪዎችን ተገልግያለሁ፡፡

### 4.1 የሽመና መስሪያ ቁሶች ስምና አገልግሎት

የሽመና መስሪያ ሸማታ አይነቶች ሁለት ናቸው፡፡ ስለሸማታዎቹ ዓይነት አቶ አደም አማን የተባሉ የሽማ ሙያተኛ የሚከተለውን ብለዋል፡፡ "አንደኛው ዝርግ ሸማታ የሚባለው ነው፡፡ ዝርግ ሸማታ ረዥም ስለሆነ ዝሃው ረዘም ብሎ እንዲታጠፍ ስለሚያደርግ የተዘረጋው ዝሃ በደንብ ተፍታትቶ አንዴ በተቋጠረው ዝሃ ብዙ መስራት የሚያስችል ነው፡፡ ነገር ግን ሰፊ ቦታ ይይዛል፡፡"(ጥር 23፣ 2003፣ መካነ ብርሃን) ከታች የሚታየው ዝርግ የሚባለው የሸማታ ዓይነት ነው፡፡



ዝርግ ሸማታ

ስዕል ተ.ቁ 1

ሁለተኛው ተመላሽ (ቁልፍ) ሸማቃ የሚባለው ሲሆን በቅርብ ርቀት የሚታጠፍና ማጠፊያው ላይ ጋድም እንጨት ያለው ነው፡፡ ጥቅሙ ብዙ ቦታ ስለማይፈልግ በጠባብ ቦታ መትከል መቻሉ ሲሆን ነገር ግን በትንሽ ቦታ ስለታጠፈ ትንሽ ትንሽ በተሰራ ቁጥር ቶሎ ቶሎ ስለሚሞላ እንደገና ተፈትቶ እንዲጠብቅ ሲደረግ ብዙ ጊዜ ስለሚወስድ ሙያተኛው እንዲሰለች ያደርጋል፡፡ እንዲሁም አዲስ ቶሎ ቶሎ ለመቋጠር ጊዜ ይወስዳል፤ (ጥር 23፣ 2003፣ መካነ ብርሃን) በማለት በሸመና ሙያ የሚተዳደሩት አቶ አደም አማን ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡



ተመላሽ ሸማቃ

ስዕል ተ.ቁ 2

ከላይ የተጠቀሱት የሸማቃ አይነቶች ሙሉ ስራ እንዲሰራባቸው የተለያዩ መስሪያ ቁሶች ያስፈልጓቸዋል፡፡ አንዱ ከጎደለ ስራው ይስተጓጎላል፡፡ ለሸማቃ መስሪያ የሚያገለግሉ ቁሶች እንጨት፣ ሳር፣ ሸንበቆ፣ ሲባጎ ገመድና ሲር ሲሆኑ ከገመድና ሲር ውጭ የሚፈልጉትን ሌሎች ቁሶች ባየ[4] ወርደው የሚፈልጉትን እንጨት በማምጣት ጠርበውና ቆርጠው በሚፈልጉት ቅርጽ በማስናዳት ሸማቃ የሚያዘጋጁት የሸማ ሙያተኞቹ ራሳቸው ናቸው፡፡ መስራት የማይችሉት ከሚችሉት ይለምዳሉ፣ አልፎ አልፎ ገዝተው ይጠቀማሉ፡፡ ሙያተኞቹ ሰርተው ይጠቀማሉ ብቻ ሳይሆን ከአሁን ለህጻን ልጆቻቸው

[4] ባየ ከከተማ ወጣ ብሎ እንጨት በገፍ የሚገኝበት፣ በተለይ ክረምት ወቅት ለከብቶች መኖ የሚገኝበት ስፍራ ነው

ጭምር ሰርተው ሸማቃዎቹ የልጆቹን መድረስ ይጠባበቃሉ፡፡ ቀጥሎ የቁሶቹን ስምና አገልግሎት አንድ በአንድ እዘረዝራለሁ፡፡ የቁሱ ስም፣ አገልግሎትና ቁሱ የሚሰራበት ነገር Fleming ቁስና አገልግሎት፣ Prown ገለጻ እና Schlereth አገልግሎት እና አሰራር ሂደት ካሉት ቲዎሪዎች ጋር አብሮ የሚሄድ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

1. **ቀሰም፡-** ውስጡ ክፍት የሆነ ሳር ሲሆን በልክ በልክ ተቆርጦ ይሰራል፡፡ ለስራ የተዘጋጀው ጥጥ ወደ ፈትልነት ሲቀየር የፈትሉ ማጠንጠኛ የሚሆነው ነው፡፡ በአካባቢው አጠራር "ቃንጫ[5]" ይባላል፡፡ ጥቅሙ ፈትሉን አቅልሞ በማዳወሪያ ለመጠቀም አመቺ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

2. **ማቅለሚያ/ማዳወሪያ፡-** ከእንጨት ይሰራል፣ ይወፍራል እንጂ የእንዝርት አቻ ነው፡፡ ቀሰሙን ማዳወሪያ ላይ በማስገባት ሴቶች አቅልመው ቀለም የሚሰሩበት ነው፡፡ ያቀለሙትን ለሸማኔው ያቀርቡለትና ሙያተኛው ይሰራዋል፡፡
3. **መሌን፡-** የምርት መሰብሰቢያውን እንጨት ገትረው የሚይዙት እንጨቶች ናቸው፡፡ ግራና በቀኝ በኩል ከመሬት ይተከላሉ፡፡ መሌኑ የምርት መጠቅለያውን ይዞ ልብሱን ለመሰብሰብ እንዲሁም ዝሃው በደንብ በተወጠረ ሁኔታ ተይዞ ሳይረግብ እንዲሰራ ያገለግላል፡፡ ምርት መጠቅለያው ካልተወጠረ መወርወሪያው ራሱ ሊወረወር/ሊሰራ አይችልም፡፡ ስለዚህ ስራው እየተሰራ እንዲቀጥል ዝሃው መወጠር አለበት፣ እንዲወጠር የሚያደርጉት ደግሞ መሌኖቹ ናቸው፡፡ ከመጠቅለያ በምን ይለያል ቢባል መጠቅለያ ብቻውን ስራውን አይሰራም፡፡ ምክንያቱም ምርቱን ቢጠቀልልም ስራው እንዲቀጥል የተጠቀለለውን ወጥሮ የሚይዝለት ነገር ይፈልጋል፡፡ ይህን ከሚያደርጉለት ውስጥ አንዱ መሌኑ ነው፡፡ የሽመና ስራ ሲሰራ ዝሃው ካልተወጠረ ስራው ይተጓጎላል፡፡

[5] ቃንጫ ውስጡ ክፍት የሆነ ወፍራምና ስፊ ሳር ወይም በመኸር ወቅት እህል ሲታጨድ ከቀርም የሚዘጋጅ ነው፡፡

4. **መምቻ/ዳፋ፦**




ስዕል ተ.ቁ 4

ዳፋ በላይና በታች ወንፊቱን ገጥሞ የሚይዘው እንጨት ነው፡፡ ዳፋ በወንፊቱ ውስጥ የሚያልፉት ዝሃዎች በወንፊቱና በሚሂኑ በስርአት አልፈው በመወርወሪያ የሚሰራውን ቀለም በደንብ በመምታት ወደ ፊትና ወደ ኋላ ማድረጊያ ነው። መፋረኪያ ከዳፋው በስር በኩል የሚገኝ ሸንበቆ ነው፡፡ አገልግሎቱ የወንፊቱን መቃ ከአደጋ መከላከል ሲሆን ወንፊቱን ዝሃው እንዳይበላው መከላከያ ነው። የዳፋ ገመድ ሌላ በዳፋው ስር የሚገኝ ቁስ ሲሆን ገመዱን አልባ ዳፋው ረግቶ ሊቆም አይችልም፣ ሊቆም የሚችለው በገመዱ ርዳታ ነው። አገልግሎቱ ዳፋው ረግቶ እንዲቆም ማድረግ ነው፡፡

5. **መርገጫ፦** በገመድ የተንጠለጠሉ እንጨቶች ሲሆኑ ጥቅማቸው እንጨቶቹን በእግር ጣት ይዞ ከፍና ዝቅ ሲደረግ ሚሂኑም ከእግሩ ጋር ዝቅና ከፍ ስለሚል በእግር ከፍና ዝቅ እየተደረገ በመቀያየር ስራው እንዲቀጥል የሚያደርገው መርገጫ ነው። መርገጫዎቹ ከፍና ዝቅ ካላሉ መሌኑ ሊከፍት ስለማይችል ድርና ማጉ ተዋህዶ ልብስ ሊሰራ አይችልም፡፡ ከፍና ዝቅ የሚሉት መርገጫዎች በአንድ ላይ ሳይሆን አንዱን መርገጫ ከፍ ሲል መወርወሪያው ይሰደድና መምቻው ይመታል፣ እንደገና ከፍ ብሎ የነበረውን ዝቅ፣ ዝቅ ብሎ የነበረውን

ከፍ በማድረግ እንደገና መወርወሪያውን በመስደድ በመምቻ እየተመታ ይሰራል፡፡ ባለ2፣ ባለ 4 እና ባለ 8 መርገጫ አለ፡፡ ብዙ ጊዜ የተለመደው ባለ 2 እና ባለ 4 መርገጫ ነው፡፡ምክንያቱም እንደኛ ቀድሞ የመጣው ባለ ሁለት፣ ቀጥሎ ባለ አራት መሆኑ፤ ሁለተኛ ከባለ ስምንቱ ይልቅ ለመስራትም ሆነ ዋጋ እነዚህ ቀላልና ዋጋቸው ስለሚቀንሱ ነው፡፡

6. **ተሸካሚ፡-** እንጨት ሲሆን የሸማቃውን እቃዎች የሚሸከም ነው፡፡ በተለይ የሚሂንና የዳፋ ገመዶችን በመሸከም ያገለግላል፤ ተሸካሚው ከሌለ ገመዶቹ አይሬጉም፡፡

7. **መጠቅለያ፡-** እንጨት ሲሆን እየተሰራ ያለው ልብስ ማስቀመጫ ሲሆን እየተሰራ ይጠመጠምበታል፤ መጨረሻ ላይ ስራው ሲያልቅ ተቆርጦ ከመጠቅለያው ይለያያል፡፡ ስለዚህ አገልግሎቱ በመሰራት ላይ ያለን ምርት ማስቀመጫ ነው፤

8. **ሚሂን፡-**




ስዕል ተ.ቁ 5

ከእንጨትና ከሲር የሚሰራ ሲሆን ከላይና ከታችቀጭንእንጨትይዘረጋበታል፡፡ በላይኛውና በታችኛው እንጨት መካከል የሃ ሴንቲ ሜትር ክፍተት አለው፡፡

ክፍተቱ ግጥም ተደርጎ በሲር ከላይ ወደታች ይታሰራል። ወደ እንጨቱ የሚሄደውን ሲር ጠምጥሞ በመያዝ እንጨቱ እንዲረጋ የሚያደርገው የሚሂን ፈረስ ይባላል። ፈረሱ ካልያዘው ዘንጉ (እንጨቱ) ይወልቃል፤ በገመዱ ስለታሰረ ዘንጉ ይረጋል።

የሚሂን ፈረስ በሚሂኑ ውስጥ ገብቶ ዳርና ዳር መታሰሩ እንጨቱ ሃይል እንዲኖረው ያደርጋል። ሌላው የሚሂን ዘንግ (ጨንገር) ሲሆን ዳርና ዳር ሚሂኑን የሚይዙት እንጨቶች ናቸው። ዘንጎቹ ከሌሉ መሂኑ ሊሰራ አይችልም፤ ምክንያቱም ሊወጠር አይችልምና። አገልግሎቱ ዝሃዎቹ ተቆጥረው በወንፊቱ ያለፉት ዝሃዎች መስመራቸውን እንደጠበቁ ስራው እንዲሰራ ማድረጉና መርገጫዎቹ ከፍና ዝቅ ሲሉ መሌኑ አብሮ ስለሚንቀሳቀስ ማግና ድሩ እንዲዋሃድ ማድረግ የሚሉት ናቸው።

9. **ማጥበቂያ /መስቀኛ/ ማጠፊያ፡-** ዝሃው በሁለቱ ላይ ጋድም ሰርቶ ተመልሶ ወደ ማጥበቂያው ይሄዳል። ከሄደ በኋላ ወደ ማጥበቂያው ይተላለፍና ይጠብቃል። ማጥበቂያ/መስቀኛ እንጨት ሲሆን ከሸማኔው ቅርብ በሆነ ቦታ ፊት ለፊት ካለ እንጨት ላይ ሸማኔው ዝሃውን የሚያጠብቅበት ነው። ጥቅሙ ዝሃውን ጉትሮ መያዝ ሲሆን ማጥበቂያ አልባ ዝሃው ስለሚረግብ ልብስ አያስራም።

10. **ባላ/ ቋሚ፡-** ባላዎቹ ከእንጨት የሚሰሩ አራት ቋሚ ናቸው። አገልግሎታቸው የሸማ ዕቃውን ቁሶች መሸከም ሲሆን ከቋሚዎቹ ተጨማሪ ጋድም እንጨት አለ፤ እሱን የሚሸከመውም ባላው ነው።እንዲሁም ቋሚው እንዳይንቀሳቀስ ይረዳል።

11. **የፊት ግንድ፡-** ጥቅሙ ዝሃ ተዘርግቶ እየተፈታ በመስራት የተቋጠረ ዝሃ በደንብ ተቢታትኖ ለመስራት አመቺ እንዲሆን ማድረግ ነው። ምክንያቱም የፊት ግንድ ረዘም ብሉ ስለሚተከል ዝሃውን ለማስማማት ይረዳል።

12. **መዘራዘር፡-** በቁጥር ስምንት ረዘም ረዘም ያሉ ገመዶችን የሚሆን ሲሆን አገልግሎት ላይ የሚውለው ዝሃ ሲያልቅ በስምንቱ ገመድ ልክ ዝሃው ተዘርዝሮ በመዘረሪያው ታስሮ የመጨረሻው ዝሃ እስኪሰራ ድረስ የሚያገለግል ነው። አገልግሎቱ ለስምንቱ ቁጢት ማሰሪያ መሆን ነው። ከዚያ ተፈትቶ፣ ተቆርጦ ልብስ ይወጣዋል። ሌላው ማጥበቂያ የሚባል ገመድ አለ፤ ለመቋጠር መዘራዘሩ ብቻ ስለማይበቃ ማጥበቂያውን በመጨመር ለመዘራዘሩ መቀጠያ በማድረግ ዝሃው እስከ መጨረሻ እንዲሰራ ማጥበቂያው ተቀጥሎ ዝሃው እንዲሰራ ያደርጋል።

13. **ደንቆሮ፡-** መጨረሻ የሚመጣው ወደ ቁጢቱ የሚቀርበው ዝሃ ደንቆሮ ይባላል። በስራው መጨረሻ ላይ የሚመጣ ዝሃው ተዘግቶ የሚቋጠረው ነው። ደንቆሮ የተባለው የመጨረሻ ስራ ስለሆነና ሲሰራ የመጨረሻ ስለሆነ የሚታይ ዓይን ስለሌለው ነው። የስራ መጨረሻው ደንቆሮ ሲባል የመጀመሪያው ደግሞ ዓይን አንበሳ ይባላል። ዓይን አንበሳ ግልጽ ባይሆንም ሸማኔዎች በስልት የሚያዩት ዓይን አለው ይላሉ። ሙያተኞቹ በተለይ በኮሻይሌ ሲዘረጋ ጨረር ብሉ ሲሄድ የሚታይ ልክ እንደ ዓይን የሚታይ ነገር አለው ይላሉ። ስለሚታይ ነው ዓይን አንበሳ የተባለው። ስለዚህ መጀመሪያ ዓይን የሚወጣለት ዓይን አንበሳ ሲባል፤ በመጨረሻ በቋጠሮ የሚዘጋው ደንቆሮ ይባላል።

14. **መዘረሪያ፡-** ዝሃውን የሚመለከት ሲሆን መጀመሪያ ዝሃው ይነከራል፤ ከተነከረ በኋላ ይጠመቅና መታ መታ (ተራግፎ) ተደርጎ ይሰጣል፤ ከደረቀ በኋላ ይቋጠርና ለስራ ይዘጋጃል። የመዘረሪያ አገልግሎት ዝሃው ተሰጥቶ እንዲደርቅ ማድረግ ስለሆነ እንደ ማስጫነት የሚያገለግል ነው።

15. **ኮሻይሌ (ድርማገንሽ)፡-** ሁለት ወይም አራት የዝሃው ዓይን ይወጣና ይዘረጋል፤ ቀጥሎ ይዘጋና(ማዘጋት) ዓይኑ ተገኝቶ ሲሞላ ይነከራል፤ ከዚያ ይደርቅና ይቋጠራል። ኮሻይሌ አገልግሎቱ ማዘጊያ መሆን ነው።

16. **መለኪያ፡-** የሚባለው ገመድ ሲሆን የሚለካውም የሸማታ እቃዎችን ለመትከል ሲፈለግ የጉድጓዶች ርዝመትና ጥልቀት ይለኩበታል፤ እንዲሁም የተሰራው ልብስ ምን ያህል እንደሚረዝም የሚለካ ገመድ ሲሆን አንዳንዴ መለኪያው እንጨት የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። የገመዱ ርዝመት ከሙያተኛ

ሙያተኛ ይለያያል። አንዳንድ ሽማኔዎች ሁለት ሜትር ገመድ ይዘው፣ የተረፈውን ምልክት በማድረግ ሲለኩ ታይቷል። ሌሎቹ ደግሞ ስድስት ሜትር ገመድ ይዘው ይለካሉ። ከስድስት ሜትር የሚበልጥ ልብስ ከሰሩ የሚለኩት የተሰራውን ልብስ ከለኩ በኋላ ወደ ተለካው ደግመው በማጠፍ ሲሆን ልብሱ ከስድስት ሜትር ካነሰ ደግሞ ገመዱን አጥፈው የተሰራውን ልብስ ይለኩበታል።

17. **መገተሪያ**




ስዕል ተ.ቁ 6

መገተሪያ ግማሽ ጨረቃ ቅርጽ ያለው ቀጭን እንጨት ሲሆን አገልግሎቱ የተሰራው ልብስ እየተሰራ እያለ ያልተሰራው ሲሰራ የሚሰራው ልብስ እንዳይታጠፍ ወይም እንዳይጨማተር ወጥሮ የሚይዝና ልብሱ እንዳማገረበት እንዲዘልቅ የሚያደርግ ነው።

18. **ጨንገር፡-** የጥበብ ጌጥ ማውጫ ሸንበቆ ሲሆን ሙያተኛው ጨንገሮቹን በትክክል ቁጥሮ ሳይዛባ መስራት ይገባዋል፤ ከተዛባ ጥበቡ ስለማይመጣ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። ጨንገሮቹና ጋሬዳው ገብቶ ሲሰራ ጥበቡ ይመጣል፤ ጥለቱ ስሌን፣ ጥበብ ወይም ጉብጉብ ሊሆን ይችላል። የጨንገሩ ቁጥር ለጥበብ ከሆነ አስራ ሁለት ሲሆን ለሌሎቹ ቁጥሩ ይቀንሳል፤ ከስድስት እስከ አስር ባለው ድረስ ይሰራል።




ስዕል ተ.ቁ 7

19. **ጋሬዳ፦** ልክ እንደ ጨንገር የጥበብ ጌጥ ማውጫ ሰፋ ያለ ጠፍጣፋ እንጨት ሲሆን ጥቅሙ ጨንገሮቹ እንዲወጡና እንዲገቡ በማድረግ ክፍተት መፍጠር ነው። ጋሬዳው በሚፈጥረው ክፍተት ጨንገሮቹን ለሚፈለገው አገልግሎት ማዋል ይቻላል። ጋሬዳው ክፍተት ካልፈጠረላቸው ጨንገሮቹ ብቻቸውን ክፍትት ሊፈጥሩ አይችሉም።

20. **መቀናጭል፦** ከእንጨትና ከገመድ የሚሰራ ሲሆን የእንጨቱ አገልግሎት የመቀናጭሉን ሚዛን መጠበቅ ነው። የመቀናጭል ገመድ ደግሞ ገመዶቹ ክፍና ዝቅ በሚሉበት ጊዜ ክፍተት ስለሚፈጥሩ ለሸማ ስራው አጋዥ ናቸው። የመቀናጭል እንጨት ሲሰራ እንጨት ተከርክሮ ገመድ ይሆንበታል። ከገመዱ ያሉት እንጨቶች በገመዶቹ ሲነኩ ከፍና ዝቅ እያሉ ይከፍታሉ። የመቀናጭል አገልግሎት ሚዛን መጠበቅና ክፍተት በመፍጠር ሸማቃውን ለስራ ምቹ ማድረግ ነው።

21. **መቆራቆር፦** ሃያ አንድ ሴንቲ ሜትር የሚረዝም ቀጭን እንጨት ነው፡ ፡ ዳሩው ከላይና ከታች በኩል ተበስቶ እንጨቱ ይገባል። አገልግሎቱ ወንፊቱ ወለል ወለል እንዳይል ግጥም አድርጎ የሚይዝ ሲሆን ወንፊቱ ረግቶ እንዲቆም የሚያደርግ ነው።

22. **መወርወሪያ፡-** ከእንጨት የሚሰራ ሲሆን አገልግሎቱ ለምርት የተዘጋጀውን መምቻ ከግራ ወደቀኝ፣ ከቀኝ ወደ ግራ ማመላለስ ሲሆን ቀለሙ እየተመላለሰ እንዲሰራ ያደርጋል፡፡ ከመወርወሪያው ውስጥ ቀለም በመክተት ዝሃና መምቻው እንዲዋሃዱ ማድረጊያ ነው፡፡

23. **ቁጢት፡-** መጨረሻ ላይ በስምንት ገመድ ዝሃው ተይዞ ከተሰራ በኋላ ለመቋጠር አገልግሎት የሚውል ነው፡፡ ቁጢት የአንድ ሸማ ልብስ የመጨረሻው ደረጃ ሲሆን አገልግሎቱም ለመቋጠር ነው፡፡

24. **ዝሃ፣ ማግና ጥለት፡-** ዝሃ የሚባለው፣ የሚሰራው ሲሆን ማግ ደግሞ የሚወረወረው ነው፡፡ ጥለት ደግሞ ጌጥ የሚሆነው፣ በጨንገር ተለቅሞ የሚወጣው ነው፡፡ ሶስቱ ሲዋሃዱ ነው አንድ ሙሉ ስራ ሆነው የሚያምር ልብስ የሚሰራው፡፡ አገልግሎታቸው ሸማው ሙሉ ስራ እንዲሆን እየተዋሃዱ የሚሰሩ ክርና ዝሃው ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ሃያ ሰባት ቁሶች በአንድ ሲዋሃዱ ሙሉ ስራው ሳይስተጓጎል ስራው እንዲቀጥል ያደርጋሉ፡፡

## 4.2 ከሽመና የሚሰሩ ቁሶች አሰራር እና ተግባር

ይህ ርዕስ የቁሶች አሰራር በቅደም ተከተል የሚዘረዘርበት፣ የቁሶቹ መሸጫ ዋጋ የሚተርብበትና ቁሶቹ ምን ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ የሚታተትበት ነው፡፡ ቁሶቹ የሚሰሩበት የተለየ ቀንና ሁኔታ የለም፡፡ የሚደረጉበት ቀንና አጋጣሚ ግን የተለያየ ነው፡ ፡ ለሚከተሉት ዕቃዎች የምሰጠው ገለጻ የሸማ ሙያተኞች መረጃ አቀባዮች የሰጡኝ መሆኑን ልጠቁም እወዳለሁ፡፡ በዚህ ስር Fleming የቁሳዊ ባህል ባህርያት ብሎ ያስቀመጣቸውን ነጥቦች እና ከመተንተኛ ዘዴዎች ውስጥ መለየት እና ባህላዊ ትንታኔን፣ Schlereth የቁስ መሰሪያ ንጥረ ነገር እና አገልግሎት እና Prown ገለጻ ያሉት አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት 2.2.2፣ 2.2.3.2.1 እና 2.2.3.2ን ይመለከቷል፡፡

## ነጠላ



ስዕል ተ.ቁ 8

ነጠላ ለመስራት በመጀመሪያ ዝሃ ይገባል። ከተገባ በኋላ በኮሻይሊ[6] ሳይጠላለፍ ይዘጋል(ሙያተኞቹ እናዘጋዋለን ይሉታል)፣ ቀጥሎም የተዘጋው ዝሃ ይነከራል፣ ከተነከረ በኋላ ይሰጣል፣ ተሰጥቶ ሲደርቅ ይቋጠርና ይሰራል። ተቋጥሮ ሲሰራ ዝሃው ሳይጠላለፍ በደንብ ተለቅሞ በወንፌቱና በሚዚኑ ውስጥ እንዲያልፍ ይደረጋል። ዝሃው በደንብ ተወጥሮ ከተቋጠረ በኋላ ከመወርወሪያው ውስጥ መምቻ ቀለሙን በማስገባት በመምቻ እየተመታ ይሰራል። የሚሰራው ስራ በመጠቅለያው እየተጠቀለለ እየተሰራ እያለ የሚሰራው ልብስ እንዳይጨማተርና ቅርጹ እንዳይበላሽ በመወጠሪያ ይያዛል። ነጠላ ሲሰራ አራት ጥለት ስላለው ሃር ገብቶለት ጥለት ተደርጎበት በጥለት ይሰራል፣ አስፈላጊ ካሆነ ያለ ጥለትም ይሰራል።

ከጥለቶቹ ውስጥ ጥቁርና ቀይ ጥለት ያላቸው ነጠላዎች ከቁስነቱ የሰፋ ትዕምርት ያላቸው ሲሆን ጥቁር ጥለት ሃዘንን፣ ቀይ ጥለት ደግሞ ባለሃር መሆንን የሚጠቁሙ ሆነው ተገኝተዋል። ስለዚህ ጉዳይ አቶ ሹመት ነጋልኝ የተባሉ ባህልና ታሪክ አዋቂ መረጃ አቀባይ ሃሳባቸውን

[6] ኮሻይሊ ርዝመስ ቅርጽ ያለው ሲሆን ዝሃውን ለመግፍታት አገልግሎት የሚውል ከሸንበቆ የሚሰራ ዕቃ ነው።

ነጠላን የሚለብሱ ሴቶች ናቸው። ያደረጉት ነጠላ ታይቶ ስለሴቷ መናገር ይቻላል። ነጠላዋን ዘቅዝቃ በጥቁር ሃር የተሰራ ከለበሰች ሀዘንተኛንኝ ማለቷ ስለሆነ የሚያውቃት ሁሉ እየሄደ ምን ገጠመሽ በማለት ያጽናናታል። ነጠላው ቀይ ጥለት ካለው ባለ ቶሌ ነኝ ማለት ነው። ሰው ሲታመም ነይ ለምኚልኝ ተብላ ልትለምን ትችላለች። ሌላ አረንጓዴና ሰማያዊውን የበጎ ነገር ምስያ ተደርጎ ይወሰዳልብለው ነግረውኛል። (ጥር 26፣ 2003፣ መካነ ብርሃን)

ጥትሱ በምዕራፍ ሁለት Schlereth ትዕምርት፣ Fleming እና Prown ትርጓሜ ካሉት ጋር ይስማማል።

ነጠላ ሲጀመርና ሲጨረስ ባለ አራት መወርወሪያ ነው። አንዱ ዝሃ፣ አንዱ ፈትል፣ ሁለቱ ክር ይይዛሉ። ከመጀመሪያና መጨረሻው ውጭ ያለው ግን ባለ አንድ መወርወሪያ ነው። ነገር ግን ነጠላው ጥለት የሌለው ከሆነ በአንድ መወርወሪያ ብቻ መስራት ይቻላል። ነጠላ ከላይ የሚደረብ ልብስ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ይሰፋና ለተፈለገው ዓይነት ልብስ ከተፈለገ ለመጋረጃና ለእንስሳ አገልግሎት ጭምር ይውላል። ብዙ ጊዜ የሚለብሱት ሴትና ልጆች ናቸው። ምክንያቱም ቀለል ስለሚል ለብሰውት ለመንቀሳቀስም ሆነ ስራ ለመስራት ከሌሎቹ በተሻለ ምቹ ስለሚሆንላቸው ነው።

ነጠላ ርዝመቱ አስራ ሁለት ክንድ ወይም ስድስት ሜትር ሲሆን ተሰርቶ የእጅ ዋጋ ሃያ አምስት ብር ነው። ሌላውን ቁሳቁስ የሚያቀርበው አሰሪው ነው። ቁሳቁሱ ሙሉ እንዲሆን እቃውን አንድ ባንድ ሸማኔው እንዲመጣለት ተናግሮ በማስመጣት ይሰራል።

ኩታ

ኩታ ሲሰራ ዝሃው በሁሻይሌ ይዘጋና ከአራት ይቀለማል፤ ስምንት ጥለት አለው በየፈርጁ ጥለቱ ይገባል። ቀለሙን ሴቶች አቅልመው ያመጡታል፤ ዝሃውን በማሰናዳት በደንብ እየተመታ ይሰራል። ኩታ በሚሰራበት ጊዜ ኩታው ጥለት ያለው ከሆነ ባህላዊው ሸግቶ ባለሁለት መርገጫ ስለሆነ የኩታ ጥለቱን ለማውጣት ሸማቃው የግድ ባለ ሁለት መርገጫ ከሚሰጠው አገልግሎት ከፍ ማለት ስላለበት ሸማኔው የግድ ጨንገር

ይጠቀማል። ጨንገር[7] በመጠቀም ጨንገሮቹ ሸማቃው ባለ አራት መርገጫ የሚሰጠውን አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ አለባቸው።

ይህንን ለማድረግ በጋሬዳ ክፍተት በማውጣት በክፍተቱ ጨንገር አስገብቶ ይሰራል። ከስራ በኋላ ያን ጨንገር ያስወጣና በጋሬዳ አሁንም ክፍተት ፈጥሮ ሌላ ጨንገር ያስገባና ይሰራል። አንድ ዙር ሰርቶ ሲጨርስ የገባው ጨንገር ይወጣል። አሁንም በጋሬዳ አስከፍቶ ሌላውን ጨንገር በማስገባት ይሰራል። የጋሬዳው ጥቅም ሸማው ሲሰራ ክፍተት ፈጥሮ ጨንገሮቹን ለማስገባትና ሲጨርስም ለማስወጣት ነው። ብዙ ጊዜ ለአንድ ስራ ከስድስት እስከ አስራ ሁለት ጨንገሮችና አንድ ጋሬዳ ያስፈልጋሉ። የጨንገሮቹ ቁጥር ከስድስት እስከ አስራ ሁለት የደረሰው አሰራሩ ራሱ ሰሌን፣ ጥበብ እና ጉብጉብ የሚባሉ የተለያዩ የጥለት ዓይነቶች ስላሉ ነው። በምዕራፍ ሁለት Schiereth ጥበብ አመልካችንት እና አካባቢያዊነት፣ Fleming ጌጥ/design ካሉት ጋር የሚስማማ ነው።

የጥበቡ ጌጥ ሞስብ የሚመስል አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ሲሆን ሲሰራ አስራ ሁለት ጨንገር ይፈልጋል። ሰሌን ጌጡ ግማሽ ሆኖ የያንሳል ምልክት(<)ያለው ሲሆን ስምንት ወይም አስር ጨንገር ይፈልጋል። ጉብጉብ ደግሞ አራት ማዕዘን ያለው በሁለት ዓይነት ክር የሚሰራ ሲሆን ስድስት ጨንገር ይፈልጋል። የጨንገሮቹ ጥቅም የሚፈለገው ዓይነት ጌጥ እንዲመጣ ማድረግ ሲሆን ጥበቡ በጨንገሮቹ ተለቅሞ ሮመበስ ቅርጽ እስኪሆን ተቆጥሮ ይሰራል፤ ሰሌኑ የያንሳል ቅርጹ  እኩል እኩል ሆኖ እንዲመጣ ተደርጎ ይሰራል። ጉብጉቡ ደግሞ  ጌጡ አራት ማዕዘኑ ቅርጹ እኩል እንዲመጣ ተደርጎ ይሰራል። በእያንዳንዱ የጥለት ዓይነት የሚሰሩት ጥለቶች የመጀመሪያው ጥለት ቀጥሎ ከሚመጣው ጥለት በመጠን መብለጥ የለባቸውም። ምክንያቱም ካልተመጣጠነ የጥለቱን ውበት ያቀንሱታል። ኩታ ጥለት የሚገባበት ክሆን ባለ ስምንት መወርወሪያ ነው። ይህ የሆነበትም አንዱ ዝሃ፣ አንዱ ሻር ሌሎቹ የተለያዩ ለጌጡ የሚሆኑ ክሮች እየተፈራረቁ ተሰርተው ወደ ተፈለገው ቅርጽ መጥቶ ጌጡ እንዲያምር ስለሚረዱ ነው።

---

[7] ጨንገር ከሸንበቆ የሚዘጋጅ ሙያተኛው ጥበብ ለመስራት የሚገለገልበት ቁስ ነው።

የጥበብ ዲዛይ(ስዕል 4)



ስዕል ተ.ቁ 9

የስሌንዲዛይን(ስዕል 5)



ስዕል ተ.ቁ 10

ድሩ፣ ማጉ እና ጥለቱ ተዋህደው ዝሃው በደንብ ተመትቶ ከተሰራ በኋላ ኩታ በጥበብ ከሆነ አንድ መቶ ሃምሳ ብር፣ ያለ ጥለት ከሆነ ሰባ እና ሰማንያ ብር ይሸጣል። ዋጋው የእዮ ዋጋ እንጂ ሙሉ ቁሳቁሱን አይጨምርም። በዚህ ዋጋ የሚሸጠው ኩታ ርዝመቱ ሃያ ስድስት ክንድ ወይም አስራ ሶስት ሜትር ይሆናል።

ኩታን ብዙ ጊዜ ወንዶች የሚለብሱት ልብስ ሲሆን የሚለበሰው በአዘቦት ቀን ሳይሆን ሰርግ፣ በለቅሶ፣ በተዝቆርና በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎችና ጥሪዎች ሲሄዱ ነው። ምክንያቱም ልብሱ በዚህ ጊዜ ከልብስነት የዘለለ ትዕምርት አለው። ይህም ልብሱ የሰውየውን አኗኗር(ድሃ ፣ ሃብታም ወይም ባለጸጋነት) ይገልጻል። በምዕራፍ ሁለት Schlereth ትዕምርት፣ Fleming እና Prown ትርጓሜ ካሉት ጋር የሚዛመድ ነው። በአለባበሱም ቃል ግጥም ይነገርለታል፣ ወይም ይነገርበታል (ስነቃልና ትንታኔው በምዕራፍ አምስት ቀርቧል)።

## ፎጣ

ፎጣ ሲሰራ ዝሃው ተዘግቶ ይጣላል፣ ከተዘጋ በኋላ በተጣለው ዝሃ ላይ ቀለሙ እየተወረወረ በደንብ እየተመታ ይሰራል። ሲሰራ አንድ መልክ/ቀለም ሲሆን ይችላል፤ ባለ ብዙ ቀለምም ሊሆን ይችላል። ብዙ ጊዜ ባለሶስት ቀለም ፎጣ የተለመደ ሲሆን የቀለሙ ዓይነት በአሰሪውና በሰሪው ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ይሆናል። አቶ አዳነ ሙሴጦፋ የተባሉ የሽማ ሙያተኛ የፎጣ አሰራርን እንደሚከተለው አስረድተዋል።

> ዝሃው ከተጣለ በኋላ ሃሩ (ክሩ) እንደ መምቻ በመጠቀም ይሰራል። ክሩን አደባልቆ በመስራት የተሰራው ጨርቅ ከፎጣ በተጨማሪ ለኮት፣ ለሸሚዝና ለአልጋ ልብስ አገልግሎት ይውላል። ብዙ ጊዜ አልጋ ልብስ ወፈር፤ ፎጣና የሸሚዙ ስራ ደግሞ ሰሳ ስለሚል የአልጋ ልብስ ሸማ ለብቻ ይሰራል። አሰሪዎቹ የአልጋ ልብሱ ሰሳ ይበል ካሉ ግን በአንድ ተሰርቶ ከተጠናቀቀ በኋላ አሰሪዎቹ የሚፈልጉትን ያህል አስቆርጠው ይወስዳሉ። ፎጣ አንድ መልክ ከሆነ በአንድ መወርወሪያ ይሰራል፤ አለበለዚያ በሁለት መወርመሪያ ተቀላቅሉ ይሰራል።(የካቲት 17፣ 2003፣ መኮነ ብርሃን)

የፎጣ ዋጋን በሚመለከት አቶ አህመድ አወል የተባሉ የሸማ ሙያተኛ የሚከተለውን ሃሳብ አጫውተውኛል።

> የፎጣ ስራ ዋጋ አንድ መልክ/ቀለም ለክንድ ሁለት ብር ሲሆን ብዙ ጊዜ ፎጣ አስራ ሁለት ክንድ ወይም ስድስት ሜትር ስለሚሆን ሃያ አራት ብር ይሸጣል። ኮትና ሸሚዝ በአንድ መልክ ከሆነ ልክ እንደ ፎጣው ሃያ አራት ብር ይሸጣል። በርግጥ አሰራሩ አንድ መልክ ሲሰሩት በአንድ መወርወሪያ ስለሆን አሰራሩ ይቀላል፤ በሁለት መወርወሪያ ሲሰራ ግን ጥለቱ ስለሚሸብረቅ ትንሽ ከበድ ይላል፤ ዋጋውም ከባለ አንድ መልኩ ከአምስት እስከ አስር ብር ይጨምራል፤ ስለዚህ የፎጣው ዋጋ ሰላሳ እስከ ሰላሳ አምስት ብር ሲሆን የኮትና የሸሚዝ ዋጋም ሰላሳ እስከ ሰላሳ አምስት ብር ይሆናል ማለት ነው። የፎጣ አብዛኛው ሸማች የገጠሩ ህብረተሰብ ነው። (የካቲት 13፣ 2003፣ መኮነ ብርሃን)

Schlereth አካባቢያዊነት ያሉትን ልብ ይሏል። ፎጣ የሚለበሰው በስራ ወቅት ስለሆነ ብዙ ጊዜ ደብዘዝ ባሉ ቀለማት ይሰራል።

በሸማ ማህበር ተደራጅተው የሚሰሩት የሸማ ሙያተኞች ዋጋቸው ከሌሎች የሚለይ ሲሆን ለሜትር አርባ ብር ይሸጣሉ። በሁለቱ መካከል ሰፊ የዋጋ ልዩነት ይታያል።

በምን ስለሚለያዩ ነው በዋጋው ላይ ሰፊ ልዩነት የታየው ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ አቶ ደጋፉ ምስጋናው የተባሉ የሽማ ሙያተኛ መረጃ አቀባይ የሰጡት መልስ የሚከተለው ነው።

> ፎጣ ሲሰራ ክር አንድ ቱባ አስራ አምስት ብር ስለምንገዛው ውድ ስለሆነ ነው። በፊት አስር ብር ይገዛ ነበር። እኛ በአስራ አምስት ብር ገዝተን አደባልቀን ስለምንሰራው ባለአራት መርገጫው በደንብ ስለሚመታ ክሩን ስለሚበላው ክር ይፈጅብናልና ሁለት ሜትሩን ስማንያ ብር እንሸጠዋለን። እነዛኞቹ ግን በአንድ መልክ ስለሚሰሩት እና ሸማታው ባለሁለት መርገጫ ስለሆነ ክር ስለማይበላ ሰላሳ ብር ያዋጣቸዋል። (የካቲት 16፣ 2003፣ መካነ ብርሃን)

## ቀሚስ

ዝሃው ተገሎ ይዘጋል፤ ዝሃው ከተወጠረ በኋላ እየተመታ ይሰራል። ለቀሚሱ ጥበብ የሚያስፈልገው ከሆነ በአስራ ሁለት ጨንገር ተለቅሞ ጥበብ ይሰራል። ጥበብ ቀሚስ ዋጋው ጥሩ ሲሆን ስራው ግን ያደክማል። በተለይ ጥበቡ እንዲጎላ ተብሎ ጥበቡ ሰፊ እንዲሆን ከተደረገ ጊዜም፣ ገንዘብም ይፈልጋል። አሰሪዎቹ ለጥበብ ሙያተኛው ሁሉንም አቅርበው ለእጅ ስማንያ ብር ይከፍላሉ። ጥበብ የሌለው ከሆነ ሃምሳ ብር ይከፍላሉ። ሸማኔ የጠሩም፣ የከተማውም ኅብረተሰብ ነው። ቀሚስ ያለጥበብ ከሆነ በአንድ መወርወሪያ፣ በጥበብ ከሆነ በሁለት መወርወሪያ ይሰራል። በጥበብ የሚሰራው ቀሚስ በጨንገሮቹ ተለቅሞ ጌጡ ባማረ መልኩ ይሰራል።

ከላይ የተዘረዘሩት ቁሶች ሲሰሩ የሴቶች እገዛ አለበት። በተለይ ጥጥ ፈትለው በማቅረብ፣ ጥጡን ፈትለው ልቅ በማድረግ፣ ልቃን በማጠንጠን፣ በማቅለም ሃላፊነታቸውን ይወጣሉ። እንዲሁም ዝሃ ነክረው፣ ዘርግተውና አድርቀው ለስራ ምቹ አድርገው በማስናዳት ለሸማኔው በማቅረብ ሙያተኛውን ይረዱታል።

## ስካርፕ

ለመስራት በመጀመሪያ ክር ይደራል ወይም ይዘጋል። ክሩ ከተዘጋ በኋላ እንደገና ክሩ ይቀለማል። የሚቀለመው ክር ለመምቻ የሚሆነው ነው። ክሩ ተዘግቶ ሸማቃው ላይ ከተጣለ በኋላ በመምቻ እየተመታ ይሰራል። አንድ መልክ ተደርቶ ሌላ መልክ ደግሞ ተወርዋሪ ተደርጎ መምቻ ይሆናል። ዲዛይን የሚደረግበት ከሆነ ደግሞ ብዙ ክሮችና መርገጫው እየተቀያየሩ ይሰራል። የዲዛይኑ አይነት፣ የልብሱ ርዝመት (አጭር፣ ረጅም) በአሰሪው ፍላጎት ይሆናል። ስካርፍ ሲሰራ ሙሉ ሥራው ዲዛይን ያለው ከሆነ በባለ አራት መርገጫ የሚሰራ ሲሆን ዲዛይኑ ጫፍና ጫፍ ብቻ ከሆነ ጫፉን ባለ አራት መርገጫ ሰርቶ ቀሪውን በባለ ሁለት መርገጫ ይሰራል። አልያም በጨንገር ተለቅሞ ጌጥ ይወጣለታል።

ስካርፕ እንደ ዲዛይኑ አጣጣል እንደ እቃው ትንሽነትና ትልቅነት ዋጋው የተለያየ ነው። ቀለል ያለ ዲዛይን ከአርባ አምስት እስከ አምሳ ብር ይሸጣል። ከበድ ያለ የውስጥ ዲዛይን ያለው ደግሞ ከሰማንያ እስከ አንድ መቶ ሃያ ብር ይሸጣል። የስካርፍ ርዝመት ቁመቱ ሁለት ሜትር ሲሆን ወርዱ አንድ ሜትር ነው። ቁመቱ አንድ ሜትር ወርዱ አምሳ ሳንቲ ሜትር የሆነው ደግሞ በሰልሳ ብር ይሸጣል። ስካርፕ ከአንገት የሚደረግ የአንገት ልብስ ሲሆን ተጠቃሚው በአብዛኛው የከተማው ህብረተሰብ ሲሆን የሚሰራላቸውን ዲዛይን በማሳየት ያሰራሉ። የገጠሩ ህብረተሰብ የዚህ ምርት ብዙም ተጠቃሚ አይደለም። ነገር ግን ቀለል ያለ ዲዛይን ያላቸውን ዲዛይኖች ለራስ መጠምጠሚያ ይገለገሉበታል።

## የአልጋ ልብስ

ሱፍ ክር በደንብ ይደራል። የአልጋ ልብስ ወርዱ በጣም ሰፊ ስለሆነ በምሂሩና በወንፊቱ ልክ ሙሉ ለሙሉ ዝሃው የሚጣል ሲሆን የተለያዩ ክሮችን መምቻ በማድረግ የተለያዩ ዲዛይኖችን በውስጥ ስንቅር በማስገባት ይሰራል። የአልጋ ልብስ ሲሰራ ድሩ አንድ መልክ ሆኖ ተወርዋሪው ብዙ መልክ ሊሆን ይገባል። ሥራው አንድ መልክ ብቻ ስለማይሆን ጥበብ እየተሰራ ሌላ ጌጥ ለማምጣት መርገጫው የተለያየ (ባለአራት)፣ የክሩ ቀለምም ከሁለት በላይ መሆን አለበት። ምክንያቱም ጥበብና ስሌን ጥለት ለማምጣት

አፈ.ንዘው የተለያየ ነውና። ሥራው ወደ አንድ ሜትር አካባቢ ዲዛይን የሚጣልበት ሲሆን አልፎ አልፎ ደግሞ የተወሰነ ሴንቲ ሜትር እየተዘለለ ሌላ አይነት ጥለት ይጣላል። ሸማቹ የከተማው ህብረተሰብ ሲሆን በሜትር ስማንያ ብር ይሸጣል።

## ሸሚዝ

ክሩ ከተደራ በኂላ ሁለት አይነት ክር ይጣላል። የሚወረወረው ሁለት አይነት ክር ሲሆን ድሩ ለመምቻነት ያገለግላል። ብዙ ጊዜ ሸሚዝ ለመስራት የሚመረጠው ሁለት መርገጫ ነው። ምክንያቱም ሸሚዙ ስስ እንዲሆን ስለሚፈለግ ነው። ባለ አራት መርገጫ ከሆነ ግን ዳፋው በደንብ ስለሚመታ ስራው/ሸማው ይወፍራል፤ ብዙ ገዥም አያገኝም። ሰዉ የሚፈልገው ስስ ሸሚዝ ነው። ሸማቹ የገጠሩም የከተማውም ህብረተሰብ ሲሆን በከተማው ሰኩዌር ሸሚዝ በጣም ይወደዳል። ሸሚዝ በሜትር ስልሳ እና ሰባ ብር ይሸጣል።

## 4.3 የሸመና ሙያተኞች ሕይወት

በዚህ ክፍል ከሙያተኞቹ ሕይወት ጋር በተያያዘ ሃይማኖት፤ መገለል፤ ሙያ ለመዳ እና በሙያውና በሙያተኞቹ ላይ የታዩ አዎንታዊና አሉታዊ ለውጦች ይዳሰሳሉ።

መገለሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል እየታየበት አዎንታዊ ጎኑ እያመዘነ ይገኛል። ሙያተኞቹ ቀደም ባሉት ጊዜያት ከሙገሳ/ምስጋና ይልቅ ነቀፌታ፤ ከሽልማት ይልቅ ቅጣት ይበዛባቸው ነበር። ጥበብ ሰርተው ባለበሱ፤ ድርብ ኩታ ሰርተው ባለበሱና ሰው ሁሉ ለብሶ እንዲያምርበት ባደረጉ አጥንት ድረስ ዘልቆ የሚወጋ ነው። ሰርተው የለፋታቸውን ዋጋ ሲጠይቁ አሰሪው ነገ ነገ እያለ ያስራብትን የሚያስቀርበት ጊዜ ነበር። እንዲሁም ገንዘቡን አዘግይቶ በፈለገ ጊዜ ያመጣ ነበር። አጥብቆ ገንዘቤን ቢል ይኼ ቁጢት በጣሽ ነዝንዞ ገደለኝ ይባሉ እንደነበር የአካባቢው ነዋሪዎችና ሙያተኞች በተለይ አቶ እሸቱ ውብልኝ ያስታውሳሉ። አሁን ግን በሙሉ ባይሆንም አሉታዊ ገጽታዎቹ ቀስ በቀስ ወደ አዎንታዊ ገጽታዎች በመቀየር ላይ ናቸው።

ከላይ ለቀረበው ሃሳብ ማጠናከሪያ ይሆን ዘንድ አቶ የኑስ ሙስጠፋ የተባሉ በሽመና ሙያ የሚተዳደሩ መረጃ አቀባይ የሰጡትን ሃሳብ እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

> እኔ ወደ 30 ዓመት ገደማ ሽማቶ ሰርቻለሁ፡፡ የድሮና የአሁኑን ሳስተያየው በጣም የተለያየ ይሆንብኛል፡፡ እንደ አሁኑ ሽማኔ በየሄደበት አሽሙር የለለበት፤ እና በራሱ ገንዘብ ቤት ሰርቶ ይኖራል ብየ አሳቤየም አልነበር፡፡ ያው ቁጢት በጣሽ ሽማኔ እየተባልንልንዘልቅ ይሆን እል ነበር፡ ፡ አሁን ግን ስድቡም የለም፣ ሁሉም ደህና እንዲያውም መንግስት እደግፋችኋለሁ በማህበር ተደራጁ እየተባልን ነው፡፡ (የካቲት 10፣ 2003፣ መካነ ብርሃን)

ድሮ ሙያተኛው/ሽማኔ ቁጢት በጣሽ ተብሎ የሚጠራ የነበረ ሲሆን አሁን ከሽማኔ በተሻለ በን ስያሜ ወጥቶለት ጥበብ ሰሪ በመባል ስማቸው ከፍ ብሎ እየተጠራ ይገኛል፡፡ ይህንን ለውጥ በምልከታና በቃለ መጠይቅ ታዝቤያለሁ፡፡ "ድሮ ልብስ ሰርተን ልብሱ ጥሩ ቢሆን እንኳ አሰሪው እንደ ምንም እንክን ፈልጎ ያችን አጉልቶ አንቋሽሾን ይሄድ ነበር፡፡ አሁንማ አለም ነው" (የካቲት18፣ 2003፣ መካነ ብርሃን) በማለት በሽመና ሙያ የሚተዳደሩት አቶ አህመድ አወል የድሮና የዛሬውን በማነጻጸር ገልጸዋል፡፡ ዛሬ በን በመስሪያቸው ሸልማቱ በቁስ ባይሆንም ጥሩ ስለሰራህ ተብሎ በሙያው እውቅና ተሰጥቶት ይመሰገናል፡፡ ምስጋናው በቃል ግጥም የታጀበ ሲሆን ብዙ ቃል ግጥሞች ይዘት የሚያተኩረው የሙያተኛው ሙያ ጥሩ በመሆኑ የምስጋናና የሙገሳ ይዘቶች ያላቸው ናቸው፡፡ ሽማኔ ከማለት ወደ ጥበብ ሰሪ የሚለው ስያሜ እየተለመደ መጥቷል፡፡ በምልፍና ሁለት Schlereth ማህበረሰብ ታሪካዊነት ካሉት ጋር የሚስማማ ነው፡፡

ከ1983 በፊት ማህበራዊ ሕይወታቸውን በተጽእኖ ይገፉ እንደ ነበር፡፡ ሰሪው ብቻ ሳይሆን የሙያተኛው ቤተሰብ በሙሉ ይንቋሸሽ እንደ ነበር፡፡ ምክንያቱም ሽማኔ ማለት ለእነሱ ፈሪ፣ እንደ ወንድ ጣባ ወርዶ ቶቅ አድኖ አለበለዚያም እንጨት ሰብሮ ማምጣት የማይችል፣ "እንደ ሴት" ቤት ውስጥ ተወዝፎ የሚውል ተደርጎ ይቆጠር ነበር በማለት በሸማ ሙያ የሚተዳደሩት አቶ አዳነ ሙስጠፋ የተባሉ መረጃ አቀባይ ሃሳባቸውን ገልጸዋል(የካቲት 11፣ 2003፣ መካነ ብርሃን)፡፡ Schlereth ባሕርይ አመልካችነት ያሉትን ልብ ይሏል፡፡ ህብረተሰቡ ለሙያተኞቹ ባህርይ አወጣላቸው ማለት ነው፡፡

ሙያተኛዉ እነሰውም ሸማኔ ቤት የሚውሰው ስራውን ለማድማት እንጂ ፈሪ ሆኖ ወይም አትም አጥቶ እንዳልሆነ በጊዜ ሂደት ተረዱ። ምክንያቱም ከ1983 ወዲህ መሬት ሲሰጣቸው ባዛ ወርደው እንጨት ለቅመውና ሩቅ ቦታ ድረስ ሄደው አርሰው በልተዋል፤ የሁኔታዎች አስገዳጅነት እንጂ ፈሪ እንዳልሆኑ አሳዩ። ዛሬ ያለመገለል ከህብረተሰቡ ጋር አብረው ይበላሉ፣ ይጠጣሉ። በጋብቻም ሆነ በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እኩል በሚባል ደረጃ ይሳተፋሉ። በተጨማሪም አቶ አዳነ ሙስጦፋ ሃሳብ ጋር የሚገናኝ ሃሳብ በሽመና ሙያ የሚተዳደሩ አቶ ሰኢድ መሃመድ

> ሽመና የስንፍ ስራ የስላም ስራ እንጂ የክርስቲያን ስራ አይደለም። የክርስቲያን ስራ እርሻ ነው። ስላምሳ ሸማታ ወይም ሸቀጥ ነው የሚሸትጥ ሲሉ ነበር። እና ስላም እርሻ አያርስም ነበር። አሁን ክርስቲያኑ በእስርቤትና አንዳንድ ብልሆች ከስላም ጠጋ ብለው ይለለጥኑና ይሰራሉ። ድሮ ግን ሽመና የስላም ስራ የፈሪ ስራ ይሉ ነበር። ብለው አጫውተውኛል። (የካቲት 27፣ 2003፣ መካነ ብርሃን)

ጥቅሱ እንደሚያሳየው የሽመና ሙያ ፈሪና ሰነፍ የሚሰራው ነው ተብሎ ይታመን ነበር፡ ፣ ፈሪና ሰነፍ ደግሞ የሙስሊም እምነት ነው በሚል ዕምነት ነበር ሙያውን ለሙስሊሞች ይሰጡ ነበር። ወ/ሮ እንክይ ጉታቱ የተባሉ የሸማ ሙያተኛ እንደገለጹት "ተጸእኖው ቀደም ባሉት ጊዜያት የጎላ ነበር አሁን ግን ሙስሊሞች ያርሳሉ፣ ክርስቲያኖም ይሸምናል። በፊት የነበረው ችግር የአመለካከትና የዕምነት ችግር ሲሆን አሁን ግን ችግሩ ተቀርፎልን ስራችንን በመስራት ላይ ነን።" (የካቲት 14፣ 2003፣ መካነ ብርሃን) በን ለውጥ እንዳለ በምልከታና በቃለ መጠይቅ ለመታዘብ ችያለሁ። ነገር ግን ችግሩ ሙሉ በሙሉ ተፈትቷል ማለቱ እንዳልሆነ ልብ ይሏል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት እንዱ የአንዱን ሙያ ላለመቀበላቸው ምክንያቱ ምንድን ነው ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ አቶ አደም አማን የተባሉ የሸማ ሙያተኛ የሰጡት መልስ "ሙስሊሙ የሚያርሰው እርሻ ስላልነበረው፣ ክርስቲያኑ ሙያው ለሙስሊም ብቻ የተሰጠ አድርጎ በማሰብ ሙያውን ከመልመድ ይቆጠቡ ስለነበር ነው።" አቶ አደም አማን እነሰውም ሙስሊሞች የሸማ ሙያተኛ የሆነበትን ምክንያት እንዲህ ገልጸውታል፡ ፣ "እኛ (ሙስሊሞች) በጊዜው የምናርሰው መሬት ስላልነበረን ለመኖር መሸቀጥ ወይ

ሸማቶ በመስራት እንኖራለን፡፡ ክርስቲያኑ ግን ሲፈልግ እርሻ ይይዛል፣ ደሞ አገረ ገዥ የሚሆኑት ሁሉ እነሱ ናቸው፡፡ . . . ከኢሃዴግ ወዲህ ግን መሬት ሲገመድ ለኛም ተገመደ፣ ማረስ ጀመርን፡፡ ሁሉ ነገር መስተካከል የጀመረው እኛ ማረስ ከጀመርን በኋላ ነው፡፡" (የካቲት 23፣ 2003፣ መካነ ብርሃን)

ከሃይማኖት አንጻር በአካባቢው አንድ ሰው ሸማኔ ከሆነ ዕምነቱ አይጠየቅም፣ ሙስሊም እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በምልከታ እንዳስተዋልኩትም ከሃያ ስድስት የሸመና ሙያተኞች ውስጥ ሃያ ሁለት ሙስሊሞች ናቸው፡፡ በቁጥር አራት የሆኑት ሸማኔዎች ደግሞ ክርስቲያን ሲሆኑ ዕድገታቸው እንዱ ሙያተኛ ከአካባቢው በራቀ አካባቢ ኖሮ አሁን በጋብቻ ወደ አካባቢው የመጣ ሲሆን፣ ሌሎቹ ደግሞ የአካባቢው ተወላጅ ኖረው በተለያዩ ምክንያቶች አካባቢያቸውን ለቀው ሌላ ህብረተሰብ ውስጥ ሙያውን ለምደው የመጡ ናቸው፡፡

የአካባቢው ሸማኔዎች በአብዛኛው ለምን የሙስሊሞች ቁጥር ከፍ አለ ብዬ አቶ አዳነ ሙስጠፋ የተባሉ የሸማ ሙያተኛን ጠይቄ የሰጡኝ መልስ "ሸመና የስላም (ሙስሊም) ስራ አድርገው ስለሚቆጥሩትና በፊት በፊት ስላም ገመድ ስላልተገመደ ሸማኔው ሁሉ ስላም ነው ብለው መልሰውልኛል፡፡" (የካቲት 17፣ 2003፣ መካነ ብርሃን) ይህን ሃሳብ አቶ እሸት ውብልኝ የተባሉ መረጃ አቀባይም ይጋሩታል፡፡ አቶ እሸት አክለውም

> ክርስቲያን ሆኖ ሽመና ሊለምድ የሚፈልግን ሰው ያልሆነው ህብረተሰብ ያለ አባትህ፣ ያለ ዘርህ ሸማኔ ልሁን ትላለህ ተብሎ ስለሚነቀፍ ለመዱውን ይተውዋል፡፡ በዋናነት ግን የሚቃወሙት ከሱ የስጋ ዝምድና ያላቸው ናቸው፡፡ ምክንያቱም እሱ ሸማኔ ከሆነ ዘመዶቹ በሱ ምክንያት ጋብቻ ሲጠይቁ አይሰጣቸውም ብለው ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡(የካቲት 6፣ 2003፣ መካነ ብርሃን)

ህብረተሰቡ የሸማ ስራ ክቡ ጥሩ እንደሆነ ቢያውቅም አሁንም ክርስቲያኑ ሸማኔ እንዲሆን አይፈልግም፡፡ ከሆነም ያለ አባቱ ይባላል፡፡ ክርስቲያን ሸማኔ ከሆኑት አንዱ አቶ ደጋፍ ምስጋናው ሁኔታውን ሲገልጹ፡-

> አገራችን ትገሽ ክበድ ይላል። እኔን ራሱ ሸሁ ነው የሚሉኝ እኔ ግን ምንም መስሉ አይታየኝም በኔ ሳይሆን በራሳቸው ነው ሸሁ ማለት በክርስቲያን ሳይሆን በስላሞችም በጣም ትልቅ ነው የሚባል ነው። ሸሁ ሲሉኝ ሸህ ነህ ለማለት ነው። ይዘኸው ያለኸው የሙስሊም ስራ ነው ማለታቸው ነው። በኛ አገር ሙስሊሞች ናቸው። ክርስቲያን እስከ አሁን የለም። አሁን አሁን ነው የመጣው። ከሙስሊም ራሱ ሴት አይሰራም። የያዙት ስራ ጥርት ያለሽ ስለሆነች አልፎ አልፎ በርታ የሚለኝ መንግስት ሰራተኞች ናቸው። ነዋሪው ሸሁ ሲሉኝ መልስ አልሰጣቸውም መልስ ከሰጠኋቸውማ ደግሞ ሌላ ይሉኛል። ስቄ አልፌ እሄዳለሁ፤ ወይም ዝም እላለሁ። ግን እንዲህ አለኝ ብየ እንዴት አደርክ እንዴት ዋልክ አልከለክልም። (የካቲት 4፣ 2003፣ መኮነ ብርሃን)

ሙያተኞቹ ሙያውን የለመዱበትን መንገድ ስንመለከት ደግሞ ሙያውን በተለያዩ አጋጣሚዎች ከአካባቢውና ከአካባቢው ውጭ ለምደው የመጡበት አጋጣሚ አለ። በትውልድ አካባቢያቸው የሚገኙ ሸማኔዎች ሙያውን የለመዱት በልጅነታቸው ዘመን ከአባት ወደ ልጅ በማስተላለፍ ሲሆን አብዛኞቹን በህፃንነታቸው ሲያጡ ከአንት ወይም ከሌላ ዘመድ ጋር ተጠግተው ሙያውን ለምደዋል። Roberts የእጅ ሙያተኞች በአብዛኛው ሙያውን የሚለምዱት ከአባት ወደ ልጅ በዘር ተስተላልፎ ነው ያሉትን ልብ ይሏል። በዚህ መንገድ ሙያውን ከለመዱት ውስጥ አቶ አህመድ አወል አንዱ ናቸው። ሙያውን የለመዱበትን መንገድ እንዲህ ገልጸውታል።

> እኔ ሙያውን የለመድኩት ገና ጭቅላ እያለሁ ነው። ጭቅላ እያለሁ አባቴ ስለሞተ እናቴ ለወንድሟ ሰጥታ ከሱ ጋር መኖር ጀመርኩ፤ እሱ ሲሰራ እኔ እከታተለው ነበር። ምኑን ሲረግጠው ምን ይመጣል እያልኩ እከታተላለሁ፤ ሲልከኝ እላክለሁ። ኋላ 16 ዓመት ሲሞላኝ ሸማ መስራት ጀመርኩ ስጀምር የሱ ረዳት ሆኘ ነው። ኋላ በደንብ ስለምድ ብቻየን ቤት ተከራይቼ መስራት ጀመርኩ። በደረግ ደግሞ በወረዳው ለሸማኔዎች አሰልጣኝ ሆኘ ተመርጬ ደባርቅ የሚባል አገር ሄጀ ስልጥኝ መጥቼ የተወሰነ

ጊዜ እዚህ (ጃናሞራ) እሰለጥኛለሁ። (የካቲት 9፣ 2003፣ መካነ ብርሃን)

ከአካባቢው ውጭ ሙያውን የለመዱት ደግሞ ከፊሉቹ በተለያየ አጋጣሚ ከነበሩበት ስራ ሲፈናቀሉ ምን ስርቼ ልብላ ብለው ሲያስቡ ጎልማሶች ማሰልጠኛ ጣቢያ ገብተው በመሰልጠን ሙያውን ለምደው ሙያተኛ የሆኑበት አጋጣሚ አለ። እንዲሁም ስልጠና ወደሚሰጥበት ስፍራ ሄደው ሠልጥነው የተመለሱም አሉ። በዚህ ሙያም ሕይወታቸውን እየመሩበት ይገኛል። በዚህ መንገድ ሙያውን ከለመዱት ውስጥ አቶ አለልኝ ጌቡ የተባሉ በሽመና ሙያ የሚተዳደሩ መረጃ አቀባይ የለመዱበትን መንገድ እንዲህ ገልጸዋል።

> ሙያውን የለመድኩት ደብርቅ ታስሬ እያለሁ ብዙ ሰዎች የእጅ ሙያ የሚለምዱበት የተለያየ ስልጠና እስርቤቱ ውስጥ ይሰጥ ነበር። ልብስ ስፌት፣ ሽመና፣ ጥልፍ ስራና ሌላም ስልጠና ነበር። ከዚህ ውስጥ ሽመናን መርጬ ሰልጥኛለሁ። ከእስር ስፈታ ያኔ በተማርኩት መሰረት ነፃ ሙያው መተዳደሪያየ ሆኖ ልጆ የማሳድገው ከዚህ በማገኘው ገቢ ነው። (ጥር 20፣ 2003፣ መካነ ብርሃን)

ሙያውን ለመልመድ ስልጠና ወደሚሰጥበት ስፍራ ሄደው ሰልጥነው ከተመለሱት ውስጥ በሽግ ማህበር ተደራጅተው በሙያው የቀጠሉ ሙያተኞች ተጠቃሽ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ወ/ሮ አለሚቱ ጌጡ የተባሉ የሽግ ሰራተኛ የለመዱውን ሁኔታ እንዲህ አስረድተዋል፡ "በቀበሌ ተመልምለን ለጥቃትን ተሰጠን ጥቃትን ደግሞ አሰልጣኝ አስመጥቶ ሲያስተምረን ሙያውን ለመድኩት። ዲዛይንና የባለ አራቱ እንጂ ነጠላ ግን ቀደም ብዮ አስራለሁ። ሙሉቀን የሚባል አሰልጣኝ መጥቶ ብዙ የዲዛይን አይነት እና መወርወሪያው (የባለ 4 መርገጫ) እንደዚህ ነው የሚወረወረው፤ ይህንን ስትረግጡ ይህ ይመጣል ይለን ነበር።" (የካቲት 8፣ 2003፣ መካነ ብርሃን)

በዚህ ሶስት አመታት ውስጥ ደግሞ በፊት በሽመና ሙያ የሚተዳደሩ ሸማኔዎች በማህበር ተደራጅተው በወረዳው ጥቃቅንና ንግድ ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ርዳታ አጭር ስልጠና ተሰጥቷቸው በባለ አራት መርገጫ መስራት ጀምረዋል። አቶ ሰዒድ

መሃመድ የተባሉ የሸማ ሙያተኛ በማህበር ከተደራጁት ጋርና በግላቸውም ስለሚሰሩ የባለ አራትና የባለ ሁለት መርገጫ ሸማቃ ጥቅም እንዲህ ገልጸውታል።

> የባለ አራቱ መርገጫ ሸማቃ ጥቅም ጊዜና ጉልበትን ይቆጥባል። በባለሁለቱ መርገጫ ሲሰራ ጥለት ለመስራት ጥለቱ በተፈለገው ጌጥ እንዲወጣ ሲባል ከስድስት እስከ አስራ ሁለት ጨንገር ተቆጥሮ ነበር፣ አንድ ዙር ተሰርቶ አንድ ጨንገር ይወጣል፣ ሌላ ዙር ሲሰራ ደግሞ ሌላ ጨንገር ይወጣል። እንዲህ እንዲህ እያለ እስከ አስራ ሁለት ጨንገር ሲሰራ የሚወስደው ጊዜ ብዙ ሲሆን ባለአራቱ መርገጫ ግን ያለ ጨንገር መርገጫዎቹን በመቀያየር ስለሚሰራ ጊዜን በደንብ ይቆጥባል። ጊዜን ከቀነሰ ደግሞ በአጭር ጊዜ ብዙ እቃ ሰርቶ የተሻለ ገቢ ለማግኘት ይረዳል። ባለ አራት መርገጫ ጊዜ መቆጠቡ ሲ... ሆኖ እያለ ግን ዳሩው በደንብ ስለሚመታ ስራው ብዙ ክር ይፈጃል። ባለ ሁለት መርገጫ ክር አይበላም። ምክንያቱም ብዙ መምታ ስለማይፈልግ። ግን በባለ ሁለት መርገጫ ጨንገር እያስገቡ ማንኛውንም ዲዛይን ያለው ልብስ መስራት ይቻላል። (ጥር 27፣ 2003፣ መካነ ብርሃን)

ሙያውን አሁንም ልክ እንደ አባቶቻቸው ለማስተላለፍ ልጆቻቸውን በማስተማር ላይ ያሉ ሲሆን ኣልደረሱ ህፃን ልጆቻቸው ጭምር ገና ከአሁኑ ሸማቃ ሰርተው ያስቀመጡ እንዳሉ በቃለ መጠይቅና በምልከታ ለመታዘብ ችያለሁ። ከነዚህ ውስጥ ሰኢድ መሃመድ ተጠቃሽ ነው። "እኔ አሁን ሶስት ሸማቃ ሰርቼ ለልጆቼ አስቀምጫለሁ። ልጆቼ ሲደርሱ አውጥቼ ሰርተው እንዲበሉ እሰጣቸዋለሁ።" (ጥር 27፣ 2003፣ መካነ ብርሃን) አቶ ሰዒድ ሞላ የተባሉ የሸማ ሙያተኛ ደግሞ ሙያውን ከእርስዎ በኋላ የሚቀበልዎ አለ ወይ ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት መልስ "ለልጆቼ አወርሳለሁ ግን ልጆቼ ገና ህፃን ስለሆኑ ወንድም አለኝ እሱ እንዲያውቅ አደርጋለሁ። ሙያው እንዲተላለፍ የምፈልገው ገቢው ጥሩ ስለሆነ ሳይሆን እውቀቱን ስለወደድኩት ነው። ስኩዌር ሸሚዝ ሰርቼ ውብ ሁና ሰው ለብሶት ሳይ ደስ ይለኛል።" በማለት ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል። (የካቲት 4፣ 2003፣ መካነ ብርሃን) በሌላ በኩል ደግሞ ሙያውን ለልጆቻቸው ሳያወርሱ

እስተምረው ልጆቻቸውን በሌላ ሙያ ማየት የሚፈልጉ አሉ። ብዙዎቹን ግን ለልጆቻቸው የሚያወርሱ ናቸው።

በሙያተኞቹ ሕይወትና በሙያው የታዩ ለውጦችን ስንመለከት የሸመና ሙያና ሙያተኞች በለውጥ ላይ ናቸው። በሙያው ረገድ ድሮ ከጥጥ ምርት ኩታ፣ ነጠላ፣ መቀነት፣ ቀሚስ ሲሰሩ የነበሩ ሸማኔዎች ዛሬ ከተፈለገ ከጥጥ ብቻ ሳይሆን ከክር ሸሚዝ፣ ሱሪ፣ ፎጣ፣ የአልጋ ልብስ በመስራት ላይ ናቸው። ድሮ በባለ ሁለት መርገጫ ሸማቶ ብቻ ሲሰሩ የነበረ ሲሆን ዛሬ በተወሰነ መልኩም ቢሆን በባለ 4 መርገጫ መጠቀም ጀምረዋል። ይህ ደግሞ ጊዜ ይቆጥባል። Roberts ሙያተኞች በውድድር ለመቆየት ምርታቸውን ከፍ አድርገውና ተወዳዳሪ ሆነው መስራት እንዳለባቸው ከመከሩት ጋር የሚዛመድ ነው።

በአሁኑ ጊዜ ህብረተሰቡ በፊት ስለሙያው የነበረው አሉታዊ አመለካከት በአዎንታ በመተካት የስራቸውን ጥሩነት በማየት ከሞራል ድጋፍ እስከ ገንዘብ አውጥቶ ምርታቸውን የመሸመት ሁኔታ ታይቷል (በተለይ በማህበር የተደራጁት)። ይህንን በምልከታ አረጋግጫለሁ።

በሙያተኞች ሕይወት ላይም ከበፊቱ የተሻለ ለውጥ ይታያል። ጎበዝ ሸማኔ ከሆኑ ህብረተሰቡ የሽመና ውጤቶችን የመጠቀም ፍላጎቱ እየተሻሻለ ስለመጣ ገቢያቸው ከበፊቱ በጣም ጥሩ ለውጥ አምጥቷል። በርግጥ በሕይወታቸው ላይ ብዙም ለውጥ የሌላቸው ሸማኔዎች አሉ። ምክንያቱ ምን እንደሆነ ጠይቄ አቶ አድጎአይቼው ዳውድ የተባሉ የሽመና ሙያተኛ የሰጡት ምላሽ፡

> ላለመለወጣቸው ምክንያት አንደኛ ብዙ ልጆች ስለወለዱ ከኑሮ ውድነቱ ጋር ተያይዞ ልጆቹን ከመመገብ የዘለለ ገቢ ማግኘት አልቻሉም። ሁለተኛ ከሌላ ቦታ መጥተው ሥራ ሲጀምሩ እስኪታወቁ ስራው ጊዜ ስለሚፈልግ ያንን ጊዜ የማለፍ ከባድ ኢኮኖሚ ስላለ፣ ሶስተኛ ሲሰሩ የሚሰራውን እቃ መምቻ ያነንሱታል፣ ወይም በጊዜ አያጠናቅቁም በአጠቃላይ የብቃት ችግር

ያለባቸው ናቸው፣ ብለው አጫውተውኛል። (የካቲት 8፣ 2003፣ መሰን ብርሃን)

አቶ ደጋፍ ምስጋናው ደግሞ ነጠላ፣ ኩታ፣ ቀሚስ ሲሰሩ የድሮውን ያለጥለት (ልሙጡን) ብቻ ስለሚሰሩና የአሁኑ ሰው ደግሞ የተለያዩ ዲዛይኖች ያሉትን ልብስ ስለሚፈልግ እነሱ ይህን በደንብ ያለማወቅ ችግር ያለባቸው እንዳሉ ገልጸዋል። በተቃራኒው ከተማው ላይ ቤት ሰርተው የሚኖሩና ሰርቢስ ቤት የሚያከራዩና አሁንም ድረስ ስራቸውን የሚሰሩ አሉ። እንዲሁም ልጆቻቸውን እስከ ዩኒቨርስቲ ደረጃ የሚያስተምሩ አሉ።

በሽማ ማህበር ተደራጅተው የሚሰሩት ደግሞ ቤት የሌላቸው ቤት በመስራት ላይ ናቸው። ቤት ያላቸው በአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ቢሮ የቁጠባ ገንዘብ እያጠራቀሙ እንደሆነ የማህበሩ ሊቀመንበር አቶ ደጋፍ ምስጋናውና ከሌሎች አባላት ውስጥ ወ/ሮ እንኮይ ጌታቱ ገልጸዋል። ከዚህ የተሻለ ስራ ለመስራት ከመንግስት የገንዘብ ብድር ጠይቀው መልስ በመጠበቅ ላይ ናቸው። የሆነው ሆኖ ከወረዳው አልፈው እስከ ጎንደር እና ባህርዳር ድረስ ምርታቸውን በመሸጥ ላይ ይገኛሉ። ይህ የሚሆነው ግን በተለያዩ አውደ ርዕዮች ኤግዚቢሽንና ባዛር ሲኖር ምርቶቻቸውን ይዘው በመሄድ ይሸጣሉ እንጂ ሁሌ በስሩ ቀጥር ወደ ገበያ አይሄዱም። ምርታቸውን የሚሸጡበት ሌላው መንገድ ደግሞ የክልልና የዞን የስራ አመራር ለስራ ጉዳይ ወደ ወረዳው ሲመጡ የስራ ውጤቶቻቸውን በማስጎብኘት ብዙ ምርት እንደሚገዟቸው ከላይ ስማቸው የተጠቀሱ ሙያተኞች አውስተዋል። ሙያተኞቹ አክለውም በአሁኑ ጊዜም ምርቱን ጎንደር ድረስ ወስደው ለመሸጥ ሁኔታዎች እንዲመቻቹላቸውና መንግስት ገበያ እንዲያፈላልግ በመጠየቅ ላይ እንዳሉ ገልጸዋል።

ሙያተኞቹ ስራቸው እያደገ ገበያቸውም እየተሻሻለ መሄዱ እውን ቢሆንም የመስሪያ ቦታ እጦት፣ የመስሪያ ቁሳቁስ መግዣ ገንዘብ እጥረት እና ሙያውን የሚያሳድጉበት ስልጠና ፈልገን የማጣት ችግር እንዳለባቸው አቶ ሰዒድ ሞላ የተባሉ የሽማ ሙያተኛ ቢሮ ለ መጠየቅ ጊዜ ጠቁመዋል። ይህንንም በምልከታ ለመታዘብ ችያለሁ። እንዴት? በገንዘብ እጥረት ምክንያት ውጥን ስራዎች ሳይጠናቀቁ መስሪያ ክርና ዝሃ አጥተው

ስራው ቀጥ መመልከት ችያለሁ። በሌላ በኩል ማንቋሸሹ ተሰውጦ በአዎንታ መልኩ ተተክቶ መታየቱ ያበል የሚያስብል ነው።

## 4.4 የአንጥረኞች መስሪያ ቁሶች ስምና አገልግሎት

በዚህ ክፍል አንጥረኞች አንድን ቁስ ለመስራት የሚገለገሉባቸውን የመስሪያ ቁሶች ምንነት፣ ከምን ከምን እንደሚሰሩና አገልግሎታቸው ምን እንደሆነ ይቀርባል። የመስሪያ ቁሶቹ በምንነት ብረት፣ ቆዳ፣ ወርቅ፣ ብር፣ ቡርሽ፣ ውሃና አፈር ናቸው። Schlereth በ2.2.3.2 አተወሳሰያዊነት እና አገልግሎት፣ በ2.2.3.1 Fleming ቁስ እና አገልግሎት ያሉትን ያመለከቷል። ቀጥሎ የሚቀርበው የቁስ ስያሜና አገልግሎት ገለጻ መረጃ አቀባዮች በተተኳሪ የቡድን ውይይት ጊዜ መረጃ አቀባዮች የተስማሙበት ሃሳብ ነው።

1. ወናፍ፡- የሚሰራው ከእንጨት፣ ከቆዳ፣ ከቀንድና ከብረት ነው። ብረቱ ውስጡ ክፍት የሆነ ቱቦ ሲሆን ብረቱን በማጋል ከቀንዱ ጋር እንዲያያዝ ብረቱ በውስጥ ቀንዱ ወሰይ ሆኖ ይገጠማል። ብረቱን የማጋሉ ምስጢር ብረቱ ግሉ ወደ ቀንዱ ሲገባ ቀንዱን በማቅለጥ ስለሚገባ በቀንዱና በብረቱ የአየር መውጫ ክፍተት ስለማይኖር አየር በታለመለት መንገድ ሄዶ ለማናፈስ ይረዳል። ቀንዱና ብረቱ ከተያያዙ በኋላ ቆዳው ወደ ቀንዱ እንዲገባ ይደረግና በቆዳው ጫፍ ላይ እንጨቱ የበሰተ ከቆዳው ጋር በማያያዝ የእጅ መያዣ ይሆናል። ቆዳው ብዙ ጊዜ የፍየል ቆዳ ሲሆን እንደ ልማድ አጠራረጡ የሚጠቀሙበት ነው። ወናፍ እንዲህ ከተሰራ በኋላ የከሰል ማያያዣ በመሆን አገልግሎት ይሰጣል።

2. መጠቅለያ፡




ስዕል ተ.ቁ 11

መጠቅለያ ብረት ሲሆን ፋስ፣ ማረሻ፣ መጥረቢያ እና ገጀሞ ሲሰሩ መጠቅለያው እየተገለባበጠ የተለያዩ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ፋስ ሲሰራ ከመጠቅለያው ረጅም የቆመች ብረት አለች የጋለውን ብረት እሷ ውስጥ በማድረግ ፋስ ይጠቀለልበታል። የቆመውን ብረት ልክ እንደ ፋስ እጀታ ተጠቅሞ ፋስ ይሰራበታል። በሌላ ገፅታው ሲገለበጥ ደግሞ ማረሻና መጥረቢያ እንዲጠቀለል የተመቸ ቅርጽ አለው። ገጀሞና ሌሎች ቁሶችን ለመቀብቀብ (ለማደስ) ደግሞ በሌላ ገጽታው ይጠቀማሉ። የተለያዩ ተግባራትን የሚወጣው አንድ መጠቅለያ ገጽታው እየተቀያረ እንደሆነ ልብ ያሳል።

3. ጉጠት፡ ብረት ሲሆን አገልግሎቱ የጋለውን ብረት ወይም ብር የቀለጠበት እቃ ይዞ የሚፈለገው ቅስ እንዲሰራና ሙያተኛው ግለቱ እጁን እንዳይበላው /እንዳያቃጥለው/ ይረዳዋል። ጉጠት ትልቅና ትንሽ ያለው ሲሆን ትልቁ ፋስ፣

ማረሻ፣ መጥረቢያ ለመያዝ የሚያገለግል ሲሆን ትንሹ ደግሞ እንደ ካራ/ቢላ ያሉ ትንንሽ ቁሶችን ለመያዝ የሚገለገሉበት ነው።

4. ሞደሻ፡- ከብረትና እንጨት የሚሰራ ሲሆን አገልግሎቱ የጋለውን ብረት ጠፍጥፎ ማረሻ፣ ፋስ፣ መጥረቢያ እንዲሆን ማስፊያ፣ መቀብቀቢያና ማጠፊያ ነው። ሞደሻ ትልቅና ትንሽ ያለው ሲሆን ጉልበት የሚፈልጉ እቃዎች በትልቁ ሲሰሩ ብዙ ጉልበት የማያስወጡት ደግሞ በትንሹ ይሰራሉ።

5. ሽክላ፣ ሰም እና ውሃ ፡- ሽክላ አንጥረኛ ወርቅ ወይም ብር አቅልጦ ቀለበት እና መስቀል መስራት ሲፈልግ ሽክላ አፈር አቡክቶ ውስጡን የሚፈልገው ቅርጽ በመቅረፅ በሰም እንዲሰራና ሰሙ ሲቀልጥ ብሩ/ወርቁ የሰሙን ማህተም እንዲይዝ ያደርጋል። ውሃ ደግሞ ወርቁና ብሩ ተሰርቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ሽክላውን ውሃ ውስጥ በመጨመር ሲቀበቅዝ ሽክላውን በመፈርከስ የተሰራው ቁስ በውሃና ሉሚ እየታሸ በቡሩሽ እየተመታ እንዲነጣ ያደርጋል። የውሃ ሌላ አገልግሎት ደግሞ አንጥረኞች በተለይ ፋስ፣ ማጭድና ማረሻ በፍጥነት በመቀብቀብና በመሞረድ ቁሱን ከሰሩ በኋላ ብረቱ እንዲጠነክር በእነሱ አባባል እንዲተባ ተሰርቶ ቁሱን ከጋለ ውሃ ውስጥ ሲጨምሩት የተሰራው ቁስ ጠንካራ ይሆናል። ያልተባ ቁስ ስራ ሲሰራበት ይጣመማል ወይም ይታጠፋል። ከተባ ግን ማጭዱ በምንም አይነት እህል አይታጠፍም፣ ፋሱ በማንም እንጨት አይታጠፍም፣ ማረሻውም እንደዛው።

6. ብረት ፡- አንጥረኞች የሚጠቀሙት የተለያዩ የብረት አይነቶችን ሲሆን በዋናነት ግን ሁለት አይነት ብረቶችን ይጠቀማሉ። እነርሱም ስቲራ/ማሊስቲራ/ እና ፌሮ ብረቶች ናቸው። ስቲራ ብረት ፋስ፣ ማጭድ፣ ማረሻ፣ መጥረቢያ፣ ገጀሞ ለመስራት ሲጠቀሙባቸው፣ ፌሮ ብረቶች ደግሞ ካራ ለመስራት ያገለግላሉ። እዚህ ላይ ብረት የሚቆረጡበት መቁረጫ መኪያ መንሳት ይገባዋል። መቁረጫው ብረት ሲሆን ተቆራጩም ብረት ነው። መያቶቹ ብረት በብረት ይቆረጣል ይላሉ። መቁረጫ ብረቱ ስል ነገር ሆኖ ከላይ መምቻው ደንዳ ያለ ሲሆን ወገቡ ላይ የሚታሰር ቀጭን

ብረት ያለው ሆኖ መምቻው ቀጥ ብሎ እንዲቆም መያዣ ነው። በእጅ ይያዝ ቢባል እንድም የሚግለው ብረት የያዘን እጅ ይፈጀዋል፤ እንድም በመደሻ ሲመታ ብረቱን መደሻ የሚቀበቅበው ሰው ተሳስቶ ብረት የያዘውን ሰው እጅ ሊመታው ስለሚችል መያዣ ብረቱ ያስፈልጋል። ቀጥሎ መምቻው ከሸቦው ከቦ በኋላ ስቴሪው ይግልና በተፈለገው ቅርፅ መምቻው ቁሞበት እንዲመታ ይደረጋል። ብረቱ ይግልና በመምቻው እየተመታ ተቆርጦ ለሚፈለገው አገልግሎት/ጥቅም ይውላል።

7. ወርቅና ብር፦ ብርና ወርቁ የሚገኘው ወርቅና ብር የሚያሰሩ ሰዎች ከተለያየ ቦታ አግኝተው የሚያመጡ ሲሆን አንጥረኞች ማርትሬዛ ብር ገዝተው በማቅለጥ የብር መስቀልና ቀለበት ይሰሩታል። አሁን ግን የለም ምክንያቱም ነጋዴዎች እያሸረቱ ስለሚሸጡት ውድ ሆነ ዛሬስ ከናካቴው ጠፍቷል በማለት በአንጥረኝነት ሙያ የሙተዳደሩት አቶ ፍቃዱ ዮሐንስ ገልጸዋል። የእቃው ጆሮ ሲሰበር ቀላጥ ጠብ አድርገው በመጠገን ወደ ድሮው አገልግሎት ስለሚመለስ ቀላጥ ማጣበቂያ የሙያተኞቹ አንድ የመስሪያ ቁስ ነው።

## 4.5 በአንጥረኞች የሚሰሩ ቁሶች አሰራር እና ተግባር

በዚህ ርእስ ስር የሚሰሩት ቁሶች የአሰራር ሁኔታን በቅደም ተከተል፣ ሁሉም የመስሪያ ቁሳቁስ በሙያተኛው ሆኖ የሚሸጡበት ዋጋ፣ሲታደሱ (ሲቀበቀቡና ሲሞጠሞጡ) የሚኖራቸው ዋጋ የሚቀርብበት ሲሆን በተጨማሪም ቁሶቹ ለምን ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ ይጠቀሳል። ሙያተኞቹ ከሚያከብሩት የበዓላት ቀን ውጭ ቁሶቹ ሲሰሩ የተለየ ቦታና ጊዜ ሳያስፈልጋቸው ይሰራሉ። ከቁሶቹ ሁሉ የወርቅ ስራ የተለየ ጊዜና ቦታ ይፈልጋል። ወርቅ ማታ ወይም ሊነጋጋ ንህ ሲቀድ ይሰራል።

ወርቅ ሲሰራ አንጥረኛው ብቻ ገብቶ ቤት ዘግቶ ይሰራል። ከሙያተኛው ውጭ ማንም እንዲገባ አይፈቀድም። ምክንያቱ ምንድን ነው ብየ በአንጥረኝነት ሙያ የሚተዳደሩት አቶ ፍቃዱ ዮሐንስ እንዲህ ገልጸውታል። "ወርቅ ሲሰራ ማንም የሚገባ ማንም የሚወጣ ከሆነ ጥላ ይወጋና ወርቁ ጥሩ ሆኖ አይሰራም።" (ጥር 18፣ 2003፣ ደረስጌ)

አቶ ሹሙት አዱኛ(ባህልና ታሪክ አዋቂ) የተባሉ መረጃ አቀባይ ከላይ ለአቶ ፍቃዱ ዮሐንስ የቀረበውን ጥያቄ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ፡-

እነሱ (አንጥረኞች) ወርቅ ሲሰሩ ከነሱ ውጭ ሌላ ሰው እንዳይገባ የሚፈልጉት ጥዓአይነት እንዳይሆን በሚል ነው። እኔም ግን ከዚህም ሌላ ምክንያት ያለ ይመስለኛል። ትኩረት እንዳያጡ ስለሚፈልጉ ነው። ማንም መጥቶ የሚያወራቸው ከሆነ ሃሳባቸው ተበታትና ወርቅ ሊባክን ይችላል፤ ወይም ስራው ተበላሽ ይሆናል። ሁለተኛው ምክንያት ጥበባቸውን ማንም ሰው እንዲያየው ስለማይፈልጉ ነው። (ጥር 26፤ 2003፤ መስበርሃን፤)

ከላይ አቶ ሹሙት አዱኛ ሃሳባቸው ከተበታተነ ስራው ስለሚበላሽባቸው ያሉትን እኔም በምልከታ ወቅት ለመታዘብ ችያለሁ። የአንጥረኝነት ሙያተኛው ፍቃዱ ዮሐንስ የመስቀል አሰራር ሲያሳዩኝ የመስቀሉ ግራና ቀኝ ገጽ ተዛንፍ ሆኖ ወጥቷል። ለምን? ትኩረታቸውን ስለሰረቅኩባቸው ይመስለኛል። ቢሆንም ሳልጠይቅ አሰራሩን ስጠይቅ በትክክል ሊሰሩ ተመልክቻለሁ።

## ፋስ

ፋስ የሚሰራው ከስቲል(ባሊስትል) ብረት ተጠምዝዞና ተጠፍጥፎ ነው። ስቲሉውን በእሳት በማጋል ብረቱ በደንብ ሲግል በጉጠት በመያዝ በመቀጥቀጥና በመጠምዘዝ ይሰራል። ስራው የሌላ ሰውን እርዳታም ይሻል። አንጥረኛው ባንድ እጁ የጋለውን ብረት ይዞ በሌላ እጁ ተጥን ሹሉ ይዞ የሚሰራውን ብረት እያመለከተ ከዚህ ላይ ምታ፤ ከዚህ ላይ ምታ በማለት ሲጠቁመው መዶሻ የያዘው የሙያተኛው ረዳት ደግሞ ምታ የተባለው ላይ እየመታ እየጠፈጠፈ ስራው ይሰራል። የፋሱን ጆሮ ለመስራት ሲጠመዘዘውም ብረቱን ያግልና "ሀ" ቅርፅ ብረት አለ ስሙ መጠትለያ ይባላል፤ ሙያተኛው የሚሰራውን ፋስ ከመጠትለያው አስገብቶ በመዶሻ ሲያስመታው ብረቱ ተጠምዞ ይያያዛል።

እንዳንድ ጊዜም የአይሱዙ መኪና ስቲሪባሊስትሩ ጆሮውን እንዳለ በመጠቀም ሌላውን ጠፍጥፎ ስለት አውጥቶ በመስራት አዲስ ፋስ ይሰራል። ትልቅና ትንሽ ፋስ ስላለ

ዋጋው ላይም ልዩነት አምጥቷል፤ ትልቁ ፋስ አምሳ እና አርባ ብር ሲሸጥ፤ ትንሹ ደግሞ ሃያ ብር ይሸጣል።ፋስ አዲስ ከመሰራት በተጨማሪም ስለቱ ሲደመዱም እየተቀበቀበና እየተሞረደ ስለት ይወጣለታል። ስለት ሲወጣለት ለአድሳት አራትና አምስት ብር ያስከፍላል።

## መጥረቢያ

መጥረቢያ ሲሰራ ስቲራው በፍላት ተቆርጦ፤ ብረቱ እየጋለ ይጠፈጠፋል፤ አሁንም እንደገና ይጠፈጠፋል፤ ከዚያ ቀጥሎ በመጠቅለያ ተጠምዝዞ የእንጨት ማስገቢያው ይሰራል። መጥረቢያ ትልቅና ትንሽ አለው። ትልቅ ለሚፈልገው ትልቅ፤ ትንሽ ለሚፈልገው ትንሽ ይሰራል። ትልቅና ትንሹ እንደ አሰሪው ፍላጎት ነው፤ ማረሻ የሚያክል መጥረቢያም አለ። ለመስማማት ያህል ግን ትልቅና ትንሽ በሚል ወስጄዋለሁ። ሲሰራም አንድ ስቲራ አራት መጥረቢያ እንዲሆን ተደርጎ የሚቆረጥ ሊሆን እንዳንዱ ከፍና ዝቅ ሊል ይችላል። መጥረቢያ ሲጠቀለል ትልቁ አምሳ ብር፤ ትንሹ አስር እና አስራ አምስት ብር ይሸጣል።

መጥረቢያ ሲታደስ (ቅብቀባ ይባላል) በእሳት ከጋለ በኋላ በትንሹ መታ መታ እየተደረገ ስለት ይወጣለታል። ዋጋው ትንሹ ሁለት ብር፤ ትልቁ ደግሞ አምስት ብር ይቀበቀባል። ድሮ ግን መጥረቢያ የሚታደሰው ማረሻ ለማሰራት የሚመጣ ሰው እንደ ምራቂ ያለ ክፍያ ነበር። የዚህን ምክንያት ያስረዱት አንጥረኛ ደሴ አየልኝ ሲሆኑ ሃሳቡን ሲያብራሩ፡-

> መጥረቢያ ሳድስ ስቀበቅብ ምራርጄ ለመስጠት እንደ መጥረቢያው ትንሽና ትልቅ ቢለያይም እንደዚዉ ሂጃለሁ። የኑሮ ውድነት ስላለ ድሮ መጥረቢያ ከማረሻ ጋር መጥቶ እንደ ምራቂ ነው ሰርቼ የምሰጠው። አንድ ማረሻ ካምጠምጣኩ ሁለት ሶስት መጥረቢያ በነፃ አምጠመጥ ነበር። ዛሬ ግን ከከሰል ውድነት አኳያ ዝቅ ያለሽውን ትንሹን ሁለት ብር ይደፈጋል። ከፍ ያለው አምስት ብር ይምጠመጣል። በማለት ምክንያታቸውን ገልፀዋል። (የካቲት 3፣ 2003፣ ድልድሊት)

### ማረሻ

አዲስ ማረሻ ሲሰራ ብዙ ጉልበት የሚፈልግ ሲሆን ሲሰራ ባሊስትራው ብረት ተቆርጦ በፊት በኩል የጦር ቅርጽ ተቀርጾ ይወጣለትና እየጋለ ያንን ቅርጽ እንዲይዝ ስለት ይወጣለታል። ማረሻ ለመስራት ሲፈለግ በአንድ ሰው ብቻ አይሰራም፤ በተለይ እየጋለ ሲሳብ ሲጠፈጠፍ፡፡ ሲሳብ ሲጠፈጠፍ ብዙ ጉልበትና ጊዜ ይፈጃልና፡፡ ከዚያ ብረቱ እየጋለ በመጠቅለያ ይጠመዘዝና ማረሻ ይሰራል። አንድ ማረሻ ትልቅ ከሆነ አንድ ኪሎ ብረት ሲወስድ ትንሽ ከሆነ አንድ ኪሎ ብረት ሁለት ማረሻ ይሆናል።

አንድ ጥሩ ማረሻ ተሰርቶ አምስት እና ስድስት ዓመት ያገለግላል። ታዲያ በአመት በአመት ይታደሳል። አዲስ ማረሻ ሲሰራ ትልቁ 110 እና 120 ብር ሲሸጥ ትንሹ ደግሞ ስልሳ ብር ይሸጣል። ሲታደስ ደግሞ ከአስር እስከ አስራ አምስት ብር ይሞጠሞጣል። ልዩነቱ እንደ ስለቱ መሞትና የተሻለ መሆን ነው። አንድ ሙያተኛ በቀን ቢያንስ ሶስት ማረሻ እና ሌሎች ተጨማሪ ቁሶችን ቅብቀባና ሙጥሞጣ ይሰራል። ማረሻ ለገበሬና ለሙያተኛው የሕይወት ወይም የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ ሲሆን ከእነሱ ውጭ ላለ ግን ቁስ ነው። የግንዛቤውም ገበሬው መሬቱን በማረሻ አርሶ ኑሮውን ስለሚገፋ፤ እንጥረኛውም ማረሻ ሰርቶ ገቢ ለማግኘት ስለሚለፋ ከቁስ የሰፋ ትርጉም ይሰጠዋል። Schiereth ተሰምሮበት፤ Fleming እና Prown ትርጓሜ ብለው በምዕራፍ ሁለት የቀረበውን ልብ ይሏል።

### ካራ/ቢላ

ካራ ሲሰራ እንደ ሌሎቹ ስቲራ ብረት ብቻ ሳይሆን ከርፈዝ ራሱ፣ ፌሮ ብረት እና ሌሎች ቀጫጭን ብረቶችም ለካራ መስሪያነት ያገለግላሉ። አሰራሩ ብረቱ ይግልና እየተጠፈጠፈ ቅርጽ ወጥቶለት ይሰራል። ካራ እንጥረኛው አዲስ ጠቅልሎ ከሰራው ትልቁ አስር ብር፣ ትንሹ አምስት ብር ይሸጣል፤ ሲታደስ ደግሞ ለአንድ ካራ አንድ ብር ያስከፍላል። እንደ አገልግሎቱ ለስጋ መክተፊያ ሲሆን ከፍ ያለ ካራ ከሆነ አጥንት ለመከትከት ያገለግላል።

## ክርፋዝ




ስዕል ተ.ቁ 12

ክርፋዝ የማረሻ ማገናኛ ሆኖ የሚያገለግል ብረት ነው። ሲሰራ ስቲራው ብረት በቀጭኑ ተቆርጦ በእሳት በደንብ እስኪፈላ ድረስ ግሉ ብረቱ እርስ በርስ በፍላት እንዲገጥም ይደረጋል። ከቁሶቹ ሁሉ ብረቱ እስኪቀልጥ የሚግል ክርፋዝ ብቻ ሲሆን ፍላት በጣም ይወዳል። ሌላው ቁስ ሲግል የሚጠፈጠፍ ነው። ክርፋዝ ፍላት መውደዱ ብቻ ሳይሆን አገልግሎት ከሰጠ በኋላ እስመታደሱ ከሌሎቹ ቁሶች ለየት ያለ ጠባይ እንዲኖረው አድርጎታል። ክርፋዙ ቢሸረፍ ወይም ቢቆረጥ ካራ ይሆናል እንጂ እንደገና ክርፋዝ ሆኖ አያሰራም። ምክንያቱም እንደገና ፈልቶ እንዲገጥም ለማድረግ ስለማያስቸግር ነው። ክርፋዝ እስከ ፃያ ብር ይሸጣል።

## ማጭድ

ማጭድ ሲሰራ መጀመሪያ ስቲራው ብረት በሚፈለገው መጠን ይቆረጣል። የተቆረጠው ብረት በፍላት የደጋን ቅርጽ እንዲይዝ ይደረጋል። ቀጥሎ በደጋን ቅርጽ የተሰራው ብረት በእሳት ከፈላ በኋላ መከተፊያ ነገር ትንሽ ብረት አለ፤ በእሱ እየተከረከረ ጥርሱ ይወጣል። ጥርሱ ከተወጣ በኋላ የተሰራው ማጭድ ጠንካራ እንዲሆን ማትቢያ ከውሃ ላይ ጨው ተጨምሮ ማጭዱ ይነከርና ለስራ ይዘጋጃል። አንዳንድ ሙያተኞች ማትቢያ ውሃ ብቻ መሆን አለበት ይላሉ። ምክንያቱም ጨው በስራ ጊዜ እንዲሰበር ያደርገዋል

ይላሉ። ማጭድ ማትቢያ የሚያደረግበት ምክንያት ያለ ማትቢያ የማጭዱ ብረት እርጥብ ሊሆን ስለሚችል እህል ወይም ሳር ሲታጨድበት የጥርሱ ስለት ሊጣመም (ሊታጠፍ) ይችላል። ሲተባ ግን ሲታጨድበት ጥሩ እጨዳ ያሳጭዳል። ስለ ማትቢያ አቶ ምሲጋናው ፍቃዱ የሰጡውን ሃሳብ ሲገልጹ፤

> ትባት ውሃ ያስፈልገዋል። በውሃ እተባዋለሁ ሲተባ ጥርሱ ያጠነክራል፤ አይታጠፍም። የብረት ትባት ሲባል ብረቱ ለስላሳ ሆኖ ሲነኩት እጥፍ የሚል ውሃ ደንቶ አድርጎ አፍልቶ ሲያበቁ በውሃ ከነከሩት ይደርቃል። ሲደርቅ እህል ወይም ሳሩ ቢያይሰው እንኳ መሰበር እንጂ አይታጠፍም። ሳይተባ ከቀረ ግን እነዛ የጠበቁት ጥርሶች ራሱ እህሉ ያጥፋቸዋል።በማለት ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል። (ጥር 29፣2003፣ ደረሰኝ)

ማጭድ ሲሰራ ከሃያ እስከ ሃያ አምስት ብር ይሸጣል። ሲታደስ ጥርሱ ያለቀ ማጭድ ተቀጥቅጦ እንደገና ሌላ ጥርስ ይወጣለታል። የሚታደሰው ማጭድ በአካባቢው ሙያተኛን የሚሰራውንና ከመንግስት የሚመጣውን በተለምዶ አብራራው የሚባለው ማጭድ ነው። ሁለቱም ዓይነት ማጭድ በመከትፈያው ተከትፎ ጥርስ ይወጣለትና ታድሶ እንደገና አገልግሎት ላይ ይውላል። ማጭድ ሲታደስ በስምንት ብር ነው።

ገጀራ

ገጀራ ለሲጋ፣ ለሌሎች ነገሮች መቁረጫ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን የሚሰራውም ስቲራ ብረቱ ገሉ፣ ተቀጥቅጦ፣ ስለት ወጥቶለት ይሰራል። ገጆሞ አሰራሩ እንደ ገጀራ ሲሆን አገልግሎቱ ጉቶ እንጨት ለመከትከትና ለመመንጠር ነው። ገጀራ ሲሰራ እስከ አስራ አምስት ብር ይሸጣል፤ ሲታደስ ደግሞ አምስትና ስድስት ብር ያስከፍላል። ገጀራ ደግሞ ሲሰራ ሃያ ብር የሚሸጥ ሲሆን፣ ሲታደስ አምስት ብር ያስከፍላል።

የቁሱ ትልቅና ትንሽ መሆን ብቻ ሳይሆን የእቃው መሳላትና ያለመሳላት ነገርም የማደሻ ዋጋው እንዲለያይ ያደርገዋል። አንዳንዱ ቁሱን ብዙ ሳይመታ ያመጣዋል ትንሽ ክፍያ ይጠየቃል። ሌላው ቁሱን በጣም አስነድቶ ያመጣዋል የማሳደሻ ዋጋውን ከፍ አድርጎ

ክፍሉ ይመስላል። ስለሆነም ዋጋ የሚወጣለት ቁሱ ታይቶ እንጂ ትልቅና ትንሽ ወይም ወፍራምና ቀጭን በሚል ውጫዊ እይታ ብቻ መሰረት በማድረግ አይደለም። ፊት ለፊት ታይቶ እንደ ጉዳቱ መጠን ተመን ይወጣለታል።

ድባብ




ስዕል ተ.ቁ 13

ድባብ ሲሰራ የብር መስቀል፣ ከፋይ ጨርቅ፣ ዙሪያ ብር ተሳሳይ ኮዳ (ቆርቆሮ) ያስፈልጋሉ። እንዲሁም 1ኛ ጥቁር ከፋይ፣ 2ኛ ቀይ ከፋይ፣ 3ኛ ሰማያዊ ከፋይ አገልግሎት ላይ ይውላሉ።

ከድባቡ ላይ የሚደረገው መስቀል ብዙ ጊዜ የብር መስቀል ሲሆን የወርቅ መስቀል ውድ ስለሆነ ብዙ ጊዜ በሙያተኞቹ አይሰራም፣ አገልግሎት ላይም አይውልም። የብር መስቀሉን እንደአስተምህሮታቸው አሰራሮቹ ወይም አንጥረኛው ሊያቀርብ ይችላል። የድባቡ መስቀል ማስቀመጫ በድባቡ የላይኛው ክፍል ይቀመጣል፣ የብር ማጣበቂያ ቁስ አለ ኮዳ ይባላል በእሱ ይጣበቃል። ይህ የድባቡ የላይኛው ክፍል ሆኖ በአንድ ተገጣጥሞ ይሰራል። የታችኛው ክፍል ደግሞ የተለያዩ ከፋይ ጨርቆች እየተሰካ ተቆርጦ ማራኪና ሳቢ እንዲሆን ተደርጎ በተለያዩ ቀለሞች ተከፋፍሎ ይሰፋል። ከከፋዩ ጨርቅ ላይ የተደገበለው ቆርቆሮ በብርና በወርቅ ቀለም ተቀብቶ በዙብ፣ በአራት ማዕዘን፣ በጦር እና በመስቀል ዲዛይን ዙሪያው ይተከልበታል። እንዲሁም በበለጠ እንዲያምር ሁለት ወይም

ለስት ዙር አሚዎች ይሆንቢታል። ያለ አሚዎች ውበት አይኖረውም ሽል ይላል ወይም ይቀላል ይባላል። የአሚዎቹ ጥቅም ድባቡ ግርማ ሞገስ እንዲኖረው ማድረግ ነው። በውስጡም መዘርጊያ እንጨት ይተከልለታል። ከዚያ በኋላ የድባቡ የላይኛው ክፍል የሆነው መስቀሉ በደንብ ተከልቶ ይመጣና ከታችኛው የድባብ ክፍል ጋር ይተከላል ድባቡ ሙሉ ሆኖ ተሰራ ማለት ነው። አገልግሎቱ የዓመት በዓል ከበራ ሲኖር ለካህናት የሚዘረጋ እንደ ጥላ የሚያገለግል ሲሆን ከወርቅ ጥላ የበለጠ ሞገስ አለው። Schlereth ባህርይ አመልካችነት ያሉትን ልብ ይሏል። መስሪያ ቁሱ ሙሉ በሙሉ በሙያተኛው ሆኖ ዋጋው 2000 ብር ይሸጣል። ነገር ግን ለታቦት ነው በሚል ሲከራከሩ 500 ብሩ ተቀንሶ በ1500 ብር ይሸጣል።

## ድሪ

ድሪ ሽቦ ስለሆነ ይላባል፣ ይሉጠማል፣ ይረዝማል። በመቀስ እየተቆረጠ እየተደነበለ (ጌጥ እየወጣለት) ማጣበቂያ አለ እየተጣበቀ ይሰራል። ድሪ የአንገት ጌጥ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ከማንነቱ ባሻገር ደግሞ የእናቴ፣ የአባቴ "ቆሌ" ድሪ አለኝ ተብሎም ድሪ የሚያስሩ ሰዎች አሉ። ድሪ ቀደም ባሉት ጊዜያት ለስት መንታ ድሪ ከአስራ አምስት እስከ ሃያ ብር ይሸጥ ነበር። አሁን ሰው ጭራሽ አይፈልገውም። ምክንያቱም አንድም የአሁኑ ትውልድ መጠበቂያ እና ቆሌ ከሚባሉ ነገሮች ጋር በተያያዘ ስሙ እንዲነሳ ስለማይፈልግ፣ አንድም የእቃው ተጠቃሚዎች ፊውዳሎች ስለነበሩ አሁን ፊውዳሎች ስለሌሉ የእቃው ተጠቃሚ ሊቀንስ ችሏል። Schlereth አካባቢያዊነት ያሉትን ልብ ይሏል።

## ጠልሰም

ጠልሰም ሲሰራ ብሩ ይጠፈጠፋል፣ ብሩ እየተጠፈጠፈ ይቀረፃል፣ እየተቀረጸ ጌጥ የሚያወጣ መንደፊያ አለ በመንደፊያው ጌጥ ይወጣለታል። ከዚያ እየታተመ ይጣበቃል። ጌጥ ማውጫው አራት ማዕዘን፣ ወይም ክብ ሊሆን ይችላል። በማተሚያው እየታተመ ከተሰራ በኋላ ኮለቶ(አስውቦ) ለባለቤቱ ማስረከብ ነው። ብሩ ከሙያተኛው አልፎ አልፎ ከአሰሪው በኩል ሊመጣ ይችላል።

አገልግሎቱ ሙሽሮች በተዳሩ ጊዜ የሙሽራይቱ የአንገቷ ጌጥ ነው። ሙሽራይቱ ካሰረች በኋላ ሚዜዎቹ አስረው እስይ የምስራች እያሉ መንደሩን ሁሉ ይዞራሉ። Schlereth ባህላዊነት ካሉት ቲምሬ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው።ዋጋው አስራ አምስት ብር፣ አስራ ሁለት ብር፣ እና ስድስት ብር የሚሸጥ ሲሆን ዋጋው እንዲለያይ ያደረገው የጠልሰሙ አይነት ነው። በስኖፍጭ በትናንሽ ምስር ምስር የሚመስሉ ጌጦች የሚሰራ አለ፣ አሰራሩ ከበድ ይላል፤ ዋጋው አስራ አምስት ብር ነው። ወርቅ ቅብ የሚባል አለ፣ ዋጋው አስራ ሁለት ብር ሲሆን የሚቀባው ወርቅ የሚመስል ቀለም እንጂ ወርቅ አይደለም። እንዲሁም ዝም ብሎ ተራ አለ በመንደፊያ እንደ ማህተሙ አንድ ጊዜ ቦግ ተደርጎ በመንደፍ ነገ ወጥቶለት የሚሰራ ሲሆን ዋጋው ስድስት ብር ይሸጣል።

አንዳንድ ሙያተኞች ደግሞ የጠልሰም ዓይነቶችን ባለሁለት፣ ባለ ሶስት እና ባለ አራት ማዕዘን፣ እንዲሁም ሸንበቆ የሚባሉ የጠልሰም ዓይነቶች እንዳሉ ገልጸዋል። ሁለት ማዕዘን የሚባለው የአንበሳ ጥርስ ያለበት ነው። አሰራሩ ብሩ ብቻውን አልያም በወርቅ ንክር ይሰራል።

## እልቦ

እልቦ ብር ሲሆን ይቀልጣል፣ ሲቀልጥ መስቢያ አለ የሚልገው ይላጋል፣ ይሳባል። እየተከነተረ ቅርጽ ይወጣለትና ማተሚያ አለው እየታተመ ይሰራል። እልቦ አገልግሎቱ የእግር ጌጥ ሲሆን ዋጋው ድሮ ባልተወደደ ጊዜ ስምንት ብር ነበር። አሁን ከአምሳ ብር በላይ ይሸጣል። አሁን በጣም ውድ የሆነበት ምክንያት ብር መጥፋቱ ነው። ብር ነጋዴው እየሰራ ሊሸጠው እስከ ሁለት መቶ ብር ስለገባ ብር መግዣ ዋጋው ተወደደ።

## ወለባ

ሽቦ፤ በደንብ ዲዛይን ወጥቶላቸው ሽቦው ዞሮ አንድ ጌጥ ይሆናል። እንደገና ከሽቦዋ በላይ አንድ ሌላ ነገር ይሰራል። እንደዚያ ሆኖ እንደ ኳት ይሰራል። ኳት ከተሰራ በኋላ ትንሽ መስቀል ይደረግበታል። ግራ ቀኝ ካሉ ደግሞ ነጥብ ነጥብ ጌጣጌጥ አለው። ወርቅ ቅብ ነውና ይብለጨለጫል። አገልግሎቱ የሴቶች ፀጉር ጌጥ ነው። ከሴቶች የፀጉር

ጌጥንት በተጨማሪ ፀጉራቸውን አይነት እንዳይበላው መጠበቂያም ነው። ዋጋው ድሮ ርካሽ ሳለ ስድስት እና ሰባት ብር ይሸጥ ነበር። ዛሬ ደግሞ ወደ አምሳ ብር ይሸጣል።

## ዶቃ

ዶቃ ከበቅሎ አንገት አካባቢ የሚደረግ ጌጥ ነው። ዶቃ ሲሰራ ከቆርቆሮና ከቆረንጮ ሲሆን ቆርንጮው ተሰክቶ በውስጥ በኩል ይሆንና በቆረንጮው እኩል ቆርቆሮ ተቆርጦ በላይ በኩል ይሆንና በትንሽ ምስማር ይመታል። ውበት እንዲኖረውም አጫዋች ይለፋለታል። አጫዋቹ የሚሰራው ዝርጉ ቆርቆሮ እየተደነበለ ቅርጽ ወጥቶለት ነው። የቆዳው አገልግሎት ቆርቆሮው ፎርም እንዲይዝና እንዳይታጠፍ ሲሆን እንዲህ ምቹ ሆኖ ስለሚሰራ በቅሎው እንደፈለገው ሆኖ ይሄዳል። የዶቃ አገልግሎት የበቅሎ መሸለሚያ ማእረግ ሲሆን ዋጋው አምሳ እና ስልሳ ብር ይሸጣል።

## ብር

ብር (ቀለበት፣ መስቀል) ሲሰራ አሰራሩ ከወርቅ ስራ ጋር ተመሳሳይ ነው። ብሩ ወይም ወርቁን በእሳት በማቅለጥ መስቀል እና ቀለበት ይሰራል። የብር እና የወርቅ መስቀል ወይም ቀለበት ሲሰራ የሚከተሉትን ሂደቶች ያልፋል። መጀመሪያ ሸክላ አፈር ወይም ዋልካ አፈር ይመጣና በውሃ ተለውሶ የሚሰራውን ቆስ ቅርጽ ይዞ ይሰራል። ከጭቃው ውስጥ የሚሰራው ቆስ ቅርጽ በሰም ተቀርጾ ይገባል። ጭቃው በፀሀይ እንዲደርቅ ይደረጋል። ጭቃው ከደረቀ በኋላ የደረቀውን ጭቃ እሳት በማስመታት ተቀርጾ የገባው ሰም በሙቀት ቀልጦ እንዲወጣ ይደረጋል። ሰሙ ሙሉ በሙሉ ከወጣ በኋላ የቀለጠው ብር ወይም ወርቅ ሰሙ በነበረበት መዝገብ ሙሉ በሙሉ ሄዶ እንዲገባ ይደረጋል። እንዲህ ከተሰራ በኋላ የደረቀው ጭቃ ውሃ ውስጥ ይነከራል። ምክንያቱም ብሩ ወይም ወርቁ እንዲቀዘቅዝ ነው። ቀጥሎ የተነከረው ጭቃ ሲፈረከስ የተሰራው ቆስ የሰሙን ቅርጽ ይዞ መስቀል ወይም ቀለበት ሆኖ ይወጣል። ከዚያ ቆሱ እንዲያበራ/እንዲያንጸባርቅ ሲባል በሎሚና በውሃ እየታሸ ይኮላል። በደንብ ሲያንጸባርቅ ስራው ይጠናቀቅና የተሰራን ቆስ ባለቤቱ ይረከባል።

ወርቅ ከብር ስራ የሚለየው ወርቅ ከቀለጠ በኋላ በደንብ እንዲበጠበጥ የሚረዳ ማይትናር የሚባል መርዝ ተጨምሮ እንዲዋሃድ ይደረጋል። መርዙ በአሁኑ ጊዜ አገልግሎት አይሰጥም። መርዙ በውሃ የሚበጠበጥ ሲሆን ሰውም ሆነ ከብት የመግደል

እቅም አለው። ወርቁን በደንብ ስለሚበላው ወደ ፈሳሽነት ለመቀየር ይረዳል። ብር ስራው ላይ ማይትናር አይጨመርበትም፤ እሳቱ ብቻ በደንብ ያቀልጠዋልና።

ብር ብቻውን ወርቅም ብቻውን እንዴት እንደሚሰራ ከላይ በዝርዝር ቀርቧል። አሁን ደግሞ ብር የወርቅ ቅብ ስራን እንመለከታለን። እንጥረኛ ፍቃዱ ዮሐንስ ብር የወርቅ ቅብ እንዴት እንደሚሰራ እንደሚከተለው አስረድተዋል።

> ብሩ ከተሰራ በኋላ ወርቁ በእሳት ይቀልጥና ከቀለጠ በኋላ ከሜርኩሪ ጋር በማዋሃድ ብሩ ይቀባል። መቅቢያው ማንም እቃ ሳይሆን ከመዳብ የተሰራ አጭር ቁመት ያለው ሽቦ ነገር ነው። ይህ መዳብ ወርቁን እንደ ማግኔት ይዞ ሳያንጠባጥብ ስለሚያነሳው በመዳቡ ይቀባል። ያለዚህ የመዳብ እቃ ላንሳው ቢባል ወለል ወለል ስለሚል አይነሳም። በመዳቡ ግን ወርቁን አንስተን ብሩን እንቀባዋለን። ከተቀባ በኋላ እንደገና በእሳት ይበላል። ከተጠበሰ በኋላ ሲነካ ያምራል። ወርቁም አይለቅም። ብር ወርቅ ቅብ የሚሰራው እንደዚህ ነው። (ደረስጌ፣ ጥር 28፣ 2003)

ዋጋው ብር ከሆነ ከአምሳ ብር ጀምሮ ይሸጣል። እንደ ብሩ መጠን ይለያያል። ወርቁ ግን 18 ወርቅ የሚያመጡት ባለቤቶቹ ስለሆኑ ሰራዎቹ የሚጠይቁት የእጅ ዋጋ ነው። ከ100 ብር ጀምሮ ያስከፍላሉ። ዋጋው እንደሚሰራው ቁስ ትልቅነትና ጌጣጌጥ ብዛት የተለያየ ዋጋ ሊመጣለት ይችላል።

## 4.6 የእንጥረኞች ሕይወት

ሙያተኞቹ ድሮ ፍፁም መጥፎ በሚባል ደረጃ ይገለሉ የነበረ ሲሆን በብዙ መልኩ ማህበራዊ ተሳትፎቸው የተገደበ ነበር። ጽዋ አብረው አይጠጡም፤ ጋብቻ ከጨዋው ጋር መጋባት በጭራሽ አይችሉም ነበር። ለዚህ በምክንያትነት የሚሰጠውን ሃሳብ እንጥረኛ ደሴ አየለኝ ሲገልጹ።

> አሹሙር ይናገሩኛል። አንጥረኛ የሆኑ ሁሉ ቤተ እስራኤላዊ ናቸው ማለታቸው ይመስለኛል። ቤተ እስራኤላዊ ከሆነ "ቡዳ" ነው ብለው ስለሚያስቡ ጸዋ አብረው አይጠጡም፤ ጋብቻ ጨዋ ነን ከሚሉት ጋር መጋባት ይከለከሉ ነበር። እቃ ማሰራት ሲፈልጉ ግን የሚመርጡት ቤተ እስራኤላዊ የሆኑትን ነው። ምክንያቱም እነሱ የሚሰሩት እቃ ጥሩ ስለሆነ ለረጅም ጊዜያት በጥራት ያገለግላል። እንዲያውም 'የማረሻው ስለት አይበርድም' በማለት ህብረተሰቡ ከሩቅ አካባቢ ተነስቶ ቤተ እስራኤላውያንን ፈልገው ይመጣሉ። እኔ ራሴ ቤተ እስራኤላዊ አይደለሁም። ግን እኔ የሊጃለም አስረስ[5] ሚስት የእህት ልጅ ስለሆንኩ ቤተ እስራኤላዊ እንደሆንኩ አስበው ከሩቅ አገር ሊያሰሩ የሚመጡ አሉ። ሰውየው እስራኤል ስለሄደ ነው። እኔ ግን አይደለሁም። የቤተ እስራኤሎች እጃቸው ጥሩ ነው፤ ማረሻው ስለቱ አይበርድም ይሉኛል። አዎ ጥሩ እንጂ አላቸዋለሁ። (ጥር25፣ 2003፣ ድልድሊት)

> በተቀራኒው በማህበራዊሕይወቴ ከጥንቱ አንጻር ለውጥ አለ ግን አሁንም ተጽዕኖ ይደረግብኛል። አንድ ጸዋ እየጠጣን ይህ መጤ፣ ፈላሻ፣ ካይላ አገራችን መጥቶ አለፈለት ይሉኛል። መስሏቸው እንጂ እኔ አገሬ ነው። ይህንን ስራ ድሮ ይሰሩ የነበሩት እስራኤሎች ስለሆኑ በርግጥ አሁን አሁን ጸዋ አብረን እንጠጣለን ነገር ግን ቡዳ፣ ፈለሻ፣ ካይላ፣ መጤ እያሉ አሹሙር መሳደባቸው አሁንም አልቀረም በማለት አስረድተዋል። (ጥር 25፣2003፣ ድልድሊት)

በማህበራዊ ሕይወታቸው ላይ በሚደርስባቸው ተጽእኖ አንጥረኞችን በሁለት ከፍሎ ማየት የሚቻል ሲሆን ወርቅ፣ ብር፣ ድባብና ሌሎች ጌጣጌጥ የሚሰሩት ማረሻ፣ ፋስና

[5] ሊጃለም አስረስ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ዘንድ ባለ ጸጋ ከሚባሉት ውስጥ የሚካተት፣ እስራኤል አገር የሚኖር ሰው ነው

ማጭድ ከሚሰሩት በተሻለ ተቀባይነት ያላቸውና ብዙ ተፅእኖም የሌለባቸው ሲሆን ጋቢም ከፈለጉት ጋር ይፈፅማሉ፣ ፅዋ ያለ ተፅእኖ ይጠጣሉ። ሲጠሩም ወርቅ ሰሪ ተብለው ይጠራሉ። ይህ የሆነበትን ምክንያት ፍቃዱ ዮሐንስ የተባሉ መረጃ አቀባይ የሰጡኝ ምላሽ "ድር ወሳኞችን ከመኳንንት፣ ከመሳፍንቱ ጋር ስለሆነ የህብረተሰቡ ምላሽ ድንቅ ነው" ብለዋል። (ጥር 28፣ 2003፣ ደረስኔ) ነገር ግን እነዚህ የመጡት ከትግራይ ስለሆነ አልፎ አልፎ መጤ እየተባሉ ይነቀፋሉ።

ዕምነትን በሚመለከት አንጥረኞች ሙሉ በሙሉ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው። ሙስሊሞች ለምን በዚህ ሙያ ውስጥ የሉም ብየ ለጠየኩት ጥያቄ አቶ አየሁ ገዛልኝ የተባሉ በአንጥረኝነት ሙያ የሚተዳደሩ መረጃ አቀባይ የሰጡኝ ምላሽ የሚከተለው ነው። "አንጥረኞች ክርስቲያን የሆኑበት ምክንያት ብዙ ጊዜ የሚሰሩት ቁሶች የቤተ ክርስቲያን እና ክርስቲያኖች የሚያጌጡበትን ጌጣጌጥ የሚሰሩ ስለሆነ ይህንን አይነት ስራ በሙስሊም ማሰራት ክርስቲያኖቹ ስለማይፈልጉ ሙስሊሞች ይህን ሙያ የመልመድና በሙያው የመስራት ፍላጎት አይታይባቸውም።" (ጥር 14፣ 2003፣ ድልድሊት) በርግጥ ማረሻ፣ ፋስ፣ ማጭድ ቢሰሩ ዕምነት አይለይም። ነገር ግን ማረሻ የሚሰሩት ወርቅ ስለሚሰሩ አንጥረኝነት የክርስቲያኖች ሙያ፣ ሽመና ደግሞ የሙስሊሞች ሙያ ተደርጎ ይታያል።

በሌላ በኩል አንጥረኝነት የእስራኤሎች ሙያ ተደርጎ ስለሚቆጠር እስራኤል ደግሞ የክርስቲያን ምድር ናት ብለው ስለሚያምኑ ሙስሊም ሆኖ ይህን ሙያ መልመድ ማለት ክርስቲያን የመሆን ያህል ይሰማቸዋል በማለት ሃሳባቸውን የገለጹት አቶ ደሴ አየልኝ ናቸው። ስለዚህ ሙያውን መልመድ አይፈልጉም። በሌላ በኩል ይህን ሙያ ቢለምዱ ችግሩ ምንድን ነው ተብለው የተጠየቁት አቶ አገር አምሳል የተባሉ በአንጥረኝነት ሙያ የሚተዳደሩ መረጃ አቀባይ የሰጡት መልስ "ቡዳ፣ ካይላ በሚል የሚደርሰውን አሽሙር መቋቋም ስለሚፈሩም ጭምር ነው። አሽሙር አገር ያስለቅቃልና ይፈራሉ። ሌላው ያለ አባቴ ፣ ያለ ዘሬ እያሉ ስለሚፈሩት እንጂ ሙያውስ አይከብዳቸውም ነበር።" በማለት ገልጸዋል (ጥር 29፣ 2003፣ ድልድሊት)

ሙያ ለመዱውን በሚመለከት አብዛኛው አንጥረኞች ሙያውን የለመዱት በዘር የእኛ ብለው እያገው ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፉ ዛሬ ላይ ያደረሱት ሲሆን ተስተላለፈው ከአባት ወደ ልጅ በሚል እሳቤ ነው። ፍቃዱ ዮሐንስ የለመዱበትን መንገድ ሲያስረዱ፡

> እኔ ከአባቴ ተማርኩት፣ አባቴ ደግሞ ከአባቱ ተማረው ገና ከ16 ዓመቴ ጀምሬ መስራት ጀምርኩኝ። እየቆየሁ ጥበቡም ተገለጠልኝ እየው እየሰራሁ እገኛለሁ፣ ጥበቡ ሲገለጥልህ ይቀላል። እኔም ለልጄ ሙያውን አስለምጄው እየሰራ ሲሆን ታናሽ የወርቅ ስራው ላይ እንደኔ በደንብ አልተገለጠለትም። በኛ ስራ ድቃቃ/ጥቃቅን/ ስህተቶች ስራ ስለሚያበላሹ እሱ ልብ ብሎ ተጠንቅቆ ስለማይሰራ ያናደኛል። ግን ምንም አይል። እሱም አሁን ወርቅም፣ የሚያሰራ ሰውም የለም እያለ ተሰል ይለዋል። በግለት ሙያውን በዘር እንደለመዱት አጫውተውኛል። (ሚያዝያ 12፣ 2003፣ ደረስ)

የልጆ ልጆ የሆነው ህፃን ወንድምሁነኝ እያሌው የቤተሰቦቹን ስራ እንደሚወደው ገልጾ የወር መስቀል አሰራር እንዴት እንደሆነ ተጠይቆ በቃል በደንብ አድርጎ ማብራራት ችሏል። ይህ የሚያሳየን ሙያው አሁንም ከአባት ወደ ልጅ በሚለው ተስተላልፎ ወስጥእንዳለና እንደሚቀጥል ይጠቁማል።

የተወሰኑ አንጥረኞች ደግሞ ሙያውን በዘር ሳይሆን ከሌላ ሙያተኛ በረዳትነት ተቀጥረው የለመዱ አሉ። ሌሎች ደግሞ ኅልማሶች ማሰልጠኛ ማቢያ የሚሰጠውን ስልጠና ወስደው ሙያውን ለምደዋል። እንዲሁም ስልጠና ወደሚሰጥበት የተለያዩ ስፍራዎች በመሄድ ሙያውን ለምደው አሁን መተዳደሪያቸው አድርገው በመስራት ላይ ይገኛሉ። በረዳትነትም ሆነ በማሰልጠኛ ማቢያዎች በሚሰጥ ስልጠና የሚለመደው ሙያ ወርቅና ብር መስራትን አያካትትም። አሁን በመስራት ላይ ያሉት ወጣትና አዛውንት ሙያቸውን ለልጆና ለልጅ ልጅ በማውረስ ላይ ያሉ ሲሆን አቶ ፈንታሁን ካሳ የተባሉት ሙያተኛ ግን ልጃቸው ይህን ሙያ እንዲማር እንደማይፈልጉና ሌላ የተሻለ ትምህርት ተምሮ ጥሩ ቦታ እንዲደርስ እንደሚፈልጉ ገልጸዋል። ቢሆንም እኒህ ሰው

ደሞዛቸው በወር ከ 4000 ብር በላይ ስለሆነ ገቢው ጥሩ እንደሆነ ቢያውቁም ስራው ትዕግስት ስለሚፈልግ ከባድ እንደሆነና ልጃቸውን ሌላ ነገር እንደሚያስተምሩትና እንደሚያሰሩት ገልጸዋል። አቶ ፈንታሁን ካሳ ሙያውን የለመዱበትን መንገድ ሲገልጹ "ከልማሶች ማሰልጠኛ ማዕከል ገብቼ ለሶስት ወር በመሰልጠን ሙያውን መተዳደሪያየ አድርጌዋለሁ።"(የካቲት 26፣ 2003፣ ደረስጌ)

አንጥረኞቹ ብርና ወርቅ ስራ የሆነበት ምክንያት ሙያው ከትውልድ ትውልድ በመተላለፍ ብቻ ሳይሆን በአንድ ጎናቸው(በእናት ወይም በአባት) ትግራይ አካባቢ በመሆን በአካባቢው ወርቅ ስለሚገኝ ሙያውን ለመልመድ አጋጣሚው ምቹ እንደሆነላቸው በአንጥረኝነት ሙያ የሚተዳደሩት አለሙ ጥጋቤ ገልጸዋል።

በሙያና ሙያተኞቹ ላይ የታዩ ለውጦችን በተመለከተ ከድሮ ጀምሮ የሚሰሩት ቁስና የመስሪያ ቁሳቸው ያልተለወጠ ሲሆን እንዲያውም አንዳንድ ድሮ የነበሩ ቁሶች (ወርቅ፣ ድሪ፣ ጠልሰም፣ ወለባ) አሁን አሁን ተጠቃሚ በማጣትና ወርቅ በመጥፋቱ ምክንያት አገልግሎት ላይ የመዋላቸው ጉዳይ እየቀነሰ የመጣ ሲሆን ከዚህ አንፃር ሙያው እየተዳከመ እንደመጣ ያሳያል። ወርቅ ማቅለጫው አሲድ፣ መርቅ መቀቢያው መዳብ እና ማር ትሬሳ ብር በአሁኑ ጊዜ ሙሉ በሙሉ በመጥፋቱ አይደለም ቁስ ሊሰራበት እና መስሪያ ሊሆን ለመቅረስ እንኳ አልተቻለም። በተቃራኒው የሙያተኞቹ ገቢ እያደገ የመጣ ሲሆን በተለይ ድባብ፣ ማሬሻ፣ ማጭድ፣ ፋስና ገጀሞ ጥሩ ገቢ ስለሚያስገኙ የሙያተኞቹ ሕይወት እየተሻሻለ እንዲመጣ ረድተዋል። ለውጡን በተመለከተ በአንጥረኝነት ሙያ የሚዳደሩት አቶ አለሜ ወንዳቸው የሰጡት ሃሳብ " ሳር ቤት የነበራቸው ቆርቆሮ ቤት ሰርተዋል፤ ቆርቆሮ ቤት የነበራቸው ከተማ (መካነ ብርሃን) ቤት መስራት ጀምረዋል። እንዲሁም ከድሮ በተሻለ መልኩ ማህበር/ጽዋ አብረን እንጠጣለን፤ የቀበሌው አመራር ውስጥ ገብተን መስራት መጀመራችን ይበል የሚያስብል ነው። ጋብቻ ላይ ግን አሁንም ጠይቆ የማገኘት ችግር አለ።" ብለዋል(የካቲት 17፣ 2003፣ ድልድሊት)።

## 4.7 የቁሶች ትዕምርታዊነት

ቁሶች ከሚወክሉት የቁስነት አገልግሎት ባሻገር ህብረተሰቡ ተጨማሪ ትርጉም ስለሰጣቸው ተምሳሌታዊ የሚሆኑበት አጋጣሚ አለ። የቁሶቹ ተምሳሌታዊነት ከባለጸጋነትና ከሉሌነት፣ ከሃብትና ከድህነት፣ ከልጅነትና ከአዋቂነት፣ ከደስታና ከሃዘን፣ ከእምነት፣ ከአዲስነትና ከአሮጌነት ጋር የተያያዘ ነው። ከላይ የቀረበው የትዕምርት ይዘት መሰረትነት የትኛው ቁስ የየትኛው ትዕምርት (ምሳሌ፦ የባለጸጋነት ወይስ የሉሌነት) እንደሆነ ቀጥሎ አብራራለሁ።

ከባለጸጋነትና ከሉሌነት ጋር በተያያዘ ትዕምርት ካላቸው ቁሶች መካከል ኩታ፣ ፎጣ፣ ወርቅና ነሃስ ተጠቃሽ ናቸው። የባለጸጋነትና ሉሌነት፣ ከሃብታምነትና ድሃ ከመሆን ጋር እኛ ሆነው የሚቀርቡበት አጋጣሚ አለ። ባለጸጋነት ህብረተሰቡ ለሰውየው የሚሰጠው ከፍ ያለ ማህበራዊ ደረጃ ሲሆን ይህ ደረጃ አልፎ አልፎ ባላቸው ሃብት ወብትም ሊወሰን ይታያል። የሃብት ደረጃው እንዳለ ሆኖ ባለጸጋነትን የሚያጎሉ ሌሎች ነገሮች ዘር፣ ፈውዳል ወይም የገዥ መደብ አባል መሆንና በህብረተሰቡ ኑሮ አዎንታዊ ሚና የሚጫወት ከሆነ ነው። ለምሳሌ ሽፍታን በመከላከል አካባቢን ማስከበርን፣ በእርቅ ስርዓት ጊዜ ወሳኝ ሚና መጫወትን ያካትታል። በመቀጠል እያንዳንዱ ቁስ ያለውን ተምሳሌታዊነት አሳያለሁ። ከዚህ በታች የቀረቡት ትዕምርቶች Schlereth ተምሳሌታዊ ካሉት ጋር የሚጣመድ ነው።

ኩታ ስምንት ጥለት ያለው ሃያ ስድስት ክንድ የሚረዝም ብዙ ጊዜ ወንዶች የመለብሱት ሸማ ነው። ይህ ሸማ በህብረተሰቡ እምነት ከቁስነት የሰፋ ትዕምርት ያለው ሲሆን ይህም ባለጸጋነትን፣ ተከባሪነትንና ተፈሪነትን የሚያመላክት ነው። የልብሱን ተምሳሌታዊነት አቶ አህመድ አወል ሃሳባቸውን እንዲህ ገልጸዋል።

> ኩታማ ኩታ ነው። ኩታ ከለበስክ ትንሽ ትልቁ ያከብርሃል፣ ይፈራሃል። ማንም እንደፈለገ አይናገርህም። ታድያ ኩታ የሚለብስ ሰው ራሱ ክበር ማለት አለበት። ሲናገር ይቆጠባል ጠብቆ ነው ጣል የሚያደርግ እና ሰዉ ይሰማዋል። እንዲያውም አሁንማ ሴቶችም እያደረጉት ነው። ሴቶቹ ግን ልክ እንደ ወንድ

የሚከበሩ ከሆኑ ነው ኩታ የሚለብሱት። (ሚያዝያ 29፣ 2003፣ መካነ ብርሃን)

ከላይ ጥቅሱ እንደሚያሳየው ኩታን የሚያደርጉ ወንዶች እንደሆኑና አልፎ አልፎ ማህበራዊ ደረጃቸው ከፍ ያሉ ሴቶችም እንደሚያደርጉት ያሳያል። ስለዚህ ልብሱ ከቁስነት በላይ የባለጸጋነት ተምሳሌት ሆኖ ቀርቧል።

በአንኮበረኘነት ሙያ ደግሞ ወርቅ የባለጸጋነት ተምሳሌት ነው። አንድ ሰው የራሱን ወርቅ አምጥቶ በአንጥረኞች አሰርቶ በማድረጉ በህብረተሰቡ የሚሰጠው ክብርና ማህበራዊ ደረጃ ከፍ ይላል። የወርቅን ተምሳሌትነት የገለጹት ወ/ሮ መንበር መዘንጊያ የተባሉ የአካባቢው ባህልና ታሪክ አዋቂ ናቸው።

> ወርቅ የመኳንንት፣ የመሳፍንት እንጂ የማንም አይደለም። ወርቅ የፊታውራሪ ይግዛው[3] ነው። ዛሬ ማንም የትም ተርቦ ገንዘብ አጠራቅሞ ወርቅ ገዛሁ ይላል። የዛሬው ወርቅ አይመስለኝም። ለምን? ወርቁ እንኳን ሊያስከብራቸው የባሰ ጠውጣዋ ነው ያደረጋቸው። የወርቅ ጥንስ ያለው ሳይሰራ ጠጠሩን ከአስመራና ከውጭ አገር አስመጥቶ ከዚህ እንደፈለጉት ሲያሰሩ ነው። እንዲህ ማድረግ ትልቅነት ነው። ድሮ ወርቅ የሚያደርጉት ስለሚታወቁ ይከበራሉ። እንዲያውም ወርቅ ከሚያደርጉ ጋቢም የጠየቀ ወርቅ ፈልጎ ነው ወይስ ልዩ ተብሎ ይታማ ነበር። (ሚያዝያ 22፣ 2003፣ መካነ ብርሃን)

ከላይ ጥቅሱ እንደሚያሳየው ወርቅ ባለጸጋነትን ባለሃብትነትን ይገልጻል ሲባል ወርቅ ከየትም ገዝቶ የሚያደርገውን ሳይሆን ባለቤቱ መጥቶ በአንጥረኛ የሚሰራውን ያልተሃለውን መሆኑን ልብ ይሏል።

[3] ፊታውራሪ ይግዛው በአካባቢው አገር ገዥና ባላባት የነበሩ ትልቅ ሰው ነበሩ፡፡ ልጆቻቸው የአሁኖቹውን ስም እየጠሩ ባለጸጋነታቸውን ሲጠሩ ለመታዘብ ችያለሁ፡፡

ኩታና ወርቅ ያላቸው ትዕምርት ከላይ ተገልጿል። አሁን ደግሞ ከሉሌነት/ ከአገልጋይነት ጋር በተያያዘ ትዕምርት ያላቸውን ቁሶች እንመለከታለን። ከነዚህ ውስጥ አንዱ ፎጣ ነው። ፎጣ የሚለብሱት በኑሯቸው የተጎሳቆሉ ከሚባሉት የህብረተሰብ ክፍሉች ውስጥ ሉሌና አረኛ ይጠቀሳሉ። ለምን ኑሯቸው ዝቅተኛ የሆኑ ሰዎች የሚለብሱት ልብስ ፎጣ ሆነ ብየ አቶ ነጋልኝ ቢያድግን ጠይቂያቸው የሰጡኝ ምላሽ፡-

> ፎጣ የአረኛ፣ የየሉሌ፣ የኩታራ ልብስ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ፎጣ እድፍ እንዲችል ተብሉ ጠቆር ባለ ክረን ስለሚሰራ፤ እንደኩታው ጌጥ ሳይወጣለት እንደ ነገር እንደ ነገሩ የሚሰራ ስለሆነ ነው። ሌላ ደግሞ ፎጣ ጠቆር ያለ ስለሆነ በእህል ውቂያ ጊዜ ገለባም ሆነ የታጨደ እህል ሲሸከሙ ሲቆሸሽ መቆሸሹን ጥቁረቱ ስለማያስታውቅበት ለሰራተኞች የተመቸ ስለሆነ ነው። (ሚያዝያ 27፣ 2003፣ መካነ ብርሃን)

ከላይ ጥቅስ እንዲመላከተው ፎጣ አንድም ቀለሙ ጠቆር ባለ ክር ስለሚሰራ፤ አንድም አፈጣጠሩ እንደ ኩታ የሚታጠፍና የሚደረብ ባለመሆኑ የሉሌዎች፣ አረኞችና ኑሯቸው የተጎሳቆለ የህብረተሰብ ክፍሎች ልብስ ተብሉ ውክልና እንደተሰጠው ይጠቁማል። ቀለም ያለው ቦታ ክፍ ያለ እንደሆነ ልብ ይሏል።

ሌላው ነሃስ ሲሆን የተጎሳቆለ ነዋሪነትን የሚጠቁም ነው። ድሃዎች ጋብቻ ሲፈጽሙ የቀለበትና መስቀል ሰጦታ ይሰጣጣሉ። ይህ የሚያሣየው የሰዎቹ የኑሮ ደረጃ ዝቅተኛ የሚባል እንደሆነ ነው። ስለዚህ ነሃስ በህብረተሰቡ የድህነት፣ የበታችነት ተምሳሌት ነው።

ሌላው ደግሞ ከደስታና ከሃዘን ጋር የሚያያዝ የቁስ ትዕምርታዊነት ነው። ቁሶቹ ሲደረጉ በመመልከት ይሄ የሃዘን፣ ይሄ ደግሞ ደስታን ይጠቁማል በሚል የተሰጣቸው ውክልና አለ። ከነዚህ ውስጥ ከቀሚስና ነጠላ የሚደረጉ ጥለቶች ያደረገውን ሰው ስሜት(የደስታና የሃዘን) ይጠቁማሉ። ቀሚስ ሙሉ በሙሉ በጥቁር ክር ከተሰራ፤ ነጠላው ጥለቱ በጥቁር ጥለት ከተሰራ የሃዘን ተምሳሌትነት አለው። የአልባሳቱን ተምሳሌትነት በተመለከተ አቶ ደጋፍ ምሲጋናው የሰጡት ሃሳብ፡ "ጥቁር በኛ የመጥፎ ምስያ ነው።

ለዚህ ነው በበዓል ወቅት ጥቁር በግ የማናርደው። አንድ ሰው ጥቁር ጥለት ያለው ቀሚስ፣ ነጠላ ከለበሰ የሞተበት ሰው አለና ቤቱ ሄደን እናጽናናዋለን።" (ሚያዝያ 25፣ 2003፣ መላኩ ብርሃን)

ከላይ የቀረበው ሃሳብ እንደሚጠቁመው የጥለቱ ቀለም ሃዘንን ይጠቁሟል። ኩታ ቀሚስና ነጠላ ያለጥለት ተሰርቶ በአዲስነቱ ከተደረገ የደስታ መግለጫ ነው። ልብሱን ያደረጉ ሰዎችም ውስጣቸው ደስታ ባለበት እንደሆነ ይጠቁማል። በሌላ በኩል ቁሶቹ ጥለት የሌላቸው ሆነው የተቀዳደዱ ከሆኑ የሃዘን ተምሳሌታዊነት የሚኖራቸው አጋጣሚ አለ። ምክንያቱም አዲስ ልብስ ለብሶ ቀብር የሚሄደው ሲያስተዛዝንና ሲያለቅስ ነው ወይስ ሊቀልድ ተብሎ ይታማል። እንዲሁም ለቅሶ ቤት ሲሄድ አለባበስን ማስተካከል ገና ነው በማለት ወ/ሮ መንበር መዘንጊያ ገለጸዋል።

ልጅነትና አዋቂነትን በሚመለከት ቁሶቹ የተሰጡት ሚና አለ። ከእነዚህ ቁሶች መካከል ፎጣና ቀሚስ ይገኙበታል። ቀሚስ የምን ተምሳሌት ነው ብየ ስጠይቅ አቶ ሹመት አዳኖ የሰጡት መልስ፡

> ቀሚስ (በሸማ ሙያተኞች የሚሰራውን) ለብሳ የታየች ሴት ምራቋን የዋጠችና እንደ ልጅ እዩኝ እዩኝ የማትል መሆን አለባት። ሌላ ይሄ የሚያበድቱማ የሚለብሱት በሜትር የሚሸጠውን ቀሚስ እንጂ ጥልፍ ቀሚስ አያደርጉትም። ይገርምሃል ወጣት ሆና አግብታ ወልዳ ቀሚስ መልበስ ስትጀምር ያን ሁሉ እብደት ጥላ የሰከነ ሰው፣ ዘመድ ጠያቂ ትሆናለች። ልብሱ ወጣትነትን ያበርድና ጥሩ ሰው ያደርጋል። እንዲያውም እሷ እኮ ቀሚስ ለባሽ ናት ይባላል፣ መስከኗን ለመናገር። (ሚያዝያ26፣ 2003፣ መላኩ ብርሃን)

ጥቅሱ ቀሚስ የአስተዋይነት፣ የታጋሽነት ትዕምርት እንዳለው ይጠቁማል። ቀሚስ የምታደርግ ሴት ጠባይ በጎ መሆኑን ልብሱ ታጋሽና አስተዋይ እንደሚያደርግ ያሳያል። ምክንያቱም ቀሚስ በህብረተሰቡ የተሰጠው ዋጋ ከፍ ያለ ስለሆነ ይህን ልብስ ለብሶ እቀወጣለሁ፣ እፈነግጣለሁ ማለት ቤተሰብንና ባህልን መናቅ ተደርጎ ስለሚቆጠር

በልብሱ አማኒነት ባህሉ ገዘፍ ልጅቱ እንድትስተካከል የማድረግ ሚና ተወጥቷል። ባህል የሰውን ልጅ ማንነት የሚቀርጽና የሚገራ ነው።

ፎጣ ደግሞ በአካባቢው ልጅነትን የሚጠቁም ነው። ፎጣ ከሉሌዎች በተጨማሪ ሀጻናትም ያደርጉታል። ቢሆንም የህጻናቱና የሉሌዎች በትልቅነትና በትንሽነት ብቻ ላይሆን በቀለምም የተለያዩ ናቸው። የህጻናት አጭር ሆኖ ብዙ ጊዜ በአረንጓዴ፣ በሰማያዊና ቀይ ቀለም ተቀላቅሎ ይሰራል። በህጻናት ፎጣ ራሱን አስሮ ወደ ስራ የሚሄድ አካውራ ምን ህጻን ይመስል በፎጣ እንደሚባል ወ/ሮ መንበር መዘንጊያ ነግረውኛል።

ሻሽ፣ ሽርብ እና ቀይ ጥለት ነጠላ ከዕምነት ጋር በተያያዘ የተሰጣቸው ትዕምርት አለ። ሻሽ የካህን ጥምጥም፣ ቀይ ጥለት ነጠላና ሽርብ የባለ ቆሌ ሰው(ብዙ ጊዜ ሴት) ተምሳሌት ነው።

ሻሽ ከቤተክርስቲያን አገልጋዮች በቀር ማንም እንደማይጠመጥም ከጠመጠመ እምነትን መድፈር፣ እግዚአብሔርን መዳፈር እንደሆነ አቶ ነጋልኝ ቢያድጎ ገልጸዋል። ምክንያቱም ሻሽ ህብረተሰብ ለካህናት ብቻ የተሰጠው ልብስ ስለሆነ ይመስለኛል። ጥምጥሙን በመመልከት የቤተክርስትያን አገልጋይ/ዲያቆን፣ ካህን፣ መርጌታ/ እንደሆነ ይለያል። ሽርብና ቀይ ጥለት ነጠላ ማድረግ ደግሞ ባለዛር መሆንን ይጠቁማል። ብዙ ጊዜ እነዚህ ቁሶች የባለዛር ሰዎች ምስያ ናቸው። ባእድ አምልኮ የሚከተሉ ሰዎች ከቤታቸው ሰው ሊታመምባቸው ባለዛሮች መጥተው ሲታመመው እንዲለምኑለት ይደረጋል።

## 5. ማጠቃለያ

በጥናቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዋና አላማ በጃናሞራ ወረዳ በተመረጡ ቀበሌዎች(ደረስጌና መካነ ብርሃን) የሚገኙ እንጥረኞችና ሸማኔዎችን ሕይወት ማጥናት ነበር። ዓላማውን ከግብ ለማድረስ መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሰብስበው በካሴት፣ በፎቶና በቪዲዮ ተቀርሰዋል። መረጃውን ለመተንተን ይረዳ ዘንድ የተለያዩ ቲዎሪዎች ቀርበው (በተለይ የ Schlereth 2.2.2፣ Fleming 2.2.3.2 እና Prown 2.2.3.1) መረጃው ተተንትኗል። ጥናቱ ሰላሳ ዘጠኝ መረጃ አቀባዮችን ቃለ መጠይቅ በማድረግና ተተኳሪ የቡድን ውይይት በማካሄድ መረጃ አሰባስቦ ተንትኗል።

ጥናቱ እንዳሳየው አብዛኞቹ ሙያተኞች ሙያውን በልማድ ተቀብለው ከትውልድ ወደ ትውልድ በቅብብሎሽ እየለመዱ አሁን ካለበት ደረጃ አድርሰውታል። አንዳንድ ሙያተኞች ደግሞ ሙያውን በስልጠና አውቀውታል።

በሸመና ሙያ የሚተዳደሩ ሙያተኞች በቁጥር አስራ ሁለት ያህል ሸማ ሲሰሩ የሚሰሩት ቁስ ስንመለከት ነጠላ ፣ ኩታ ፣ ስካርፕ ፣ ሸሚዝ ፣ ፎጣ ፣ ሸርብ ፣ ቀሚስ፣ የአልጋ ልብስ፣ መቀነት፣ ሻሽ፣ ሸርብ፣ ወዘተ ናቸው። የቁሶቹ ዋጋ አንዱ ከአንዱ የሚለይ ሲሆን በምክንያትነት የሚጠቀሱት ነጥቦች አንደኛ የሚሰራው ልብስ ርዝማኔ መለያየት፣ ሁለተኛ የልብሱ ጌጥ/ጥለቱ ዓይነትና ብዛት፣ ሶስተኛ ብዙ መምቻ(ብዙ ክር ወይም ዘሃ) የሚፈልግና በጥቂት መምቻ የሚጠናቀቁ በመሆናቸው ነው። ለአብነት ፎጣ ከሰላሳ አምስት እስከ ሰማንያ ብር ይሸጣል። ምክንያቱም ሰላሳ አምስት የሚሸጡት የሚሰሩበት መምቻ ብዙ ክር የሚፈጅ ስላልሆነ፤ በሰማንያ ብር የሚሸጡት ግን መስሪያ ቁሱ ባለ አራት መርገጫ ስለሆነ መምቻው ብዙ ክር ይፈጃል፤ በደንብ ይመታዋልና።

እንጥረኞች ደግሞ አስራ ስድስት ያህል ቁስ የሚያመርቱ ሲሆን እነርሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል። ፋስ፣ ማጭድ፣ ማረሻ፣ መጥረቢያ፣ ከርፊዝ፣ ገጀራ፣ ጋሻም፣ ካራ/ቢላ፣ ቀለበት(የብር)፣ ቀለበት(የወርቅ)፣ መስቀል(የብር)፣ መስቀል(የወርቅ)፣

ድባብ፣ ጠልሰም፣ አልቦ እና ድሪ ናቸው። ሙያተኞቹ በአማካይ ትልቅ ወይም ትንሽ በሚል ለቁሶቹ አማካይ ዋጋ ያስቀመጡ ቢሆንም እንደ አሰሪው ፍላጎት የትልቅ ትልቅ ወይም የትንሽ ትንሽ ሊያሰራ ይችላል። ዋጋው እንደሚፈጁት ብረትና ጊዜ ወይም ብርና ጊዜ አዲስ የዋጋ ተመን ይወጣላቸዋል። እንዲሁም ሲታደሱ እንደሚታደሰው ቁስ ትልቅነትና ትንሽነት ብቻ ሳይሆን እንደ ቁሱ ብዙ መጎዳትና አለመጎዳት የማሳደሻ ዋጋው ይለያያል። ቁሶቹ አብዛኛው የሚታደሱ ሲሆን ክርፈዝ ግን አይታደስም።

ሙያተኞቹ ማህበራዊ ሕይወታቸው የተገደበ ሲሆን በጋብቻ፣ በሽምግልናና ሌሎች ማህበራዊ ኢንስቲትዩሽኖች የሚሰጣቸው ሚና አነስተኛ የሚባል ነው። ነገር ግን ጥበብ ሰሪ በመሆናቸው የሚሰጣቸው ስም በፊት ከነበረው አሉታዊ ስም በመሻሻል ላይ ያለ መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል። ለዚህ ማሳያ ሰባ ስድስት ያህል ሽመናን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች የተሰበሰቡ ሲሆን ማህበራዊ ሕይወታቸውን ያሳዩ ናቸው። ማብራሪያ በምዕራፍ አምስት ቀርቧል። የሁለቱን ሙያተኞች ሕይወት በገቢ ደረጃ ጥሩ የሚባል ቢሆንም ማህበራዊ ሕይወታቸው ላይ የሚደርስባቸው አሉታዊ ተጽዕኖ አሁንም ድረስ እንዳልተቀረፈ ጥናቱ አሳይቷል።

በቁሶቹ ተጠቃሚነት የሽመና ሙያ ከአንጥረኝነት የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። በሌላ በኩል አንጥረኝነት ሙያተኞች የሚሰሩት ቁስ ተጠቃሚነቱ እየቀነሰ መጥቷል። ምክንያቱም ብርና ወርቅ እየጠፋ በመምጣቱ እና በተለምዶ "ክባዕድ አምልኮ/ቆሌ" ጋር በተያያዘ በሰሙታ መልክ የሚጣሉ ጥለቶች እየቀሩ ስለሆነ የምርት መቀነስ ታይቷል። ሙያተኞቹ አሁንም ድረስ "ቡዳ" እንደሚባሉ እንደሚሰደቡ፣ ማህበራዊ ሕይወታቸውም የተገደበ እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል። የአንጥረኞችን ሕይወት የሚመለከት አርባ አንድ ቃል ግጥሞች ተሰብስበው ፣ የተወሰኑት ተተንትነዋል። ሙያተኞቹንና ሙያቸውን የሚመለከት 126 ቃል ግጥሞች የተሰበሰቡና የተተነተኑ ሲሆን ይዘታቸው ከፊሎቹ የሙያተኞቹን ጥበብ በማድነቅ ምስጋና የሚያቀርቡ፣ ከፊሎቹ ደግሞ የሙያተኞቹን የፍቅር ሕይወት የሚዳስሱ እና ቀሪዎቹ ደግሞ ሙያተኞቹና ሙያቸው የሚነቀፉበት ሆኖ ተገኝቷል።

ቁሶቹ መጀመሪያ ከተሰሩበት አገልግሎት ባሻገር ሌላ ውክልና ተሰጥቷቸው ሲያገለግሉ ታይተዋል፡፡ ለምሳሌ ኩታ፣ ሻሽ፣ ሽርብ ማህበራዊ ደረጃን ሲያሳዩ፤ ፎጣ፣ ወርቅ፣ ብር ኢኮኖሚያዊ ደረጃን የሚያሳዩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ እነዚህን ግኝቶች መሰረት በማድረግ ቢደረጉ ይበጃሉ ያልኳቸውን የሚከተሉትን የይሁንታ ሃሳቦች ሰንዝሬያለሁ፡፡

## የይሁንታ ሃሳቦች

• የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ለቁሳዊ ባህል ያለው ግንዛቤ ከፍ እንዲል የሚቀጥራቸው ሰራተኞች ከባህል ጋር ግንኙነት ባላቸው ትምህርት ክፍል የተማሩ ቢሆኑና ሰራተኞቹም ስለ ቁሳዊ ባህል ምንነት፣ ጥቅምና አገልግሎት ህብረተሰቡን ማስተማር ቢችሉ፤

• በሸመና ሙያ የሚተዳደሩ ሙያተኞች በማህበር ተደራጅተው መስራት ከጀመሩ ወዲህ ደብዝዞ የነበረው የሸመና ሙያና ቁስ መልሶ በማንሰራራት ላይ ስለሆነ እንጥረኞችም በማህበር ተደራጅተው መስራት ቢጀምሩ ቁሶቹ ወደ ቀድሞ አገልግሎታቸውና ሙያተኞቹም የተሻለ ገቢ ሊያገኙ ስለሚችሉ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮና የወረዳው ጥቃቅንና ንግድ ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ቢጋራ ቢሰሩ፤

• የወረዳው ባህልና ቱሪዝም፣ የወረዳው የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት እና የወረዳው ጥቃቅንና ንግድ ኢንዱስትሪ ቢሮዎች የገንዘብና የስልጠና ርዳታ በማድረግ ሙያተኞቹ ስራዎቻቸውን ይዘው ወደ ተለያዩ ቦታዎች ተንቀሳቅሰው እንድም የሰሩትን ቁስ ሸጠው ገቢ እንዲያገኙ፤ እንድም የዕውቀትና ልምድ ልውውጥ ቢያደርጉ ሙያው ከፍ እንዲል ያስችላልና በዚህ ጉዳይ ከላይ የተገለጹት ቢሮዎች በትብብር ቢሰሩ፤

• የወረዳው ጥቃቅንና ንግድ ኢንዱስትሪ ቢሮ ለሸመና ሙያተኞች የገንዘብና የጥሬ ዕቃ ብድር ሰጥቶ እንዲንቀሳቀሱ እንዳደረገ ሁሉ ሙያተኛውና ሙያው የተሻለ እንዲሆን ተመሳሳይ ስራ በእንጥረኝነት ላይም ቢሰራ፤

• የወረዳው ጥቃቅንና ንግድ ኢንዱስትሪ ቢሮና አክሽን ኤይድ ድርጅት ለሸመና ሙያተኞች አስልጣኝ አምጥተው እንዳሰለጠኑ ሁሉ ለእንጥረኞችም ተመሳሳይ ስራ ቢሰሩ፤ ገበያም ቢያፈላልጉላቸው ፤

• የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በአካባቢው፣ የቋንቋና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ጥናት ለማድረግ መስክ ሲወጡ ጥናት በሚያደርጉበት አካባቢ የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎችን መሰብሰብና መሰነድ ቢችሉ፤

- የወረዳው የኮሙኒኬሽን ጉዳይ ጽ/ቤት ቁሳዊ ባህልን በተመለከተ ፕሮግራም ሰርቶ ለክልሉ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ማሰራጫዎች ቢልክና ቁሳዊ ባህልን የማስተዋወቅ ስራ ቢሰሩ፤
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስር ያሉ ቁሳዊ ባህል የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ቁሳዊ ባህልን ለማጥናት ተከታታይና ተጨባጭ የሆነ ስራ ቢሰሩ፤
- ሙያና ሙያተኛው ከፍ ወዳለ ደረጃ እንዲሸጋገሩ የሚመለከታቸው ድርጅቶች በአንድ የሚገናኙበትና ቢጋራ የሚመክሩበትና የሚሰሩበት ሁኔታ ተፈጥሮ ቁሳዊ ባህሉን ቢሰበስቡ፣ ቢቀርሱና ቢተንትኑ።

# የተጠቀሱ ምንጮች


ሔለን አሳምረው ፣ "ባህላዊ ሽመናና የቆዳ ስራ በደንበጫና አካባቢዋ" ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣1999።

ዋልተንጉስ መኮንን፣ "የሽመናና የጥልፍ ትውፊት በአክሱም "፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2000

ደስታ ተክለወልድ፣ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962።

ፊቃደ አዘዘ፣ የስነ ቃል መምሪያ፣ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991።

Burley, Dexter. "The Despised Weaver of Addis Ababa" Proceedings of the 5th International Conference of Ethiopian Studies, University of New Hampshire: 1978.

Dorson, Richard. "Introduction: Concepts Folklore and Folk Life Studies in Richard Dorson(ed.), Folklore and Folk Life; An Introduction. Chicago and London; the University of Chicago Press: 1972.

Fleming, E. McClung. "Artifact Study: a Proposed Model." On line at; URL: http://www.jstor.org/stable/1180572

Gevers, Michael. "Cotton and Cotton Weaving in Medieval Ethiopia" In a Gromyko (ed.) Proceedings of the 9th International Conference of Ethiopian Studies,Moscow. 26-29 August 1986 Moscow: Mauka Publishers: 1988.

Glassie, Henry. Material Culture. Bloomington and Indianpolis. Indiana University Press: 1999.

Jones, O. Michael. How can Apply Event Analysis to Material Behavior, and Why Should we? On line at: http//www.jstor.org

Kenneth, Goldstien. A Guide for Field Work in Folklore. Pennysylvania; The American Folklore Society: Folklore Associates I. N. C: 1964

Leymans. "Folk Life and Field work: A Leymans Introduction to Field Techniques" on line at: http://www.btnep.org

Leone, P. Mark. "Henry Glassie and General Meaning of Thing" on line at: http//www.jstor.org

List, George. "Field Work: Recording Traditional Music." In Folklore and Folk Life: An Introduction. Dorson, Richard (ed.) Chicago and London; the University of Chicago Press: 1972.

MacDonald, Donald. "Field work: Collecting oral literature." In Folklore and Folk Life: An Introduction. Dorson, Richard (ed.) Chicago and London; the University of Chicago Press: 1972.

Martin and Martha C. Sims. Living Folklore. Utah State University Press: 2005.

Pankhurst, Richard. "History of Ethiopian Hand Crafts and Hand Craft Workers" In Palo Diece and Claudio Vie Zoli (ed).Resatel and Rural Development in Ethiopia Socio and Economic Research, training and technical assistance in the Bless Valley: 1992.

Prown, David. "Mind in Matter: An Introduction to Material Culture Theory and Method." On line at: http//www.jstor.org

Roberts, Warren. "Field Work: Recording Material Culture." In Folklore and Folk Life: An Introduction. Dorson, Richard(ed.) Chicago and London; the University of Chicago Press: 1972.

"Material Culture: Folk Crafts." In Folklore and Folk life: An Introduction. Dorson, Richard(ed.) Chicago and London; the University of Chicago Press: 1972.

Schlereth, Thomas. Material Culture Studies in America. Nashville: America Association and Local History:1982.

. . . . "Understanding the Nine Models of Material Culture Interpetation" On Line. Available at: http//www. btneporg.

. . . . . "Material Culture Research and Historical Explanation." On Line. Available at: http//www.jstor.org/stable/33775481.

Sophie, Desta. "Cottage Crafts" Ethiopian Observer, V.1: No 3, 1963

Wilson William. "Documenting folklore". In Folk groups and Folklore Genres: An Introduction. In Elliot Oring(ed.). Logan; Utah State University Press: 1986.

Woodward, Ian. Understanding Material Culture. SAGE Publications: 2007.

አባሪ 1

የሽመና መሳሪያዎች ለስራቸው የሚገለገሉባቸው ቁሶች

| የቁስ ስም | መስሪያ ንጥረ ነገር | አገልግሎት |
|---|---|---|
| ፈትል/ ቀለም | ጥጥ | ለመምቻነት |
| ኮሸሮሊ | ሽንበቆ + እንጨት | ዝሃ መወጠር |
| መወርወሪያ | እንጨት | ቀለም ማመላለስ |
| ቀሰም | ቃንጫ | ቀለም ማጠንጠን |
| ማትለሚያ/ ማዳወሪያ | እንጨት + ሽንበቆ | ብዙ ፈትል በአንድ ማጠንጠን |
| መሌን | እንጨት | ምርት መሰብሰቢያውን እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ |
| መምቻ/ ዳፋ | እንጨት | ወንፈቱን መያዣ |
| ወንፈት | ሽንበቆ + ሳር | ዝሃው ሳይጠላለፍ ማሳለፊያ |
| መፋረኪያ | ሽንበቆ | የወንፈቱን መቃ ከአደጋ መከላከል |
| የዳፋ ገመድ | ሲር + ሲባን | ዳፋው እንዲረጋ ማድረግ |
| መርገጫ | እንጨት + ገመድ | ምሺኑ እንዲከፍት ማድረግ |
| ተሸካሚ | እንጨት | የሸማ ዕቃውን መሸከም |
| መጠቅለያ | ›› | ምርት መሰብሰቢያ |
| ምሺን | እንጨት + ሲር | የተቋጠረ ዝሃ ማሳለፊያ |
| የሚሺን ፈረስ | ሲር | ዘንጉ እንዳይወልቅ ማድረግ |
| የምሺን ዘንግ | እንጨት | ምሺኑ እንዲረጋ ማድረግ |
| ማጥበቂያ/ መስቀያ | ›› | ዝሃ ገትሮ መያዝ |
| ዓሳ | ›› | ተሸካሚውን መሸከም |
| የፈት ግንድ | ›› | ዝሃ ለማፋታታት |
| መዘራዝር | ገመድ | መቋጠሪያ |
| ደንቆር | ዝሃ | ዝሃውን ለቁጢት ማዘጋጀት |
| መዘረሪያ | ዝሃ | ዝሃ ማስጫ |

| | | |
|---|---|---|
| መለኪያ | ገመድ | የተሰራውን ልክ ለማወቅ |
| መጥረጊያ | ሳር | የሚሰራውን ማጽጃ |
| መንተሪያ | እንጨት | የሚሰራው ልብስ እንዳይጨማተር ማድረጊያ |
| ጨንገር | ሸንበቆ | ጥለት/ ጌጥ ማውጫ |
| ጋሬዳ | እንጨት | ለጨንገሮቹ መግቢያና መውጫ ክፍተት መፍጠሪያ |
| መቆናጥል | እንጨት + ገመድ | ሚዛን መጠበቅ + ክፍተት መፍጠር |
| መቆራቆር | እንጨት | ወንፊቱ እንዲረጋ ማድረጊያ |
| ቁጢት | ዝሃ | የስራውመጨረሻናመቋጠሪያ |
| ዝሃ | ጥጥ | ለሽማ ስራ ተጥሎ መሰራት |
| ማገ | ጥጥ | ለተጣለው ዝሃ መምቻ |
| ጥለት | ክር | ለተሰራው ስራ ጌጥ |

አባሪ 2

የአንጥረኛ ሙያተኞች ለስራቸው የሚገለገሉባቸው ቁሶች

| የቁስ ስም | የሚሰራበት ንጥረ ነገር | አገልግሎት |
|---|---|---|
| ወናፍ | እንጨት+ ቆዳ +ቀንድ+ ብረት | እሳት ማቀጣጠያ |
| መጠቅለያ | ብረት | ቁስ እንዲጠቀለል ማድረግ |
| ጉጠት | ፡፡ | የጋለ ብረት መያዣ |
| ሞደሻ | ብረት + እንጨት | ብረት መጠፍጠፊያ |
| ሸክላ | አፈር | የወርቅና የብር ማፈኛ |
| ስም | የማር ሰፈፍ | የወርቅና የብር ቅርጽ ማውጫ |
| ውሃ | - | የተሰራው ቁስ ማትቢያ |
| ቡርሽ | እንጨት + ሽራ | የቁስ ማጽጃ |
| ኒኬል | - | ቀልጦ ለዕቃ ማጣበቂያነት |
| ከሰል | እንጨት | ቁሱ እንዲግል(እንዲቀልጥ) ማድረግ |

አባሪ 3

ከሽመና ሙያ የሚገኙ ቁሶች

| [illegible] | ቁስ የሚሸፍነው የሰውነት ክፍል | መስሪያ ንጥረ ቁስ | አማካይ ዋጋ (በብር) | ርዝማኔ በሜትር(ሜ) በክንድ(ክ) | ተጨማሪ መረጃ | የለውጥ ሁኔታ | የትንታኔው ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| [illegible] | ከወገብ በላይ | ዝሃ + ማግ + ጥለት | 25.00 | 6ሜ፣ 12ክ | ብዙ ጊዜ የሴቶች ልብስ ነው | ለውጥ አልተካሄደበትም | በቀጥታ ትንታኔ ተደርጎበታል |
| [illegible] | ከታፋ በላይ | ›› | 90.00 | 13ሜ፣26ክ | በኢኮኖሚ ከፍ ያሉ ሰዎች ያደርጉታል | ›› | ›› |
| [illegible] | ›› | ክር | 45.00 | 6ሜ፣ 12ክ | የእረኞችና "የሎሌዎች" ልብስ | ፍላጎቱም አሰራሩም ከፍ ብሏል | ›› |
| [illegible] | ሙሉ ሰውነት | ዝሃ + ማግ+ ጥለት | 65.00 | 10ሜ፣ 20ክ | የአዋቂ ሴቶች ልብስ | ›› | ›› |
| [illegible] | ከአንገት በላይ | ክር | 60.00 | 1ሜ | የወጣቶች ልብስ | ›› | ›› |
| [illegible] | ሙሉ ሰውነት | ዝሃ+ ማግ+ ጥለት | 80.00 | 3ሜ | ለሁሉም የሚሆን | ›› | ›› |
| [illegible] | ከወገብ በላይ | ክር | 65.00 | 2ሜ | ›› | ›› | ›› |
| [illegible] | የራስ ልብስ | ዝሃ+ፈትል | 15.00 | 2ሜ | ለካህናት | ፍላጎቱ ቀንሷል | አልተተነተነም |

## አባሪ 4

በእንጥረኞች የሚሰሩ ቁሶች

| [illegible] | መስሪያ ንጥረ ቁስ | አገልግሎት | አማካይ ዋጋ (በብር) | የለውጥ ሁኔታ | የትንታኔ ሁኔታ | ተጨማሪ መረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| [illegible] | ብረት | እንጨት መፍለጫ | 45.00 | ለውጥ አልተካሄደበትም | በቀጥታ ትንታኔ ተደርጎበታል | ከሙያተኞቹ ውጭም ከፋብሪካ ተሰርቶም ይመጣል |
| [illegible] | ፡፡ | እንጨት መላጊያ | 30.00 | ፡፡ | ፡፡ | ዋጋው እንደ ቁሱ ትልቅነትና ትንሽነት ይለያያል |
| [illegible] | ፡፡ | መሬት ለማረስ | 80.00 | ፡፡ | ፡፡ | - |
| [illegible] | ፡፡ | ማረሻ ማጥበቂያ | 20.00 | ፡፡ | ፡፡ | አይታደስም |
| [illegible] | ፡፡ | ሳርና እህል ማጨጃ | 25.00 | ፡፡ | ፡፡ | በጨው ሲተባ የመሰበር ጠባይ አለው |
| [illegible] | ፡፡ | ስጋ መክትከቻ | 15.00 | ፡፡ | ፡፡ | - |
| [illegible] | ፡፡ | ቁጥቋጦ መመንጠሪያ | 20.00 | ፡፡ | ፡፡ | በከተማ ብዙ አይታወቅም |
| [illegible] | ብረት፣ ብር፣ ነሐስ | ፀሀይ መከላከያ | 1500.00 | ፡፡ | ፡፡ | የቤተክርስቲያን ሞገስ ነው ይባላል |
| [illegible] | ሽቦ | የአንገት ጌጥ | 17.00 | በመጥፋት ላይ ነው | ፡፡ | ከእምነት ጋር የተያያዘ ትርጓሜ አለው |
| [illegible] | ብር | ፡፡ | 10.00 | ተጠቃሚው እየቀነሰ መይቷል | ፡፡ | በሰርግ ጊዜ ሙሽሮች ያደረጉታል |
| [illegible] | ብር | የእግር ጌጥ | 8.00 | ፡፡ | ፡፡ | - |
| [illegible] | ሽቦ | የጸጉር ጌጥ | 7.00 | ፡፡ | ፡፡ | ጸጉርን ከዓይነት ይጠብቃል ይሉታል |
| [illegible] | ነሐስ | [illegible] | 55.00 | ፡፡ | ትንታኔ አልተደረገበትም | - |
| [illegible] | ወርቅ(ብር) | የጣት ጌጥ | 78.00 | ፡፡ | ትንታኔ ተደርጎበታል | ወርቁን አሰሪው ነው የሚያቀርበውየሚያቀርበው |
| [illegible] | ወርቅ(ብር) | የአንገት ጌጥ፣ የቤተክርስቲያን ጌጥና ማስጌጫ | 95.00 | ፡፡ | ፡፡ | ፡፡ |

አባሪ 5

የአውራ መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ቱ ስም | ጾታ | ዕድሜ | ብሄር | መኖሪያ አካባቢ | ቀበሌ | የስራ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አህመድ ል | ወ | 50 | አማራ | መካነብርሃን | መካነብርሃን | በሽመና ሙያ የሚተዳደሩ የአካባቢው ነዋሪ |
| እንኩዬ | ሴ | 29 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| አለሚቱ | ሴ | 27 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| ብር፡ቱ | ሴ | 40 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| መንበር ብሆ | ሴ | 78 | ›› | ›› | ›› | ታሪክ አዋቂና የአካባቢው ተወላጅ |
| አደም ን | ወ | 45 | ›› | ›› | ›› | በሽመና ሙያ የሚተዳደሩ የአካባቢው ነዋሪ |
| ደ.ጓ፡ ሁሴው | ወ | 30 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| አዳነ ሰጠፈ | ወ | 47 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| ሰኢድ | ወ | 51 | ›› | ›› | ›› | ›› |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሰጠፋ | | | | | | |
| የኑስ ሰጠፋ | ወ | 56 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| ሹመት ኛ | ወ | 54 | ›› | ›› | ›› | ታሪክ አዋቂና የአካባቢው ነዋሪ |
| ነጋልኝ ሁ | ወ | 82 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| ፍቃዱ ሰ | ወ | 54 | ›› | ደረሰኄ | ደረሰኄ | በአንጥረኛ ሙያ የሚተዳደሩ |
| ምስጋናው ዴ | ወ | 30 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| አየሁ ኝ | ወ | 46 | ›› | ›› | ድልድሊት | ›› |
| አለሙ ዘ | ወ | 60 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| ደረሰ ሙ | ወ | 35 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| ዋ ቸኮለ | ወ | 42 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| አለሜ ዋው | ወ | 52 | ›› | ›› | ደረሰኄ | ›› |
| ጌትነት ሁ | ወ | 27 | ›› | ›› | ድልድሊት | ›› |
| አገር ሻል | ወ | 41 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| ት ስሜነህ | ወ | 26 | ›› | ›› | ›› | ›› |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ላው ዳውድ | ወ | 79 | ›› | መካነብርሃን | መካነብርሃን | ታሪክ አዋቂና የአካባቢው ተወላጅ |
| አለልኝ | ወ | 44 | ›› | ›› | ደረስጌ | በሽመና ሙያ የሚተዳደሩ |
| ከድር ፈሂም | ወ | 36 | ›› | መካነብርሃን | መካነብርሃን | ›› |
| ሰዒድ ሞላ | ወ | 41 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| ቤትእህመድ | ሴ | 32 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| እሸት ወቤ | ወ | 29 | ›› | ደረስጌ | ደረስጌ | ›› |
| ባእይቸው ድ | ወ | 35 | ›› | መካነብርሃን | መካነብርሃን | ›› |
| ደሌ ኝ | ወ | 51 | ›› | ድልድሊት | ደረስጌ | በአንጥረኝነት ሙያ የሚተዳደሩ |
| ፋንታሁን | ወ | 43 | ›› | ›› | ›› | ›› |
| አድነው ት | ወ | 55 | ›› | ደረስጌ | ደረስጌ | ቃል ገጣሚና ተራኪ |
| ላቀች | ሴ | 58 | ›› | መካነ ብርሃን | መካነ ብርሃን | ›› |
| ሞሉ ው | | 62 | ›› | ›› | ›› | የአካባቢ ነዋሪና ተወላጅ |

አባሪ 6

የኢንፎርመንት መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ስም | የሰጡት መረጃ | የስራ ድርሻ |
|---|---|---|
| አቶ የኑስ ሁሴን | መረጃ አቀባይ መጠቆምና ማገናኘት | የጃናሞራ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ |
| አቶ የሃ መሐመድ | ከጥናቱ ጋር የሚዛመድ መረጃ ሰጥተዋል | የጃናሞራ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የባህል እሴት ጥናት አጠቃቀም የስራ ሂደት ባለሙያ |
| ወ/ሪት ወሰን አያሌው | ,, | የጃናሞራ ወረዳ ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የፕሬስ ስራዎች ዜና ባለሙያ |
| አቶ ያንተነው አዳነ | ,, | የጃናሞራ ወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ የስራ ሂደት ባለሙያ |
| አቶ ሰጊድ የኑስ | ,, | የጃናሞራ ወረዳ ጥቃቅንና ንግድ ኢንዱስትሪ ጽ/ ቤት የማደራጃና ቁጥጥር የስራ ሂደት ባለሙያ |

አባሪ 7

የሽመናና የእንጥረኝነት ሙያተኞችን በቡድን ለማወያየት ቃለ መጠይቅ

• የተሳታፊዎች ስም፣ ዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ እና ስራ?

• ሙያውን እንዴት ለመዳችሁት?

• በሙያው የተሰማራችሁት ከመቼ ጀምሮ ነው?

• ሙያውን ተገልግላችሁ ምን ምን ቁሶችን ትሰራላችሁ?

•ቁሶችን ለመስራት ምን ምን ግብዓት ትጠቀማላችሁ?

• ቁሶቹን ስትሰሩ የምትከተሏቸውን ሂደቶች ቅደም ተከተል ብትገልጹልኝ?

• የምትሰሯቸውን ቁሶች ስምና ዋጋ አንድ በአንድ ብትገልጹልኝ፤ የገቢያው ሁኔታስ እንዴት ነው?

• ተደራጅቶ መስራት እንቅስቃሴው ምን ይመስላል? ያልተደራጃችሁትስ ለመደራጀት ታስባላችሁ? ካልሆን ለምን?

• ከሙያችሁ ጋር በተያያዘ የተነገሩ ቃል ግጥሞች፣ እንቆቅልሾች፣ ተረቶችን ፣ ወ.ዘ.ተ ብትነግሩኝ?

• የአካባቢው ህብረተሰብ ለእናንተና ለሙያችሁ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል? እናንተስ ለህብረተሰቡ ያላችሁ አመለካከት ምን ይመስላል?

• በሙያው ውጤታማ እንዳትሆኑ እንቅፋት የሆኗችሁን ችግሮች በዝርዝር ብትገልጹልኝ

•በሙያው ውጤታማ እንድትሆኑ የረዷችሁን ጉዳዮች ብትገልጹልኝ

## አባሪ 8

## የሽመናና የእንጥረኝነት ሙያተኞችን ለማወያየት በግል የቀረበ ቃለ መጠይቅ

- የመረጃ አቀባይ ስም፣ ዕድሜ፣ የቤተሰብ ሁኔታ፣ ስራ
- በሙያው የተሰማሩት ከመቼ ጀምሮ ነው
- የሚሰሩበት ቁሶች ስም ምን ምን ይባላል
- ምን ምን ዕቃዎችን ይሰራሉ
- የሚሰሯቸውን ቁሶች አሰራር አንድ በአንድ ቢያጫውቱኝ
- በስራዎ የሌሎች እገዛ አለ? ካለ ምን ምን ነው
- የሚሰሯቸውን ቁሶች አገልግሎት ቢነግሩኝ
- የሚሰሩት ቁስ ከህብረተሰቡ ጋር በምን በምን ይዛመዳል
- ሙያውን ከማን ተማሩት? ቅብብሎሹስ ምን ይመስላል
- የገበያ ሁኔታስ ምን እንዴት ነው
- ኑሮዎ እንዴት ነው
- እርስዎ ለህብረተሰቡ ያለዎት አመለካከት ምን ይመስላል
- ህብረተሰቡስ ለእርስዎ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል
- ሽመናን/ እንጥረኝነትን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞችን ቢነግሩኝ

አባሪ 11



ክርፋዝ

ስዕል ቁ.1

መገተሪያ



ስዕል ቁ.2



ጋሬዳ

ስዕል ቁ. 3

በሙያተኞቹ
የተሰራ ሸሚዝ



ስዕል ቁ. 4



ሚሂን

ስዕል ቁ.5

ነጠላ



ስዕል ቁ. 6



በጥበብ ጌጥ የተሰራ ጥለት

ስዕል ቁ. 7



በሰሌን ጌጥ የተሰራ ጥለት

ስዕል ቁ.8



ቁልፍ ሸማቃ

ስዕል ቁ. 9



ዝርግ ሸማቃ

ስዕል ቁ. 10



ጻፉ

ስዕል ቁ 11



መጠቅለያ

ስዕል ቁ. 12



ሙያተኛው በሻይሌ ዝሀ ሲያዘጉ

ስዕል ቁ 13



ድባብ

ስዕል ቁ. 14

## ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የኔ ወጥ ስራ (Original work) መሆኑን እና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች ምንጭ በትክክል የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም ______________________

ፊርማ ______________________

ማስረከቢያ ቀን ________________

87
14
101